መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!
©ALL RIGHTS RESERVED.

የመጀመሪያ ኅትመት ጥር 1994 ዓ.ም.
ሁለተኛው ኅትመት ጥር 1995 ዓ.ም.
ሦስተኛው ኅትመት ጥቅምት 1998 ዓ.ም.

አድራሻ:- 251 - 091 - 1 -61 70 77
☎ 251 - 011 - 2- 13 32 32
✉ 57133

E-mail Hibretyes@yahoo.com

## ማውጫ

| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፩ | ትዳር | 7 |
| | • ሠርግ ወይም ከብካብ | 7 |
| | • ቬሎ | 13 |
| | • ጥሎሽ | 17 |
| ምዕራፍ ፪ | ጋብቻ ምሥጢር፣ ታላቅ፣ ክቡር፣ ቡሩክና ንጹሕ ስለመሆኑ | 19 |
| ምዕራፍ ፫ | የጋብቻ ዓላማዎች | 24 |
| ምዕራፍ ፬ | እርግዝናንና ወሊድን መከላከል በሃይማኖት እንዴት ይታያል? | 37 |
| ምዕራፍ ፭ | ሩካቤ ወይም ተላጽቆ | 47 |
| | • ሩካቤና የእግዚአብሔር ፈቃድ | 48 |
| | • የባልና ሚስት አለመፈቃቀድ | 51 |
| | • የባልና ሚስት ሩካቤን መከላከል | 57 |
| | • በትዳር ውስጥ በሚፈጸም ሩካቤ ወሳኞቹ ሁለቱ ብቻ መሆን የሚኖርባቸው እንዴት ነው? | 72 |
| | • እግዚአብሔር ባልና ሚስት የሚለያዩበትን ሥራ አይሠራም | 74 |
| | • የሚስት ባልን መጠየቅ እስከየት? | 75 |
| ምዕራፍ ፮ | ቅድመ ሩካቤ የሚደረጉ ዝግጅቶች | 78 |
| | • ሕሊናዊ ዝግጅት | 80 |
| | • አካላዊ ዝግጅት | 85 |
| ምዕራፍ ፯ | ሩካቤና ሥርዓቱ | 89 |
| | • ሩካቤ በስውር መፈጸም አለበት ሲባል እንዴት ነው? | 92 |
| | • በሩካቤ ጊዜ ዘርን በአፍአ ማፍሰስ አይገባም | 100 |
| | • ሩካቤን በቁም መፈጸም ክልክል ነው? | 101 |
| | • ሩካቤና ስካር | 102 |
| | • በገዛ ትዳር ውስጥም ቢሆን ፍትወት ማብዛት አይገባም | 104 |
| | • ሩካቤና የእምስቱ ሕዋሳት ተይዩነት | 106 |
| | • ሩካቤና ሥርዓት አልባ እንቅስቃሴ | 107 |
| | • ሩካቤና የባልና የሚስት ትብብር | 109 |
| | • ከሩካቤ በኋላ ምን ማድረግ ይገባል? | 110 |
| | • ሩካቤን የት መፈጸም ይገባል? | 111 |
| ምዕራፍ ፰ | የተጋቡ ሰዎች ከሩካቤ የሚታቀቡባቸው ዕለታት | 115 |
| | • በሕርስ (በአራስነት) እና በትክት (በወር አበባ) ጊዜ | 116 |
| | • በእርግዝና ጊዜ | 118 |
| | • ክርስትና በማንሣት ጊዜ | 118 |
| | • ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ | 119 |

- በዓበይት በዓላትና በሰንበት ዕለት .............. 120
- ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አስቀድሞ .............. 121
- ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉ በኋላ .............. 122
- በአጽዋማት፣ በሱባኤና በቀኖና ጊዜ .............. 122

ምዕራፍ ፱ ኣታመንዝር .............. 125
- ማመንዝር ሥጋን እንዴት ይበድላል? .............. 127
- ካመነዘሩ በኋላ መሸሸግ ይቻላል? .............. 127
- የማመንዝር ቅጣት .............. 128
- ወደ ማመንዝር የሚገፋፉ ሐሳቦች .............. 129
- ከባልና ከሚስት የአንዳቸው መሞት .............. 131
- ለማመንዝር መብት ያለው ሰው ይኖራልን? .............. 132
- ማመንዝርን ማን ሊፈቅድ ይችላል? .............. 132
- ባልና ሚስት ለማመንዝር ቢፈቃቀዱስ? .............. 133



ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ በሥራዬ ሁሉ የረዳኝን ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ::

በመቀጠልም በማንኛውም መንገድ ቅን ትብብራቸውና ፍቅራቸው ላልተለየኝ ለውድ አባቴ ለአቶ የሺጥላ አደራ እንዲሁም ለውድ እናቴ ለወ/ሮ ከበቡሽ ፍሰሐና ለመላው ቤተሰቦቼ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

እጅ ጽሑፉን በማንበብ ገንቢ አስተያየትና እርማት ለሰጡኝ መምህራንና ካህናተ ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ::

መታሰቢያነቱ

በሰሜን ሸዋ ሀ/ስ/ሊ/ጳጳስ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ስም ለተቋቋመው ለማኅበረ ማርያም ዘጎርጎርዮስ፣ በፍጹም ትጋት ቤተክርስቲያንን እያገለገሉ ላረፉት ለመምህር ግርማ ከበደ፣ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ለሚገኙ ለመምህራን ቤተ ክርስቲያን በሙሉ እና ለጉ/ተ/ጽ/ቅ/ህ/ሰ/ት/ቤት ትሁንልኝ::


## መቅድም

ይህች መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ስለትዳር ጠቅላላ መንፈሳዊ ይዘትና በይበልጥ ደግሞ በውስጡ ባልና ሚስትን አንድ ስለሚያደርጋቸው ግብር ማለትም ስለ ሩካቤ አብራርታ የያዘች በመሆኗ "ትዳርና ተላጽቆ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ" ተብላ ተሰይማለች።

ትዳር የሚለው ቃል በመጠኑም ቢሆን በመጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ከመብራራቱም በላይ ዘወትር የምንገለገልበት በመሆኑ ብዙ ማብራሪያ አይሻም። በቅርብ ዓመት ውስጥ በትዳር ዙሪያ የተጻፉ ጥቂት መንፈሳዊ መጻሕፍቶች በርእሳቸው "ጋብቻ" የሚለውን ቃል ከሌሎች ዘርፈ ብዙ ቃላቶች ጋር በማዛመድ ስላሰፈሩት ከነዚያ መጻሕፍቶች ለየት ለማድረግ "ጋብቻ"የሚለውን ቃል ትቼ ይህችን መጽሐፍ "ትዳርና ተላጽቆ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብያታለሁ"።

"ተላጽቆ" የሚለው ቃል ደግሞ "ተላጸቀ" አንድ ሆነተያያዘ ፣ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ፍቺውም አንድነት የሚል ነው። ይህን ቃል ያለ ምንም ለውጥ ቅዱሳት መጻሕፍት ሩካቤ የሚለውን ቃል ለመተካት ተጠቅመውበታል። ለምሣሌ በራዕይ ፯÷፯ ላይ "ወእለ እምውስተ ሕዝበ ሌዊ እልፍ ወዕሥራ ምእት" ወይም "ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ" በማለት ወንጌላዊ ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱም ነገደ እሥራኤል ከፍጹምነት ደርሰው ለመንግሥተ ሰማያት እድምተኞች የሆኑ ሰዎችን ልክ የገለጸበትን ቃል የትርጓሜ መጽሐፋችን ሲያብራራው ሌዊ ማለት ልጹቅ ማለት ነው ተላጽቆ እንጂ በአባለ ዘርዕ ነው። አባለዘራቸውን ከክፉ ነገር ከልክለው ከፍጹምነት የደረሱ ይህን ያህል ናቸው። ሲል ያትታል ይህም 'ተላጽቆ' የሚለውን ቃል 'ሩካቤ' ለሚለው ተለዋጭ አድርጎ መጠቀም በዚህች መጽሐፍ እንዳልተጀመረ ያስረዳል።

ምንም እንኳን 'ተላጽቆ' የሚለው ቃል 'ሩካቤ' ለሚለው ቃል ብቁ ተለዋጭ መሆን እንደሚችል ከላይ የተብራራ ቢሆንም ይህን ቃል የተጠቀምኩት በርዕሱ ላይና በመጽሐፉ ውስጥ እጅግ ጥቂት በሆኑ ቦታዎች ላይ ብቻ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ይህን ቃል በብዛት ያልተጠቀምኩት 'ሩካቤ' ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ፍቺ ስላላቸው አንባቢ ይህን ከተረዳ በኋላ የቃላት መለዋወጥ ምንም ጥቅም እንደሌለው በማሰብ ሲሆን በርዕሱ ላይ ደግሞ 'ግብረ ሥጋ' ወይም 'ሩካቤ' ከሚሉት ቃላት ይልቅ 'ተላጽቆ' የሚለውን ተመሳሳይ ፍቺ ያለውን ቃል የተጠቀምኩት ከመነሻው አንባቢያንን ወደ አንድ ድርጊት ላለመሳብና መልእክቱም እንዳይፈጥ አስቤ ነው። በተጨማሪም የዚህ ቃል ፍቺ ምን ይሆን? በማለት አንባቢያኑን ለማለበም/ለማመራመር/ ስል ነው።

## መግቢያ

በዚህች መጽሐፍ መልክ ስለጋብቻና በውስጡ ስለሚፈጸም ሩካቢ(ተላጽቆ) በተብራራ መልኩ ለመጻፍ ይህ ወቅት አንገብጋቢ ወቅት ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም:-

፩) በተክሊል(በሥጋ ወደሙ) የተጋቡትን ጨምሮ ብዙ ባልና ሚስቶችን እንዳይስማሙ የሚያደርጉት ችግሮች በጥልቀት ሲታዩና ሲመረመሩ ባለትዳሮች በሩካቤ ጊዜ ያላቸውን ድርሻ፣ መብትና ግዴታ እንዲሁም በአጠቃላይ ስለሩካቤ በቂ ግንዛቤ ካለመያዛቸው የሚመነጩ ናቸው።

፪) ቤተክርስቲያን በዕድሜ፣ በጾታ፣ በመንፈሳዊ ይዞታ፣ በመለያየት ለሁሉም እንደደረጃው ጠቃሚውንና ጎጂውን ለይታ ለማስተማር የምታደርገው ጥረት በተለያዩ መገናኛ ብዙኀን በሚተላለፈው ምርትን ከግርድ ባልለየ ስብከት እየተቀደመ ነው።

፫) የዘመናችንን ክፉ ደዌ ኤድስን እንዲስፋፋ ካደረጉት ነገሮች አንዱ የትዳራቸውን ጉጣጉጥነት ለመታገሥ ባለመቻል ከትዳራቸው ወጥተው የሚማግጡ ሰዎች ቁጥር መበራከት ነው። ይህች መጽሐፍ ደግሞ የዚህ ዓይነቱን የትዳር ወጣገባነት ለማስተካከል መጠነኛ አስተዋጽኦ ታደርጋለች። በዚህና ከላይ በጠቀስናቸው ሐሳቦች የመጻሕፏን ወቅታዊነት እንረዳለን።

በነገረ ሃይማኖት ምሥጢር የተባሉና መሸሸግ የሚገባቸውን ነገሮች የምንሰውረው በቃል ከመናገርና በተግባር ከማሳየት ነው እንጂ ከማወቅና ጽፎ ከማኖር አይደለም። ለዚህም ማስረጃው ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ጠቅላላ ሁኔታው በዝርዝር ያልተጻፈ ምንም አናገኝም። መጽሐፍ ቅዱስ ያለምንም ድብብቆሽ ብዙ ነገርን ዘግቧል። አዋልድ መጻሕፍትም እንደዚሁ። ይህች መጻሐፍም ልክ ያለው ግልጽነት ይንበብባታል።

መጻሕፍትን ከማንበብና ከመስማት የቦዘኑ ሰዎች ይህችን መጽሐፍ ይልቁንም "ባልና ሚስት ከሩካቤ የሚታቀቡባቸው ዕለታት" በሚለው ርዕስ ስር የሰፈሩትን ሐሳቦች በተመለከቷቸው ጊዜ "ይህን ማን ሊፈጽመው ይችላል" በማለት ሲጠይቁ ከፊሎቹ ደግሞ "በዚህ ዓይነትማ ዓመቱን ሙሉ ተከለከልን ማለት ነው።" እያሉ በትካዜ ማዕበል መስጠማቸው አይቀርም። ሌሎች ደግሞ "የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም" ማቴ. ፲፱:፲ እንደሚሉም እገምታለሁ። ቢሆንም ጨርሰው ቢያነቧትና ሊፈጽሟት ቢጥሩ ሁሉም ነገር ካሰቡት ውጪ ሆኖ ያገኙታል።



## ምዕራፍ ፩

## ትዳር

ትዳር ከቅርብና ከሩቅ ተቀራርቦ አንድ መሆንንና ራስን ችሎ መተዳደር መጀመርን የሚያመለክት ቃል ነው ። በተለይ ግን ሁለት ዐቅመ ውርዛዌ (አካለመጠን) ያደረሱ ወንድና ሴት ተስማምተው አንድ የሚሆኑበት ምሥጢር ጋብቻ፣ አውስቦ ወይም ትዳር ይባላል። ይህ የጋብቻ አንድነት የሚፈጸምበትና ለወዳጅ ለዘመዶቻቸው ይፋ የሚሆንበት ሥርዓት ሠርግ ወይም ደግሞ ከብካብ ይባላል።

## ሠርግ ወይም ከብካብ

ሠርግ የሙሽራውና የሙሽሪት ጋብቻ የሚታወጅበትና የሚጸናበት መንፈሳዊና ባሕላዊ ዝግጅት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሙሽሮችን አስመልክቶ የሚደረግ ተድላ ደስታንም ያጠይቃል። ሠርግ እንደየሰው ባሕልና ልማድ ጎጂና ጠቃሚ ነገሮች የሚታዩበት ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ያለው መንፈሳዊ አፈጻጸሙ ግን ፍጹምና እንከን የማይገኝበት ማራኪ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስም በብሉይና በአዲስ ኪዳን ሠርግን የሚደግፉ ጽሑፎች እናገኛለን። በብሉይ ኪዳን ላባ ልጁን ራሔልን ለያዕቆብ በዳረለት ጊዜ "ላባም የዚያን ስፍራ ሰዎች ሁሉ ሰበሰበ ሠርግም አደረገ።" ዘፍ ፳፱:፳፪ በማለት ላባ ልጁን ሲድር ሠርግ ሠርጎ እንደነበር ተጽፏል።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ "በሦስተኛው ቀን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ነበረ። የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፣ ኢየሱስም ደግሞ ደቀመዛሙርቱም ወደ ሠርጉ ታደሙ።" ዮሐ ፪:፩ በማለት በቃና ዘገሊላ ዶኪማስ የተባለ ሰው ሠርግ እንደሠረገና እመቤታችንንና ጌታን፣ ተማሪዎቹን ሐዋርያትንም ወደ ሠርጉ እንደጋበዛቸው ጌታችንም ሠርጉን ሳይቃወም መገኘቱንና እንዲያውም የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ በእናቱ አማላጅነት ስድስት ጋን ሙሉ ውኃ ወደ ወይን ጠጅነት ለውጦ በአምላካዊ ሥራው ለሠርጉ መከናወን በፈጸመው ተአምር አክብሮቱን ገልጧል። እመቤታችንም ምንም እንኳን በድንግልናዋ ከዚህ ዓለም የተለየች ባሕታዊት ብትሆን ሠርግን ሳትንቅፍ ከመገኘቷም በላይ በሠርጉ ላይ ልጇ ከመጋበዙ በፊት በሥራ እየረዳች እንደነበርና ልጇንም በመለመን ል.ዩ አስተዋጽኦ ማድረጓ ሠርግ ምን ያህል ክቡር መሆኑን አስገንዝባለች። በተጨማሪም በሉቃ ፲፬:፰ላይና በማቴ ፳፪:፩-፲፬ የሰፈሩት ታሪኮች ሠርግ በሃይማኖት ክቡርና የማይነቀፍ መሆኑን ያስገነዝቡናል።

ከላይ በተገለጸው ሐሳብ መንሻነት ማንኛውም ሰው ሥርዓቱን የጠበቀና መንፈሳዊነት ያለውን ሠርግ መጥላትና መጸየፍ እንደሌለበት ጌታና እመቤታችን ሐዋርያትም አርአያ ሆነውናል። ጌታችን ያልነቀፈውን ሠርግ መንቀፍ ከፈጣሪ በላይ ነኝ ማለት ነውና። እንዲያውም እመቤታችን በሥራና በአማላጅነት፣ ጌታ ተአምራዊ ወይንን በመስጠት እንደተሳተፉ እያንዳንዱ ግለሰብ ባለው ተውህቦ (ስጦታ) መንፈሳዊ መርሐ ግብር በመንደፍ፣ በስብከት፣ በመዝሙር፣ በሀብትና በጉልበት በሌላም መንገድ ትብብር ሲያደርግ ሠርግ ታላቅ በረከት እንዳለው መታወቅ አለበት።

ሠርግ ዓይነተኛ ጥቅም አለው። አንዳንድ ሰዎች ባላቀዱት ጊዜና ባልፈቀዷቸው ሰዎች ለጋብቻ እንዳይጋበዙ ሳያገቡ ባለትዳር ለመምሰል ቀለበት ማሰራቸው እየተለመደ መጥቷል። ይህም አግብቻለሁ ማለት ብቻ እንኳን እንዴት ፈተናን ሊከላከል እንደሚችል ያሳያል። ይህ ከሆነ በእውነት ተጋብቶ ጋብቻን በሠርግ ይፋ ማድረግ ምን ያህል እርዳታ እንዳለው መረዳት ረቂቅ አይሆንም። የቀኖና መጽሐፍትን ጋብቻ ይፋ መሆን እንዳለበት ደግፎ ሲናገር "ብዙዎች ሳይሰበሰቡ በሥውር ምንም ተክሊል አያድርጉላቸው።" ፍትሕ. መን. አንቀጽ ፳፬:፳፻፶፱ በማለት ይጽፋል። ሌሎች ደግሞ ካገቡ በኋላ ከቤታቸው ደጃፍ አልፍ እንዳሉ ወይም ከባለቤታቸው እንደተለዩ የቃል ኪዳን ቀለበታቸውን በኪሳቸው ያኖሩታል። ይህንንም የሚያደርጉት ያላገባ ለመምሰልና ለመባለግ እንዲረዳቸው ነው። ለዚህ ችግር መጠነኛ መፍትሔ የሚሆነው ጋብቻን ግልጽ ማድረግ ነው። ምክንያቱም በተለይ እንደ ሀገራችን አኩሪ ባሕል አንድ ሰው ማግባቱ ከታወቀ ለሁለተኛ ጋብቻ የሚጠይቀው የለም እርሱም ለመጠየቅ ቢሞክር አስቀድሞ ማግባቱን እያወቀ ሐሳቡን የሚቀበል አይኖርም። በዚህም ግልጽ ጋብቻ ሰዎችን ከመፈተንና እነርሱንም ከመባለግ እንደሚታደጋቸው እንረዳለን። ጋብቻ በአዋጅ የሚገለጸው ደግሞ በሠርግ በመሆኑ የሠርግን ጠቀሜታ አወቅን ማለት ነው።

በተጨማሪም ያገቡ ሰዎች ማግባታቸው በይፋ ከተገለጠበት (ከሠርጋቸው ዕለት) ጀምሮ እንደ ዕድር፣ ሠርግ እና በመሳሰሉት ሌሎች ማኅበራዊ የሕይወት ጉዞዎች እንደሙሉ ሰው ታይተው ተሳታፊዎች ይሆናሉ እንጂ እንደ አንድ ቤት ንዑስ አባል ወይም ልጅ ተደርገው አይቆጠሩም።

አንድ ሰው በሚወለድበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በዕድሜ ከእርሱ የሚበልጡ ሰዎችና ወላጆቹ ከሚነግሩት ታሪክ በቀር አዝኖም ተደስቶም እንደነበር ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። እንደዚሁም ሁሉ "ከእርሱ በኋላስ የሚሆነውን ያይ ዘንድ የሚያመጣው ማን ነው"



መክ ፫:፳፩ እንደተባለው ሰው ከሞተ በኋላ ምን ተደርጎ ይሆን? በማለት ለማየት አይመጣምና በሞተ ጊዜ እና ከዚያ በኋላ ያለውን ሁኔታ የማንኛውም ሰው ነፍስ ሕያዊትና ለባዊት ስለሆነች ቢያውቅም እንኳን ወደዚህች ዓለም መጥቶ ሥጋዊ ተድላ አያደርግም። ስለዚህ በሚወለድበት ጊዜ ያላወቀውንና ከሞተም በኋላ የማያገኘውን ደስታ ዓይኑ እያየችና እያወቀ ማግኘት የሚችለው በሠርጉ ዕለት ነው። ሠርግ የልደትና የሞት ጥምር በዓል ነው። ሙሽራ ክቡር ነው። ሙሽርነትም እጅግ አስደሳች ወቅት ነው። ይህንንም ጌታችን ራሱ "ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን?" ማቴ ፱:፲፭ በማለት ሠርግና ሙሽርነት ከሙሽሮች አልፎ ለሚዜዎችም ጥምር የደስታ ወቅት መሆኑን ገልጿል። ምናልባትም አንድ ጠያቂ ይህንን ቃልግ ጌታችን ስለራሱና ስለሐዋርያት መስሎ ተናግሮት የለምን? ሊል ይችል ይሆናል። እርግጥም በወርቁ ጌታ ስለራሱ የተናገረው ቢሆንም በሰሙ ግን ማንኛውንም ሙሽራ ይመለከታል። ጌታ በሌላ ነገር ምሳሌ አይመስልምና። ስለሆነም ሠርግ የሙሽርነት እምብርት በመሆኑ በዕለቱ ፍጹም ደስታ ይደረጋል።

መንፈሳዊያን ሰዎች በሙሉ በሠርጋቸው ዕለት መጨነቅ የሚገባቸው እግዚአብሔርን ሳያስቀይሙት እንደምን ባለ ሥርዓት ሠርጋቸውን መፈጸም እንደሚገባቸው በማሰብ ነው እንጂ በሠርጋቸው ላይ በመገኘት የኅደላቸውን የሚሞላና የጋብቻ ሕይወታቸውን የሚቀድስ መንፈስ ቅዱስን እያሳዘኑ ቁሳዊ ለሆኑና ለሙሽሮች አንድነት ምንም ዓይነት ጠቀሜታ ለሌላቸው ነገሮች መጡ፣ ቀሩ፣ ተገኙ፣ ጠፉ እያሉ መጨነቅ ተገቢ አይደለም። አዳምና ሔዋን በተጋቡ ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ አንድ እንዲሆኑ አደረጋቸው እንጂ ብዙ ታዳሚዎች፣ ዓይነቱ ብዙ የሆነ ድል ያለ ድግስና ዛሬ ያሉ ዘመናዊ መጓጓዣ ተሽከርካሪዎች በሠርጋቸው ላይ አልተገኙም ፤ ነገር ግን ጋብቻቸው በእግዚአብሔር የተወደደና በመላእክት የታጀበ ስለነበር በውድቀታቸውም በመነሣታቸውም አንድ ሆነው ኖሩ። ምክንያቱም ሙሽሮችን አንድ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ የደመቀ የሠርግ ሥርዓት አይደለምና፤ ሠርግ ስለሙሽሮች ተዘጋጅቷል እንጂ ሙሽሮች ስለሠርግ ተብለው ሙሽሮች አልሆኑም ይህን ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ከሚያገቡት ሰው ይልቅ ተጨንቀውና ወደው የሚያከብሩትና ዘብ የሚቆሙት ለሠርጋቸው መድመቅና ማማር ነው። ስለዚህም ሠርጋቸው ምን መምሰል እንዳለበት ሲወያዩ በሐሳብ መግባባት ባለመቻላቸው ምክንያት ጋብቻቸውን ጨርሶ የሰረዙ ወይም በየቀኑ ወደ ስምምነት እስኪደርሱ ድረስ የጋብቻ ዕለታቸውን የሚያራዝሙ ሰዎች አልጠፉም።

ማስደሰት ይገባናል እንጂ በልጅቱ ዘፈን ምክንያት የዮሐንስ አንገት እንደተቆረጠች እኛ ክርስቲያኖችም ብዙዎች ኃጢአት ሠርተው በነፍስ የሚሞቱበትንና ሃይማኖታችንም የሚነቀፈውን ዘፈንና ስካር ከሠርጋችን ማራቅ ይጠበቅብናል። በዘፈኗ ተደስቶ ሄሮድስ የዮሐንስ መጥምቅን ራስ እንደሰጣት መንፈሳዊ ጨዋነት በተሞላ የሠርግ ሥርዓታችን ክርስቶስን ብናስደስተው የዮሐንስን ራስ ሳይሆን ክብር ያገኘበትን ጸጋውን በረከቱንና የጽድቅ አክሊሉን ይሰጠናል። ስለዚህ ሠርጋችን እንደ ቃና ዘገሊላ ሠርግ የጎደለንን የሚሞላ ጌታ፣ በጽድቅ የምታማልደን መንፈሳዊ እናት እመቤታችን፣ ትጉሃን መላዕክትና ቅዱሳን ሐዋርያት የሚገኙበት ሊሆን ይገባል እንጂ የክት ልብስ የለበሱ ጌጠኞች ብቻ የሚያጅቡት መሆን የለበትም። ጋብቻችን በሥጋውና በደሙ ታትሞ በፍጹም መንፈሳዊነት ታጅቦ ሕይወት የምናገኝበት ካልሆነ የብዙ ሰዎች እኛን አጅቦ መጨፈር ምን ይጠቅመናል። 'በድን ባለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ' ተብሏልና። ማቴ. ፳፬:፳፰።

ያለ ምንም የሠርግ ዝግጅት መጋባት ይቻላል፤ ለዚህም ሁለት ራሳቸውን ብቻ ሆነው ተጋብተው የሚኖሩ ሰዎች ምስክሮች ናቸው። በተጨማሪም በባለቤቶቻቸው ሞት ምክንያት ዳግመኛ ስለሚያገቡ ሰዎች ሠርግ ሲናገር "በሰፊ ዝግጅትና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አይሁን" በማለት የቀኖና መጽሐፋችን ያዛል። ፍት.ሕ. መን. አንቀጽ ፳፬፥ ይህም ያለ ሠርግ ዝግጅት ሥጋ ወደሙን በመቀበልና መንፈሳዊ ሥርዓቱን በመፈጸም ብቻ ጋብቻ ሊፈጸም እንደሚችል ምስክር ነው። አንዳንድ ሰዎች ሠርጋቸውን ከነዳያን ጋር አሳልፈውታል። ሉቃ. ፲፬:፲፪-፲፬ የሠርግ ወጪአቸውን ድኩማንን ለመርዳት አበርክተው ያለ ምንም የሠርግ ዝግጅት ወደ አዲስ ጎጆአቸው የገቡም አሉ። ከክርስቲያኖች ሁሉ እንዲዚህ ያለ መንፈሳዊ አርበኝነት የሚጠበቅ ሆኖ ባለ ይህን አለመፈጸማችን ሳያንሰን እግዚአብሔር የማይወደውን ድርጊት ስንፈጽምና በተለያዩ ሁለት ቀናት መንፈሳዊና ዓለማዊ የሠርግ ሥርዓቶች በማዘጋጀት ራሳችንን ከማስጨነቃችንም በላይ ሁለት ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ሥርዓቶችን በአንድ ሕይወታችን ለማስኬድ በመሞከር ቤተክርስቲያንን እንበድላለን። እንዲህ ዓይነቱ ሥራ መጥገብን በማያውቁ በግፈኞች እንጂ ቁጥብ ምኞት ባላቸው በክርስቲያኖች ሕይወት መታየት አልነበረበትም። ያለሙሽራ ሠርግ የለም ያለ ሠርግ ግን ሙሽርነት አለ። ይህን ተረድተን ውጫዊ ነገሮች አባብለውን በዕዳ በመዘፈቅ፣ በማጭበርበር፣ በመስሰትና በግፍ ለሠርግ የሚሆን ወጪ ከማዘጋጀት ምኞትን በልክ አድርጎ ዕቃም የፈቀደውን ብቻ ማድረግ ተገቢ ነው። በሰው ላብ፣ እንባ እና ደም ጋብቻችንን መሥርተን



በነፍሳችን፣ በሥጋችንና በልጆቻችን ላይ ጥፋትን ከምናመጣ የአንድ ቀን ሥጋዊ ተድላ ቢቀርም እንኳን እንዳልተጎዳን ማሰብ አለብን። ያየነውንና የሰማነውን ነገር ሁሉ በእኛም ሠርግ ላይ መደረግ አለበት ካልንና ከጎመጀን መለያየታችን ከደጃፋችን ቆሟል ማለት ነው። ምክንያቱም ምኞት መለያየትን ያመጣልና "መለየት የሚወድ ምኞቱን ይከተላል።" ምሳ. ፲፰:፩ በማለት ጠቢቡ በግልጽ ያስፈረው ለዚሁ ነው።

በመጨረሻም ሰው ሁሉ ማወቅ ያለበት በተለያዩ ምክንያቶች ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል መፈጸም ያልቻሉ ሰዎች ንስሐ ገብተው ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ዝግጁ እስከሆኑ ድረስ ጋብቻቸውን ለማጽናት የቤተክርስቲያን ደጆች ዘወትር የተከፈቱ መሆናቸውን ነው። ነገር ግን ማንኛውም ክርስቲያን ጋብቻውን በመንፈሳዊ መንገድ (በሥርዓተ ተክሊል) መፈጸም እንዳለበት ልቡናው እያወቀ ከእግዚአብሔር ሕግ ወጥቶ ልቡናው እንደወደደው ለመሆን በመፈለግ ለምሳሌ:- ከጋብቻ በፊት ሩካቤ ለመፈጸምና ጋብቻው በቬሎ ወይም ከሥርዓተ ተክሊል ጋር አብሮ በማይጓዝ አሕዛባዊ ሥርዓት ለማድረግ ወዶ "ቁርባን እኮ ከጋብቻ በኋላ የሚደረስበት ነገር ነው። አሁን ግን በወደድነው መንገድ ብንጋባ ምን አለበት?" ቢል በእግዚአብሔር እየዘበተ መሆኑን ሊያውቀው ይገባል። መጽሐፋችን ደግሞ "አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም።" ገላ ፮:፯ በማለት ይህን የመሰለ ነገር ፈጽመን መሞከር እንደሌለብን ያስጠነቅቀናል።

## ቬሎ

ቬሎ በአውሮፖና በሌሎችም አህጉራት ለሠርግ የሚለበስ የሙሽራ ልብስ ሲሆን በሀገራችንም ብዙ ሰዎች በቬሎ ካልተሞሸሩ ያገቡ መሆናቸውን እስከመጠራጠር ደርሰው ለሠርግ ቬሎ መለበስ እንዳለበት አምነዋል።

"ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ይሏታል" እንደሚባለው ቬሎን በሀገራችን ብዙ ሴቶች ስለሚናፍቁት በእርሱ ለመሞሸር እንዲረዳቸው በግድ ያማረ ትርጉም ሊሰጡት ቢሞክሩም ብዙ ሰዎች የሚስማሙት ቬሎ ከወንድ ጋር የባለቁ ሴቶች የሚሞሸሩበት የሠርግ ልብስ መሆኑን ነው። ይህን ያሰኘው ብዙ ጊዜ ሙሽሮቹ ከሠርጋቸው አስቀድሞ በወለዷቸው ልጆች ሻማ ያዥነት ስለሚታጀቡና ቬሎ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚያወግዝ ሥርዓት ስለሌለው ነው። ስለሆነም ቬሎ ንጽሕናን ከሚሻ ሥርዓተ ተክሊል ጋር ጎን ለጎን መሄድ የማይችል መሆኑን ልብ ይበሉ።

ከባህል አንጻር ስንመለከተው ቬሎ ባሕላችን አይደለም። ከሁሉ የሚያስደንቀው ደግሞ የባህሉ ባለቤቶች እንኳን ለፊልምና ለተለያዩ መስል ዝግጅቶች ካልሆነ በቀር በእውነተኛ ሠርጋቸው በስፋት የማይጠቀሙበትን ዘርፋፋና ሰፊ ቬሎ እኛ ለሠርጋችን ስንጠቀምበት እነርሱ ግን በየዕለቱ ከሚለብሱት የተለመደ አለባበስ እምብዛም ባልተለየ አለባበስ ሠርጋቸውን ሲፈጽሙ ማየታችን ነው።

ማንኛውም ግለሰብ ጎጂነት እስከሌለው ድረስ የሀገሩን ባህል መጠበቅ ይገባዋል። የኛ የኢትዮጵያውያን ደግሞ እያንዳንዱ ባህላችን ከባህልነቱ በተጨማሪ ከእውነተኛይቱ ሃይማኖታችን ጋር በቁረኝነት የሚገዝ ስለሆነ ከየትኛውም ሀገር ዜጋ ይልቅ ባህላችንን የመጠበቅ መንፈሳዊ ግዴታ አለብን። ስለሆነም እጅግ የሚያኮራ የሀገር ልብስ፣ካባ እና ልብስ ተክሊል እያለን ቬሎን ስንፈልግ መገኘታችን እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው።

የሠርግ ልብስ በሃይማኖታችን ትልቅና ልዩ ክብር ላላቸው ለጥምቀትና ለንስሐ ምሳሌ በመሆኑ ራሱ የሠርግ ልብስ ልዩ ክብር የሚሰጠው ነው። የሠርግ ልብስ አለመልበስና ለሠርግ ተገቢ የሆነውን ልብስ በማይገባ ለውጦ መጠቀም እንደሚያስቀጣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያትን በሠርግ መስሎ በሚያስተምርበት ጊዜ "ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው አየና ወዳጄ ሆይ የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው። እርሱም ዝም አለ። በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን እጁንና እግሩን አሥራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።" ማቴ. ፳፪ ፲፩-፲፫ ያለው ቃል ያስረዳል። ከዚህ ዐረፍተ ነገር እንደተረዳነው ታዳሚ እንኳን የሠርግ ልብስ ባለመልበሱ የሚጠየቅ ከሆነ የሠርግ ራስ የሆኑ ሙሽሮችና የሚያጅቧቸው ሚዜዎች በሚገባ ልብስ ካልተሸለሙ ምን ዓይነት ወቀሳ እንደሚጠብቃቸው መገመት ይቻላል። ስለዚህ የሠርግ ልብስ ተገቢ ትምህርት ሊሰጥበት ይገባል እንጂ 'ይህ አያከራክርም እንደሆነ ይሁን' የሚባል ተራ ነገርም አይደለም።

ሙሽሮች ከወዳጅ ዘመዶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ይልቅ በሠርጋቸው ላይ እንዳይፈጸም የፈለጉትን ነገር ለማስቀረት ወሳኝ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል። ይህ መሆን ሲገባው ብዙዎች "ቤተሰቦቻችን በቬሎ ካልተሞሸራችሁ የሙዚቃ ባንድ ካላቆምንላችሁ አይሆንም አሉን" እያሉ ራሳቸው የሚሹት ሆኖ ሳለ ከትችት ለመዳን በቤተሰባቸውና እርስ በእርስ ሲያመካኙ ይታያል። እንዲህ የሚሉ ሰዎች የሚያገቡት ሰው በቤተሰባቸው ቢጠላ ለመተው ይፈቅዳሉን? ጨርሶ አይፈቅዱም



ቢፈቅዱም ተሳስተዋል። የማይፈቅዱ ከሆነም ቤተሰቦቼ እኔ ያልፈቀድኩትን ነገር በሠርጌ ላይ አደረጉብኝ ማለት እንዴት ይቻላል? ስለዚህ የራሳችንን አቋም ማስተካከል ይጠበቅብናል! እኛ ባንፈቅድ ቤተሰቦቻችንን መርታት ቀላል ነውና።

ከሁሉም ነገር በፊት መቅደም ያለበት መንፈሳዊ ሕግና ሥርዓት ነው። መንፈሳዊነት የማይፈቅድልንን ማንኛውንም ዓይነት ተግባር በሠርጋችን ላይ ማከናወን ከወቀሳ አያድነንም። ነገር ግን ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ጉዳትና ጥቅም የሌላቸው ሥጋዊ ድምቀትን የሚያጎናጽፉ የተለያዩ ባህሎችና ጊዜ የሚወልዳቸው አዳዲስ ሥርዓቶች ስላሉ የማንኛውም ክርስቲያን ሠርግ ይህን መምሰል አለበት በማለት የሠርግን ዝግጅት መልክ ማስያዝና ወሰን መሥራት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ እንደኔ ባለ ኅጡእ አእምሮ ግለሰብ የሚሞከር ጉዳይ አይደለም። ስለሆነም ብመምህራን ቤተክርስቲያንና በምክረ ካህን በመታገዝ ሠርጋችንን በተገቢ ሥርዓት መፈጸም አለብን።

## ጥሎሽ

ጥሎሽ ቅድመ ጋብቻ ሙሽራው ለሙሽሪት እንደ ዐቅሙ የሚያበረክተው ስጦታ ነው። ከዚህ አስቀድሞ በመተጫጨት ጊዜ የሚያደርግላት ስጦታ ማጫ ሲባል ፤ ከቤተሰቦቿ ጎጆ መውጫ እንዲሆናት የሚበረከትላት ስጦታ ደግሞ ትልወት ይባላል።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የእምነት፣ የተስፋ እና የፍቅር ምሳሌ የሆኑ ወርቅ፣ እጣንና ከርቤን በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል፣በቅዱስ ገብርኤልና በቅዱስ ሩፋኤል አማካይነት ለአዳም ሰጠው። አዳምም ይህን ሁሉ ለሔዋን ሰጣት። ሚስትም ሆነችው ደረሰባትም አቤልንም ወለደች። ይህም ወርቅ ዕጣንና ከርቤ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ ለሰብአ ሰገል ደርሷቸዋል እነርሱም ከምሥራቅ ኮከብ እየመራቸው በመጡ ጊዜ ለጌታ አበርክተውለታል። ማቴ. ፪:፲፩። በተመሳሳይ መልኩ አዳም ለሔዋን እንዳበረከተው ስጦታ ባልም ለሚስቱ እምነት፣ ተስፋና ፍቅርን ማሳየትና የተለያዩ ስጦታዎችን ማበርከቱ እጅግ የሚወደድ ሆኖ ሳለ ከአቅም በላይ በመጨነቅ፣ ብድር በመግባትና በመዋስ የሚደረግ ጥሎሽ ግን ለብዙ ሰዎች የጋብቻ ኑሮ እንቅፋት ሆኗል።

ባል ለሚስቱ እምቃ ማቅረቡ የሚነቀፍ አይደለም። እንኳን በሠርጓ ዕለት ይቅርና ካገባትም በኋላ በማንኛውም ጊዜ ወቅት ጠብቆ ስጦታ ቢሰጣት ይመስገንበታል ፍቅራቸውንም ያደራጀዋል። ስጦታ የፍቅር መግለጫ ነውና። እግዚአብሔር የእጁ ፍጥረታት የምንሆን እኛን የሰው ልጆችን ምን ያህል እንደሚያፈቅረን ካስረዳበት መንገዶች ዋነኛው ስለ እኛ ሲል አንድያ ልጁን ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት አሳልፎ

አድርገው ሲወስዱት እንመለከታለን። ነገር ግን ጋብቻ ለብቻ ከመኖር የሚበልጥ የብቸኝነት ታላቅ በመሆኑ እግዚአብሔር "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ አግባብ አይደለም" በማለት ሔዋንን እንደፈጠረለት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናነባለን። ዘፍ. ፪:፲፰ ቅዱስ ጳውሎስም ስለጋብቻ በሚናገርበት ጊዜ "ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው" ኤፌ. ፭:፴፪ በማለት ጋብቻን 'ታላቅ' በማለት የገለጸው ሳያገቡ በተናቀና በተዋረደ ተግባር በዝሙት ሲልከሰከሱ ከመኖርና ተለይቶ ምናኔ ወይም ምንኩስና ተብሎ ከማይጠራ ወንደላጤነት እና ሴተላጤነት ይልቅ ጋብቻ ታላቅ ዋጋ ያለው መሆኑን ለመግለጽ ነው።

## ጋብቻ ክቡር ነው

መጽሐፍ ቅዱስ "ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ" ሮሜ. ፲፫:፯ በማለት ይመክረናል። በክርስትና ሃይማኖት ከከበሩ ነገሮች አንዱ ደግሞ ጋብቻ ነው። ስለዚህ ሁሉም ባለትዳር ለጋብቻው ልዩ ክብርን መስጠት፣ በሌሎች ሰዎችና በራሱም ዘንድ ጋብቻ የተቃለለ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባዋል። ጋብቻን የሚያከብር ሰው እርሱ ይከብራል። እግዚአብሔር እርሱ ያከበረውን ማንኛውንም ነገር ሰዎች ቢያቃልሉበት አይወድምና። ጋብቻን የሚያቃልሉትን እርሱ ያቃልላቸዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጋብቻ በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ. ፲፫:፬ ያለውን በመገንዘብ ያላገቡ ሰዎች ከሚያዋርድ አኗኗር ራሳቸውን በማላቀቅ የክብር ሁሉ ግምጃ ቤት ወደምትሆን ወደ ትዳር ለመግባት መሽቀዳደም ይኖርባቸዋል። ጋብቻ አክብረው ወደ እርሷ የገቡትን ታከብራለችና።

## ጋብቻ ቡሩክ ነው

በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን 'ብዙ ተባዙ' ብሎ ሲባርካቸው ጋብቻ የተባረከ ሆነ። በመቀጠልም "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው" የሚል ትንቢት የተነገረለት አስካለ በረከት (የበረከት ፍሬ) ጌታችን ራሱ በቃና ዘገሊላ በተዘጋጀ ሠርግ በመገኘትና የጎደለውን በመሙላት በኃጢአታችን ምክንያት እርግማን ወድቆበት የነበረውን ጋብቻ ዳግመኛ ባርኮ አስረክቦናል። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያስወግድ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል መዝገበ በረከት ነውና። ቅድስት ኤልሳቤጥም እመቤታችንን ስታመሰግን "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።" ሉቃ. ፩:፵፪ በማለት ቡርክት



እመቤታችን የወለደችልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበረከት አባት መሆኑን ባደረባት መንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ ምስክርነቷን ሰጥታለች።

ጠቢቡ ሰሎሞንም ጋብቻና ሩካቤን በወንዝና በምንጭ መስሎ የጋብቻን ጣዕምና እርካታ በገለጸበት አንቀጽ እንዲህ ብሏል "ከጉድጓድህ ውኃ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ" ይህም ፈቃደ ሥጋ በተነሣብህ ጊዜ የግልህ ከሆነች ከሚስትህ ጋራ ተኛ እንጂ የሌላይቱን ብብት አትቀፍ ማለት ሲሆን ቀጥሎ "ምንጮችህ ወደ ሜዳ ወንዞችህ ወደ አደባባይ ይፈሳሉን? ለአንተ ብቻ ይሁኑ ከአንተ ጋር ላሉ እንግዶችም አይሁኑ" ይላል ይህም ሚስትህ ትሰስናለችን? አንተስ ታመነዝራለህን? ሚስትህ ለአንተ ብቻ ትሁን አንተም ከነምንጭህ ለእርሷ ብቻ ሁን በአንተ ዘንድ ላሉ እንግዳ ሴቶች አትሁን አታመንዝርም ይልና "ምንጭህ ቡሩክ ይሁን ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ" ምሳ. ፭:፲፭-፲፰ በማለት በጋብቻችን ደስ እንድንሰኝና ሩካቤያችንም ቡሩክ እንደሆን ጨምሮ ጠቅሶልናልና።

## ጋብቻ ንጹሕ ነው።

ዝሙት ክርስቲያኖች ሊጸየፉት የሚገባ የረከሰ ተግባር ነው። ጋብቻ ግን የተቀደሰና ንጹሕ የሆነ እግዚአብሔር ወዶና ፈቅዶ ለሰው ልጆች የሸለማቸው ብርቅ ስጦታ ነው። ስለዝሙት ርኩስነት የምንሰማቸው ስብከቶች በጋብቻ ንጹሕነት ላይ እንድንጠራጠር ተጽዕኖ ሊያሳድሩብን አይገባም፡፡ ሌብነት እና ደከሞ ሠርቶ ምንዳ (ደመወዝ) መቀበል የተለያዩ እንደሆኑ ሁሉ በትዳር መሐል በሚገባ መልኩ የሚፈጸም ሩካቤ እና ዝሙት ፍጹም የተለያዩ ናቸው።

ብዙ ክርስቲያኖች ግን የጋብቻን ንጹሕነት ከመስማት ብቻ በቀር ከሰውነታቸው ጋር በእምነት ስላላዋሐዱት በተቀደሰ ጋብቻቸው የሚፈጽሙትን ሩካቤ ላለመፈጸም ሲጸየፉና ሲሸሹ ሌሎች ደግሞ ከፈጸሙት በኋላ ስሕተት እንደሠሩና እንደረከሱ አድርገው በመቁጠር ኅሊናቸውን ሲያስጨንቁ ይታያል። ይህ አመለካከት የቤተ መቅደስንና የቤተ ጣዖትን፣ የሚያምንንና የማያምንን፣ የክርስቶስንና የቤልሆር (ዲያብሎስን) ልዩነት አጥቶ እንደመዳከር ነው ፩ኛ ቆሮ. ፯:፲፬-፲፯ ጋብቻንና በውስጡ የሚፈጸም ሩካቤን እንደረከሰ ነገር ማሰብ ፍጹም ንስሐ የሚያስፈልገው ኃጢአት ነው።

ባላጋራችን ዲያብሎስ በመልካም ጋብቻ ይቀናል። ስለሆነም ባለው ችሎታ ሁሉ ተጠቅሞ የትዳራችንን ካስማ ለመንቀል ይጥራል። አስቀድሞ ወደ ትዳር እንዳንገባ ብዙ እንቅፋት በመፍጠር በኃጢአት እየተንከባለልን እንድንኖር ያደርጋል። ይህ ካልሆነለት ደግሞ ካገባን

በኋላ በማግባታችን እስከንጸጸት ድረስ በትዳራችን ብዙ ፈተና ያመጣና ጋብቻችንን እንድንጠላው ያደርገናል። ይህም ካልተሳካለት ያለ መጠን እንድንመጻደቅ በማድረግ በተቀደሰ ጋብቻችን የምንፈጽመውን ሩካቤ እንደ እድፍ ቆጥረን እንድንጸየፈውና ከባለቤቶቻችን ጋር በምንጣፍ እንዳንገናኝ የማይጠቅም መንፈሳዊ ትጋት ያሳድርብናል። ይህንን የሰይጣን ሽንገላ ተረድተን በትዳር የሚፈጸመውን ሁሉ በማክናወን ትዳራችንን ማጽናትና ማክበር ይጠበቅብናል።

ዝሁላነ አእምሮ (አእምሮአቸው የዛገ) የሚባሉ አይሁድ እና ሁለት አማልክትን በማምለክ የሚታወቁ ግኖስቲኮች ጋብቻን ይቃወሙ ነበር። በተለይ ግኖስቲኮች ደግና ክፉ አማልክትን ስለሚያመልኩ እንደ እነርሱ እምነት ወንዶች የደጉ አምላክ ፍጥረታት ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ የክፉ አምላክ ፍጥረታት ናቸው። ስለዚህ በእነርሱ አመለካከት ጋብቻ የሁለቱን አማልክት ፍጥረታት እንደመቀላቀል ስለሆነ መጋባትን ፈጽመው ያወግዛሉ። እነዚህን ሰዎች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ" ፩ኛ ጢሞ. ፬፡፫ በማለት ነቅፏቸዋል። ክርስቲያኖችም በአንድ አምላክ ብቻ ልባቸውን በማሳረፍ የጋብቻን ቅዱስነት በማመንና የግኖስቲኮችን የተሳሳተ ሐሳብ በመንቀፍ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ይተባበራሉ።

ከላይ የጠቀስናቸው አይሁድና ግኖስቲኮች ያቆዩት እርሾ ያቦካቸው አንዳንድ የክርስቲያን ሊጦች ቢኖሩ በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት መሠረት ከግኖስቲኮች ጋር በአንድነት እንዳይወገዙ የተቀደሰ ጋብቻን ከመንቀፍና ርኩስ ከማለት ሊመለሱ ይገባቸዋል። እግዚአብሔር የቀደሰውን ርኩስ ነው ይልዘንድ ሰው ምንድር ነው? "እግዚአብሔር የቀደሰውን አንተ አታርክሰው" የሐዋ. ፲፡፲፭ የሚል ጽሑፍ አለና። ሰዎች የተቀደሰውን ነገር እንደረከሰ ነገር መቁጠር የሚጀምሩት በአንጉል ሰብከቶችና በዙሪያቸው ከሚያዩዋቸው ክፉ ክፉ ክንውኖች የተነሣ የገዛ ሕሊናቸው ሲረክስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው።" ቲቶ. ፩፡፲፭ ይላልና። ለማንኛውም ሰው ከማግባቱ በፊት ከሁሉ የሚቀድመው የጋብቻን ንጹሕነትና ተወዳጅነት በሚያሳስብ ትምህርት ሕሊናውን ማጽዳት ነው።

በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት የጋብቻን ንጹሕነት የሚጠቁሙ ጽሑፎች ይገኛሉ። መጽሐፈ ቀዳሴ "እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሯቸዋልና" ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ.



፲፫፡፬ በማለት ጽፏል። 'መኝታውም ንጹሕ ይሁን' ሲል የመኝታችን ትራስና አንሶላ ንጹሕ መሆን እንዳለባቸው ለመጠቆም ሳይሆን ማንኛውም ሰው የባልና የሚስት ግንኙነታቸው ንጹሕ መሆኑን በሕሊናው ይረዳ በልቡ ይመን ለማለት ፈልጎ ነው። ምክንያቱም አንሶላና ትራስ ከመንፈሳዊ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት ስለሌላቸው ሐዋርያው ተጨንቆ መልእክቱን የሚጽፍባቸው ጉዳዮች አይደሉም። ደግሞም ዐቅሙ እስካለውና ሁኔታዎች እስከፈቀዱለት ድረስ ማንኛውም ሰው ለራሱ ያውቃልና አንሶላና ትራስህን ንጹሕ አድርግ የሚል መልእክት አያስፈልገውም። ስለዚህ ሐዋርያው በግልጽ 'መኝታውም ንጹሕ ይሁን' ያለው በተዋዋ የባልና የሚስት ግንኙነት ንጹሕ መሆኑን ለማሳሰብ ነው።

በሌላ አቅጣጫ የጋብቻን ንጹሕነት የሚጠቁም ነጥብ በፍትሐ ነገሥት ሰፍሯል፤ በአንድ ዕለት ውስጥ ሰባት የጸሎት ጊዜያት እንዳሉ ከብዙ ክርስቲያኖች የተሰወረ አይደለም፤ ከሰባቱ ጊዜያት ውስጥ ሁለቱ ማለትም ጸሎተ ሌሊት እና ጸሎተ ነግህ ከመኝታችን ተነሥተን የምንጸልያቸው ስለሆኑ ምናልባትም በሕልመ ሌሊት(ዝንየት) ምክንያት ስአበት (ርኩሰት) ሊያገኘን ስለሚችል ፊትን፤ እጅንና እግርን በውኃ በማበስ ያም እንኳን ባይሆን ከአፋችን እንትፍ ብለን ፊታችንን ካበስን በኋላ ለጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደሚገባ ሥርዓት ተሠርቷል። ባልና ሚስት ግን ይህንን ሥርዓት ባይጠብቁ እንኳን እዳ የለባቸውም ለምን ቢባል የባልና የሚስት ግንኙነት ንጹሕ ነውና። ለብቻችን ሆነን በሕልማችን ከምንፈጽመው ዝሙት ጋር እንኳን የባልና የሚስትን ሩካቤ ማመሳሰል አይቻልም። መጽሐፋችንም ይህን ሲያብራራ "ካልታጠብን አንጸልይም አይበሉ ግንኙነታቸው የተቀደሰ ነውና።" በማለት ያትታል።

"ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና" ማቴ. ፭፡፰ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለማየት ንጽሕና ዋነኛ ነገር መሆኑን ገልጿል። ቅዱስ ጳውሎስም "ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለእርሱ ጌታን ሊያይ የሚችለው የለምና።" ዕብ. ፲፪፡፲፬ በማለት ያለ ቅድስና እግዚአብሔር እንደማያድርብንና ልናየውም እንደማንችል ገልጾልናል። የእመቤታችን የቅዳሴ መጽሐፍም ነቢያት እግዚአብሔርን እንዴት እንዳዩት ሲገልጽ "እስመ በእንጽሐ መንፈስ ርእዮ ነቢያት ለእግዚአብሔር ወተናጸሩ ገጸ በገጸ" ይህም ማለት "ነቢያት ልቡናቸውን ንጹሕ በማድረግ እግዚአብሔርን አይተውታል ፊት ለፊትም ተያይተዋልና" በማለት ይጽፋል ሰው ባልንጀራውን

እንደሚያናግር ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ለቃል የተነጋገረ ሙሴ የተገኘው ከጋብቻ ከመሆኑም በላይ ራሱም ባለ ትዳርና የልጆች አባት ነበር። ይህም የጋብቻን ቅዱስነት ያሳያል። ጋብቻ ንጹሕ ባይሆን ኖሮ ባለትዳሩ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ባልተፈቀደለትም ነበርና። እርሱም ብቻ ሳይሆን አርከ እግዚአብሔር የተባለ አብርሃም፣ ልበ አምላክ የተባለ የእግዚአብሔር ነቢይ ዳዊት እና ሌሎችም ቅዱሳን አባቶቻችን በትዳር በመኖራቸው ምክንያት ተመሰገኑ እንጂ አልረከሱም ወይም የቅድስና ማዕረግ አልቀረባቸውም። የዚህን ነገር ምክንያት የቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ሲያብራራ "ወኢኮነ አውሰቦ ንጹሕ ዘያረኩሶ ለሰብእ እም አመኮነ" "ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ንጹሕ ጋብቻ ሰውን የሚያረክሰው አልሆነም" በማለት ብዙ አባቶቻችን በጋብቻ ኖረው ቅዱሳን የተባሉት ጋብቻ ንጹሕና ርኩሰት የሌለበት ስለሆነ እንደሆነ መልስ ሰጥቷል።

## ምዕራፍ ፫

## የጋብቻ ዓላማዎች

ጋብቻ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ እንደ መሆኑ መጠን እንደማናቸውም ምሥጢራት ሁሉ የራሱ የሆነ ዓላማ አለው። ዋና ዋና ዓላማዎቹ ሦስት ሲሆኑ እነርሱም:-

፩ ከባሕርይ ፍትወት ለመጠበቅ
፪ ለመረዳዳት እና
፫ የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ

### ፩ ከባሕርይ ፍትወት ለመጠበቅ

አንድ ሰው አካለ መጠን አድርሶ ጤናማ ሰውነት እስካለው ድረስ ተቃራኒ ጾታውን በማሰብ በምኞት መፈተኑ የማይቀር ነው። ነገር ግን በምኞት እየተቃጠሉ መፈተን አዳምና ሔዋን ከመሳሳታቸው በፊት በሰዎች ሰውነት ውስጥ አልነበረም። ይህን ማለት ግን አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ተስማምተውላቸው ይኖሩ ስለነበር በፍትወተ ሥጋ አይቃጠሉም ነበር ማለት ነው እንጂ መጋባትና ልጅ መውለድ አይችሉም ነበር ማለት አይደለም። አምላካችን እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን "ብዙ ተባዙ" በማለት በገነት እንዲኖሩ ማድረጉ አዳምና ሔዋን ከመሳሳታቸው በፊት እንኳን መጋባት እና መውለድ እንደሚችሉ ብቃታቸውን ሲያስረዳ ፤ ሳይተፋፈሩና በግብር ሳይተዋወቁ (ሳይገናኙ) ለሰባት ዓመታት ያህል በገነት ከኖሩ በኋላ በስህተታቸው ምክንያት ከገነት እንደተባረሩ ብዙም ሳይቆዩ በግብር መተዋወቃቸውና ልጆችን ለመውለድ መብቃታቸው



ደግሞ "አዳምና ሔዋን ከመሳሳታቸው በፊት በፍትወት አይፈተኑም ነበር።" በማለት ያስፈርነውን ሐሳብ ግልጽ ያደርገዋል። ዘፍ. ፪:፳፭ ፤ ፱:፩።

በተጨማሪም እግዚአብሔር የአዳም ዘር በእርሷ አማካይነት እንዲበዛና እንድትረዳው ሔዋንን ፈጥሮ ለአዳም ሲሰጠው 'የምትመቸውን ረዳት እንፍጠርለት' እና 'ብዙ ተባዙ' በማለት ሁለቱን የጋብቻ ዋና ዋና ዓላማዎች ብቻ መጥቀሱና ሌላኛውን ማለትም 'ከባሕርይ ፍትወት ለመጠበቅ' የሚለውን ሦስተኛ የጋብቻ ዓላማ አብሮ ከሁለቱ የጋብቻ ዓላማዎች ጋር በአራት አለመጥቀሱ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር አትብሉ ያላቸውን በመብላት ስሕተት ከመፈጸማቸው በፊት ሰውነታቸውን እንደረመጥ የሚፈጀው ፍትወተ ሥጋ እንዳልነበረባቸው ያሳያል።

ከፋም ይሁን ደግ ነገር አስቀድመን ሳንመኘው አንፈጽመውም። ሐዋርያው "ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች" በማለት የተናገረውም ዐቢይ ቃል ምንም ነገር ከመከናወኑ በፊት የሚቀድመው ምኞት መሆኑን ያስረዳል። አዳምና ሔዋንም እግዚአብሔርን ባስቀየሙት ጊዜ ከተግባራቸው ምኞታቸው ይቀድም እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ "ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት መልካም እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች።" ዘፍ. ፫:፮ ይላል። አዳምና ሔዋን በመመኘት ለሠሩት ኃጢአት ቅጣታቸው የተለያዩ ነገሮችን በመመኘትና በመጎምጀት መስቃየት ሆነ ከሚሰቃዩባቸው ምኞቶቻቸው አንዱ ፍትወተ ሥጋ ነው። በመጎምጀትና በመመኘት በተግባር ለፈጸምነው ኃጢአት በእግዚአብሔር የተፈረደብን ቅጣት ራሱ ምኞት ስለሆነ የሰው ልብ የማይጠቅመውን ከመመኘት ዕረፍት የለውም።

"አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደመሬት ትመለሳለህ" ዘፍ. ፫:፲፱ የተባለው የአዳም ሥጋ ከመሬት የተፈጠረ መሬታዊ (መሬት) ስለሆነ ነው። "ምድር (መሬት) እሾህንና አሜኬላን ታበቅልብሃለች።" ዘፍ. ፫:፲፰ ሲልም በጥፋታችን ምክንያት በአዳማዊ ልቡናችን የተፈጠረብንን ክፉ ክፉ ምኞትና ሐሳብ ለማመልከት ነው እንጂ በምድር ስለሚበቅሉ እሾህና አሜኬላ የተነገረ አይደለም። እሾህና አሜኬላ አዳም ሳይፈጠር የተፈጠሩ የማከሰኞ ዕለት ፍጥረታት ናቸውና። ነገር ግን "ምድር እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሃለች" ከሚለው የእርግማን ቃል የተነሣ "የሰው ልጅ ልብ ክፋትን ተሞላች። በሕይወቱም ሳለ እብደት በልቡ

እለ ልቡ መመኘትን ለመደ፣ ዓይኖቿንም አመንዝራነት ከደናቸው" መክ. ፴:፲፯ ፩ኛ ጴጥ. ፩:፲፪።

ምንም እንኳን በምኞት መፈተን በስሕተታችን ምክንያት የተፈረደብን ቅጣት መሆኑ ቢታወቅም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የክፉ ምኞት ምንጭ የሆነውን ሕሊናችንን ለማዳን ሲል የመልካም ሐሳብ ሁሉ መገኛ የሆነ ራሱን (ጭንቅላቱን) በአይሁድ እጅ በዘንግ እንደተቀጠቀጠና እርሱን ብቻ ማሰብ በራሳችን (በሕሊናችን) እንዲነግሥ የሰው ሁሉ ራስ የሚሆን አዳም በተቀበረበት የራስ ቅል በሚባል ስፍራ በቀራንዮ ላይ በመስቀል እንደነገሠ (እንደተሰቀለ) ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም።

ዳግመኛም ሴቶች በ፹ ወንዶች ደግሞ በ፵ ቀናችን ስንጠመቅ ባገኘነው የመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ኃይል ታግዘን ዘወትር ከክፉ ምኞት ጋር ልንታገል ያስፈልጋል። ቀን ጥሎን በኃጢአት በወደቅን ጊዜም ቶሎ ንስሐ በመግባት ታጥቀን መቆም ይገባናል እንጂ በጀመርነው ኃጢአት ጸንቶ መኖርና ተስፋ መቁረጥ ለክርስቲያኖች ተገቢ አይደለም። ምንም እንኳን ብዙ ድካም ቢጠይቅ በኃጢአታችን ምክንያት የመጣ የፍትወተ ሥጋ ፈተና በብዙ ገድል እና ጸንቶ ትሩፋት በመሥራት ሊወገድ ይችላል። ሰዎች ይህን መንፈሳዊ ምዕዳን(ምክር) ተቀብለውና በተግባር ፈጽመው በመገኘታቸው ምክንያት በማናቸውም ሁናቴና ጊዜ በፍትወት የማይፈተኑ ሲሆኑ የባሕርይ ፆር ጠፋላቸው ይባላል።

በምኞት መፈተን ከአዳምና ከሔዋን ስሕተት በኋላ የመጣ በመሆኑ በአዲስ ኪዳን የተነሣው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ "በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ" ፩ቆሮ ፯:፱። በማለት በአራት ያልተጠቀሰውን የጋብቻ ዓላማ እንደ ሦስተኛ የጋብቻ ዓላማ አድርጎ በመጥቀስ ስለዝሙት ጠንቅ በፍትወት ለሚቃጠል ሰው ጋብቻ ፍቱን መድኃኒት እንደሆነ አረጋግጧል። ስለዚህ ከጋብቻ ዓላማዎች አንዱ ከባሕርይ ፍትወት ለመጠበቅ የሚል ነው።

ብዙ ሰዎች ማመንዘር እንደማይገባቸው በሚነገራቸው ጊዜ "ምን እናድርግ ተፈጥሮ ሆኖብን ነው" ይላሉ። ነገር ግን አስቀድመን ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመጥቀስ እንደተረዳነው በዝሙት መፈተን ያልታዘዝነውን በመፈጸማችን ከአዳምና ሔዋን ስሕተት በኋላ የመጣ የራሳችን ፍዳ ነው እንጂ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ያሳደረብን አይደለም። የዝሙት ፈተና ከሰውነታችን ጋር አብሮ የተፈጠረ ቢሆን ኖሮ እንዴት እንደፈጠረን ስለሚያውቅ እግዚአብሔር አታመንዝር በማለት ከተፈጥሮአችን ጋር ፍጹም የሚፃረር ትዕዛዝ ባላዘዘንም ነበር። ዝሙት ተፈጥሮአዊ ላለመሆኑ ዘመናቸውን በሙሉ በድንግልና



የሚፈጽሙ ሰዎች ተጨማሪ መረጃዎች ናቸው። ምክንያቱም ዝሙት ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ይህን መፈጸም አይቻልም ነበርና። ስለዚህ ተራ ምክንያት በመፍጠር ራሳችንን ማስነፍ በመተው ለንጽሕና ታጥቀን መነሣት ይገባናል።

## ፪) ለመረዳዳት

የጋብቻ ሁለተኛ ዓላማ መረዳዳት ነው። ምንም ዓይነት እርዳታና ረዳት የማያስፈልገው ሁሉን በችሎታው የፈጠረ የሰማይና የምድር ንጉሥ ክርስቶስ ብቻ ነው። በተረፈ ግን ሰው ሁሉ ይነስም ይብዛ ረዳት ያስፈልገዋል። የባል ደግሞ ፍጹም የሆነች ረዳቱ ሚስት ናት። እግዚአብሔር በሥላሴነቱ "የምትመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" ዘፍ. ፪:፲፰ በማለት በአጥቂ ባሕርይው ለአዳም ረዳት እንደሚያስፈልገው ተረድቶ ሔዋንን ፈጥሮአታል። ረዳትነቷም ፍጹምና ምቹ ነው። እንደተቀጠቀጠ ሸንበቆ የማይመች ረጂ አለና ከዚያ ለመለየት ሲል 'የሚመቸውን ረዳት' በማለት ገለጻት። ሸንበቆን ቢመኩቱበት ያስጎዳል ቢመረኮዙበት እርሱም ይደቃል እጅንም ይወጋል ፤ ሔዋን ግን እንደሸንበቆ አይደለችም በአምላክ ቃል ምቹ ረድኤት ተብላለችና።

በተመሳሳይ ሁኔታ ለአዳም የሚያስፈልገው ርዳታ በሙሉ እንዲያውም በበለጠ መጠን ለሔዋንም ያስፈልጋታል። የአዳም ረዳት ሔዋን ናት የተባለው እርሷ መረዳት የሚያስፈልጋትን እርዳታ በሙሉ አዳምን በምትረዳበት መንገድ ስለምታገኘው ነው። ሚስት ለባል እርዳታ እንደተፈጠረች በተጻፈበት መጽሐፍ ቅዱስ ባልም ሚስቱን መርዳት እንዳለበት "እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ" ፩ኛ ጴጥ. ፫:፯ ተብሎ ተጽፏል። ሚስቶች መረዳት እንዳለባቸው ሲገልጽ 'ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ' በማለት የሚረዱበት ደካማ ጎን እንዳለባቸው ከገለጸ በኋላ ባሎች ደግሞ ሚስቶቻቸውን እንዲረዱ ሲያዝ "ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ" ብሏል። አብሮ መኖር በደከሙበት መንገድ ለመርዳት ነውና። ስለዚህ መረዳዳት የጋራ ነው እንጂ የአንድ ወገን ልዩ ተግባር አይደለም። ባልና ሚስት አንዱ ተረጂ ሌላው ረጂ አንዱ ተመጽዋች ሌላው ለጋሽ እንዳይደሉ መታወቅ አለበት።

አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን መርጦ ሲልካቸው ሁለት ሁለት አድርጓቸው እንደነበር "ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር" ማር. ፮:፯ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ከዚህ ቃል ጋር የሚስማማ ኃይለ ቃል በሌላም

ስፍራ "ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል፡፡ ቢወድቁም አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና፤ አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት ሁለቱም በአንድነት ቢተኙ ይሞቃቸዋል አንድ ብቻውን ግን እንዴት ይሞቀዋል? አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ ፤ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም፡፡" መክ. ፬:፱-፲፪ የሚል ተጽፎ እናገኛለን፡፡ የሰዎች ሁለትና ሦስት መሆንና እርስ በርሳቸው መረዳዳታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ እንዲህ የሚደነቅና የሚመሰገን ከሆነ ፍጹም የሆነው የባልና የሚስት መረዳዳት ምን ያህል ተወዳጅ ይሆን?

ይህንን ፍጹምና ተወዳጅ የሆነ የባልና የሚስት መረዳዳት በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ተገቢ ነው፡፡

፩ኛ አፍአዊ መረዳዳት

፪ኛ ውስጣዊ መረዳዳት

## ፪.፩ አፍአዊ መረዳዳት

አፍአዊ (ውጫዊ) መረዳዳት በኑሮ ውጣ ውረድ ምክንያት የሚፈጠርን ድካም ለማቃለል የሚያደርጉት መረዳዳት ነው፡፡ ለአንድ ሰው ኑሮ በቤት ውስጥ የሚሠራ ሥራ ማለትም ምግብን ማብሰል፣ በቤቱ ዙሪያ ያሉትን ነገሮች ንጽሕና መጠበቅ፣ ልጆችን ጠብቆና ተንከባክቦ ማሳደግ በአጠቃላይ ቤትን መምራትና ማስተዳደር በተጨማሪም ቤቱን የሚመራበት ወጪ ለማግኘት የሚያስችል ሥራ መሥራት የግድ ያስፈልጉታል፡፡ አንዱን ራሱ ሲሠራው ሌላኛውን ሥራ የሚሠራለት በማጣቱ እንዳይቸገር ሰው ረዳት መፈለጉ አይቀርም፡፡ አጋር የሌለው ሰው የራቀውን የሚያቀርብለት፣ የቀረበውን ደግሞ የሚያርቅለትና አንዱን ራሱ ሲሠራ ሁለተኛው የሚሠራለት አለመኖሩ ኑሮውን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይህን የኑሮ ውጣ ውረድ ለማቃለል በመለኮታዊ ኃይል የተዘጋጀ ፍቱን መድኃኒት ጋብቻ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለቆነጃጅትና ስለሚስቶች ሲናገር "በቤት የሚሠሩ፣ በጎዎች፣ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ" ቲቶ. ፪:፭ ይሁኑ በማለት የጻፈውን በመያዝ ሴት ልጅ ከቤት ውጪ የሚሠራ ሥራ መሥራት የለባትም በማለት ተገቢ ያልሆነ እምባ ጓሮ ለመፍጠር ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው እንደጊዜው ልማድ አብዛኛውን የቤት ውስጥ ሥራ የሚያከናውኑት ሴቶች በመሆናቸው አንዳንዶች "በወንጌል ማመን ሴቶች የቤት ውስጥ ሥራ አንሠራም እንዲሉ ነውን?" በማለት በወንጌል ላይ የተቃውሞ ምላሳቸውን



እንዳይዘረጉ ለማዳቸውን ሳይለውጥባቸው "በቤት የሚሠሩ" ይሁኑ አለ እንጂ ሴቶች እንደቢሮ ሥራ ባለ ማንኛውም የሥራ መስክ መሰማራት አይችሉም አላለም፡፡ በተጨማሪ ምንም እንኳ ሴቶች ማንኛውንም ሥራ የመሥራት መብት እንዳላቸው ቢታወቅም ቤትን መምራት እና ማስተዳደር ሰለችተው ቸል እንደይሉ "በቤት የሚሠሩ" ይሁኑ በማለት በቤት ውስጥም ድርሻቸውን ሳይዘነጉ ማከናወን እንዳለባቸው አመልክቷል፡፡ ፍትሐ ነገሥታችንም ይህን "ወኢትትሀከይ እምልእክተ ቤታ" "የቤቷን ሥራ ቸል አትበል" በማለት ያጸናልናል፡፡

ሥራን ሁሉ ይህ የሴት ነው ይህ ደግሞ የወንድ ነው ሳይሉ በመሥራት መተባበር ለዚህ ትውልድ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡ ቀድሞም ቢሆን በቅዱሳን አባቶቻችንና በቀሉ ተማሪዎች ዘንድ የወንድና የሴት ሥራ ተብሎ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ጥበብኛው ሲራክ "ከሚስቱም ጋር በሥራ የተባበረ ሰው የተደነቀ ነው፡፡" ሲራክ ፳፭:፩ እንዳለ ሁሉ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው በሥራ ሁሉ መደጋገፍ አለባቸው፡፡ ባል ሲያርስ፣ ሲቆፍርና ሲተክል ፤ ሚስት ስታርምና ስትነለቅል እርሱ ሲጽፍና ሲሥል እርሷ ምግቡን ስታበስል ፤ ሚስት ስትጋግር፣ ስታጥብና ስትፈትል እርሱ ወጧን ሲያማስል መኖር ይገባቸዋል፡፡ የጋብቻ ዓላማ መረዳዳት ነው ያስኘው አንዱ ይህ ነውና፡፡ ነገር ግን ዋናው የባልና የሚስቱ መስማማት ስለሆነ ሥራው ኃጢአት አይሁን እንጂ በፈቀዱት ዓይነት አሠራርና የሥራ መስክ ተመካክረው ከወሰኑ በኋላ በየፊናቸው መሰማራት ይችላሉ፡፡

አንድ ሰው ለጊዜው ምንም ዓይነት ረዳት እንደማያስፈልገውና በግሉ ያጋጠመውን ሁሉ ተጋፍቶ ማለፍ እንደሚችል ይሰማው ይሆናል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሐሳብ ግን በሽመግሉና በደዌ ተይዘው በአልጋ ላይ በዋሉ ጊዜ መድረሻ ያጣል፡፡ ስለዚህ ሰው ሁሉ በግድ ረዳት ያስፈልገዋል፡፡ በበሽታ ጊዜ ደግሞ ከማንኛውም ሰው እርዳታ የባል ወይም የሚስት እርዳታ እጅግ የሚሻል ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች የጋብቻ ዋና ዓላማ በዚህ መልክ መረዳዳት ከሆነ ሳናገባ በጸታ ከሚመስለን ማንኛውም ሰው ጋር ተረዳድተን ብንኖር አይቻልምን ? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ በርግጥ አንድ ዓይነት ጸታ ያላቸው ሰዎች ለጊዜው እርስ በርሳቸው በንብረት፣ በሐሳብ፣ በሥራና በጉልበት ሊረዳዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሰው ከዚህ ሌላ በስሜትም መረዳት የሚያስፈልገው ስለሆነ መረዳዳታቸው ጎዶሎ ከመሆኑም በላይ ከጊዜ በኋላ እድሜያቸው ሲገፋ አንድ አይነት ጸታ በመያዛቸው ምክንያት ራሳቸውን ማደስ (ልጅ መውለድ) ስለማይሆንላቸው በእርጅና ምክንያት መረዳዳታቸው ይቀርና ሁሉም ወደተረጂነት ዐዘቅት

ይወረወራሉ። ባልና ሚስት ግን በስሜት ለመረዳዳት ከመቻላቸውም ሌላ ምንም እንኳ ግርጅታቸው በአንድነት በተመሳሳይ ጊዜ ቢሆንም በሁሉም መንገድ ለመረዳዳት ወደው ስለተጋቡ በእርጅናቸው ጊዜ የሚረዳና የሚጦር ልጅ መውለዳቸው ራሱ መረዳዳት ነውና እንድ ዓይነት ጾታ ካላቸው ሁለት ሰዎች ይልቅ የባልና የሚስት መረዳዳት ፍጹም ነው።

### ፬.፪ ውሳጣዊ መረዳዳት

ውሳጣዊ መረዳዳት ባልና ሚስት በሐሳብ በስሜትና በመሳሰሉት በማይጨበጡና በማይዳሰሱ ነገሮች በረቀቀ መልኩ የሚረዳዱበት መንገድ ሲሆን ለተሻለ ግንዛቤ እንዲረዳን በአራት መንገድ ከፍለን እናየዋለን

፩ የሥነ ምግባር ለውጥ እንዲመጣ በማድርግ መረዳዳት
፪ በማንኛውም ጉዳይ በመመካከር መረዳዳት
፫ መጥፎና ክፉ ነገሮች እንዲረሱ በማድረግ መረዳዳት
፬ የፍትወተ ሥጋ ፈተናን በማቃለል መረዳዳት

#### ፬.፪.፩ የሥነ ምግባር ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ መረዳዳት

ሰዎች የተለያዩ ሰዎችን ይወዳሉ። እንደ ትዳር አጋራቸው ግን የሚወዱት ሰው የለም ሊኖርም አይገባም። ፍጹም ፍቅር ባለበት ደግሞ ቃልን መስማትና መታዘዝ አለ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ዮሐ. ፲፬:፲፭ በማለት የተናገረው ትእዛዝን መጠበቅ የሚገኘው በፍቅር ውስጥ ስለሆነ ነው። እንደዚሁም ሁሉ ባልና ሚስት በመካከላቸው ካለው ፍቅር የተነሣ እንዳቸው የአንዳቸውን ቃል ሰምተው ለመፈጸም ይገደዳሉ። ስለዚህ በብዙ መንገድ ሰምተው በቸልታ ያለፉትን መልካም ነገር እና መልካም ምክር በጉሮ አጋራቸው በተመከሩ ጊዜ ግን ለመፈጸም የሚጥሩ ስለሆነ በፍቅር የተደገፈ ትዳር ክፉውን በመሸሽ መልካሙን ነገር ደግሞ በመከታተል በቃል የማይገለፅ የሥነ ምግባር ለውጥ እንዲታይብን የሚጫወተው ሚና ወደር የለውም። ይህም በዋጋ የማይተመን ውሳጣዊ መረዳዳት ነው።

በተጓዳኝ ላይ ከፍተኛ የሥነ ምግባር ለውጥ ማምጣት የሚችል ረቂቅ ኃይል መፋቀር ሲሆን በአሉታዊ ገጽታው ተጠቅመውበት አፍቃሪያቸውን የሚጎዱ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። የተፈቀሩ ሰዎች የወደዳቸውን ሰው እንዲህ ያላደረግህ ወይም እንዲህ ያልሆንክ እንደሆነ አብረን መኖር አንችልም በማለታቸው ምክንያት አፍቃሪዎችም ስሜታቸውን በመከተል የወደዷቸውን ሰዎች ላለማጣት ብቻ ሲሉ እንደ ጠፍ ከብት በመነዳት ሃይማኖታቸውን እንኳን እስከ መካድ ደርሰው



በተለያዩ አንጉልና ጸያፍ ተግባራት ተመርዘው ቀርተዋል። ክርስቲያኖች ግን ቢወዱም ቢወደዱም በሃይማኖት መጽናትና በምግባር መጎልመስ ይጠበቅባቸዋል። ፍቅር ወደ መልካም ጎዳና ካልመራ ፍቅር አይባልም። ለዝሙት እና ለሌብነት የሚያስማማና እንደስሜት እርሱም ፈጥኖ የሚጠፋ የሥጋውያን ሥጋዊ ፍቅር አለና። ጠቢቡ ሰሎሞን "ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንአታቸውም በአንድነት ጠፍቷል" መክ. ፱:፮። በማለት የገለፀው የዚህ ዓይነቱን ሥጋዊ ፍቅር ነው። መንፈሳዊ ፍቅር ግን ጥላቻና ቅናት አይቀላቀለውም፤ የሚጠፋም ሳይሆን ዘወትር ጸንቶ የሚኖር ነው። "ፍቅር ግን ለዘወትር አይወድቅም" ተብሎ ተነግሮለታልና። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫:፰ እኛም ከላይ "በባልና በሚስት መካከል አስደናቂ የሥነ ምግባር ለውጥ ይፈጥራል" በማለት የገለጽነው ከሥጋዊ ፍቅር የተለየ የዚህ አይነት መንፈሳዊ ፍቅር በመሃከላቸው ያለ እንደሆነ ነው።

አንዲት ሴት የወደደችውን ወንድ ለማግኘትና ላለማጣት ስትል ምንም እንኳን እርሷ የምትወዳቸውን ነገሮች ቢሆኑ ያ የምትሻው ሰው እርሷ የምትወዳቸውን እነዚያን ነገሮች እንደማይወዳቸው ባወቀች ጊዜ ከእርሷ በማራቅ እርሱ በሚወደው መልኩ ራሷን ስታዘጋጅ መመልከታችን ምንም እንኳን ለማስመሰል የሚደረግበት ጊዜ ቢኖርም ከዚህ በመነሣት ግን ባሎች በሚወዷቸው ሚስቶች ላይ እስከ መጨረሻ የሚጸና መልካም የሥነምግባር ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ መገንዘብ እንችላለን። በዚህም የሚወደድ ባል ሕሊናን በመግዛት ልንተወው ያልቻልነውን መጥፎ ነገር እንኳን ለእርሱ ካለን ፍቅር የተነሣ ለውጥ አድርገን በመተው ጥሩ የሥነ ምግባር መሻሻል እንዲታይብን በፍቅር እንደሚያስገድደንና ውሳጣዊ እርዳታ እንደሚያደርግ ማወቅ ይቻላል ።

አንድ ሰው ክፉ ነገርን ለመተው እና ደግ ነገርን ለመሥራት ሕሊናውን የሚደግፍለት አይዞህ ባይ ያስፈልገዋል። የዚህ ዓይነት ድጋፍ ከሕክምና ባለ ሙያ፣ ከመጻሕፍትና ከትምህርት የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ ሁሉ ግን የሚበልጠው የትዳር ጓደኛ ድጋፍ ነው። ስለሆነም በብዙ ክፉ ልማዶች እና ሱሶች ተመርዘው የነበሩ ሰዎች በብዙ ምክር እና ወቀሳ ያልተውትን ክፉ ድርጊት ወደትዳር በገቡ ጊዜ በሚያስደንቅ ፍጥነት እርግፍ አድርጎ በመተው የሥነ ምግባር ለውጥ ያሳያሉ። ይህም ለባሎች የሥነ ምግባር መስተካከል ሚስቶች፤ ለሚስቶች ደግሞ ባሎች ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ያሳያል። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ስብከት የማይገዛቸው ክፉ ክፉ ባሎችን በሥነ ምግባር እንዲያገጡ የማድረግ ልዩ የተፈጥሮ ጸጋ ለሚስቶች እንደተሰጠ ሲገለጽ "እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ሆይ ከባሎቻችሁ አንዳንዶች ለትምህርት የማይገዙ ቢኖሩ

በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው” ፩ኛ ጴጥ. ፫፡፩-፪ በማለት ተናግሯል። አንድ ሰው ስለባል ወይም ስለሚስት ብሎ መልካም መንፈሳዊነትን ገንዘብ ቢያደርግ ስለ እግዚአብሔር ብሎ አላደረገውም እና ምን ይጠቅመዋል አይባልም። “ወይፈቅድ ምክንያተ ለድኂን” ለማዳን ምክንያት ይሻል ተብሎ ተጽፏልና እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ባልን፣ ሚስትን ወይም የፈቀደውን ነገር ምክንያት አድርጎ መጠቀም ይችላል። በሌላም ስፍራ በባል ወይም በሚስት ምክንያት ወደ መንፈሳዊነት መሳብ የዘለዓለም ሕይወት እስከ ማግኘት ድረስ የሚጠቅም ረቂቅ የድኅነት በር መሆኑን “አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚ እንደሆነ ምን ታውቂያለሽ? ወይስ አንተ ሰው ሚስትህን ታድን እንደሆነ ምን ታውቃለህ?” በማለት ሐዋርያው ጽፎልናል ፩ኛ ቆሮ. ፯፡፲፮።

## ፪.፪.፪ በሐሳብ በመመካከር መረዳዳት።

የመመካከርን መልካምነት ለመገለጽ “ተማክረው . . . አይሸትም” ተብሎ ይተረታል። መመካከር በምንም መልኩ ጠቃሚ ቢሆንም በተለይ በትዳር ውስጥ ያለው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ነው። ባልና ሚስት ትልቅ ትንሽ ሳይሉ በሚመለከታቸው ጉዳይ ሁሉ መመካከር ይጠበቅባቸዋል። ይህም በአንድ በኩል እርስ በእርስ መከባበራቸውን ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ ውጤታማ የሚያደርግና ፍቅራቸውን የሚያደራጅ ነው።

ከአንድ ሰው ሐሳብ የሁለት ሰው ሐሳብ ውጤታማ ነው። ባልና ሚስት ደግሞ ማንኛውንም ነገር ተመካክረው ቢሠሩት በየግል ከሚሠሩት ይልቅ ጸጸት የሌለው ስኬታማ ሆኖ ያገኙታል ። ይልቁንም ቀልጣፋ ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ነገሮች የተሻለውን መርጦና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወስኖ የመናገር ችሎታ ጎልቶ በሴቶች ላይ የሚታይ በመሆኑ ይህን ልዩ ስጦታ በትዳር ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ከባለቤታቸው ጋር በመወያየት ያለምንም ዳተኛነት በጥቅም ላይ ሊያውሉት ይገባል ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ባልና ሚስቶች ክፉና ደግ ነገሮችን በአንድ ልብ መክረው ሲፈጽሙ እናነባለን የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ያልተፈቀደላቸውን ዕፀ በለስ ቆርጠው ሲመገቡ በአንድ ልብ መክረው ነበር። ሄሮድስና ሄሮድያዳም ስለኃጢአታቸው ይገስፃቸው የነበረ ቅዱስ ዮሐንስን አንገቱን አስቆርጠው ሲያስገድሉ በፍጹም ልባቸው ተስማምተውና መክረው ነው። በድርሳነ ሚካኤል በተጻፈ ታሪክም እንደ ምናነበው ተላሶን የተባለ ብላቴናን ኅብታችንን



ይወርሰናል በሚል ስጋት እንዲሞት ብለው ወደ ባሕር የጣሉት ሁለት ኅብታም ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው ከተማከሩ በኋላ ነበር ።

በተጨማሪም ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ሁለት ባልና ሚስት የሐዋርያት ጉባኤ እንደሚፈታ (እንደሚበተን) በማሰብና የወደፊት ኑሯቸው ችግር ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት መሬታቸውን ከሸጡ በኋላ የሸጡበትን ዋጋ አካፍለው እኩሌታውን በመደበቅ እና ይህን ያህል ሸጥነው በማለት አታለው ከሐዋርያት ማኅበር ለመደመር ጥረት ባደረጉ ጊዜ ተመካክረው እንደነበረ ተጽፏል። ይህንንም ቅዱስ ጴጥሮስ “የጌታን መንፈስ ትፈትኑ ዘንድ ስለምን ተስማማችሁ?” የሐዋ. ፭፡፱ በማለት የተናገረው የተግሣጽ ቃል ግልጽ ያደርገዋል። እነዚህ ባለትዳሮች በአንድ ልብ መክረው መንፈስ ቅዱስን ለመቀሰጥ ስለሞከሩ ሁለቱም በሥጋቸው ተቀሥፈው በሰዓታት ልዩነት ተቀብረዋል። የሐዋ. ፭፡፩-፲፩። በባልና በሚስት መካከል መመካከር ተገቢ ቢሆንም ሕግ አፍርሶ ኃጢአት ለመሥራት፣ ሃይማኖት ለመካድ ፣ ለጥንቆላ እና ለመሳሰሉት ነገሮች በአንድ ሐሳብ መምከር ከላይ የጠቀስናቸው ሐናንያንና ሰጲራን ያገኘ መቅሠፍት አይሳተን በማለት ተያይዞ ኢላማ ውስጥ እንደ መግባት ነው።

ከባልና ከሚስት አንዳቸው በሰይጣን ተፈትነው የተንኮል ዕቃ ቢሆኑ እና ለሰይጣናዊ ሐሳብ ምንጭ ሆነው በእኩይ ነገር እንድንተባበራቸው ቢያማክሩን ምክራቸውን ፈጽሞ ልንቃወም ይገባናል። መጽሐፍ “ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና” ማቴ. ፭፡፴፭ የሚለውን ሲተረጎም ዓይን የተባለች ሚስት ናት ዓይን ሁሉን እንዲያዩበት በሚስትም ራስን ያዩባታልና፤ “ዓይንህ ብታሰናክልህ” ሲል ደግሞ ሚስትህ ሰው የሚጎዳበትንና እግዚአብሔር የሚያዝንበትን ሥራ እንሥራ ብትልህ ማለት ሲሆን “አውጥተህ ካንተ ጣላት” ማለትም እሺ አትበላት የሚስትህን ምክር ሰምተህ ከምትኮነን እምቢ ብለሃት ብትጸድቅ ይሻልሃልና ማለት ነው በማለት ከሁለት ባልና ሚስት አንዳቸው የማይገባ ሐሳብ ቢያስቡና ቢያማክሩ ሌላኛው ወገን መስማማት እንደማይገባው ምክር ይሰጣል።

በአንጻሩ ደግሞ መልካም መመካከር ለሚፈጽሟት ሰዎች መልካም ናትና እግዚአብሔርን በሚያሳዝን መልኩ ለነፍስና ለሥጋቸው ድኅነት የሚሆን ነገር የመከሩ ብዙዎች ናቸው ከእነርሱም ውስጥ አብርሃም አባታችን አንዱ ተጠቃሽ ነው። አብርሃም ከባለቤቱ ጋር በረኃብ ምክንያት ስደት በጀመረ ጊዜ ወደ ግብፅ አቅራቢያ እንደደረሱ በባለቤቱ ምክንያት እርሱን እንዳይገድሉት በመስጋት ከሣራ ጋር “አንቺ

በማለት ያን ሁሉ ስቃይ ለመርሳት ከሕፃን ልጇ በተጨማሪ ባሏም የራሱን ሚና እንደሚጫወት መጽሐፍ ሲገልጽ "በፀነስሽም ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛዋለሁ በጭንቀም ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደባልሽ ይሆናል" በማለት ሚስት ባልን መፈለጓ መውለድ ከሚያመጣባት ስቃይ በላይ በመሆኑ ፈጽማ መከራዋን ረስታ ዞራ ከባሏ ጋር አንድ መሆንን እንደምትፈልግ "ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል" የሚለው ዓረፍተ ነገር ያስረዳል። አግብቶ እና ተፋቅሮ መኖር እንኳን ይሆናሉ ተብለው የሚሰጋባቸውን ክፉ ክፉ ነገሮች ይቅርና ደርሰውብን የነበሩ ጉዳቶችን እንዳልደረሱብን እስከነሆን ድረስ የማስረሳት ኃይል አለው። ለዚህም መረጃ ከላይ የጠቀስነው ሴት ልጅ የደረሰባትን የወሊድ ጊዜ ሕማም በልጇና በባሏ ምክንያት መዘንጋቷ ነው። ለሕይወታችን የማያስፈልጉ መጥፎ ትዝታዎችን መርሳት ትልቅ ዕድል ነው። ይህ ደግሞ ያለ ምንም ጉዳት እና ስሕተት ወንዶች ከሴቶች ሴቶች ደግሞ ከወንዶች በጋብቻ የሚያገኙት ሲሆን በራሱ በዋጋ ሊተመን የማይችል ረቂቅ የሆነ ውሳጣዊ መረዳዳት ነው።

### ፩.፪.፬ ፍትወተ ሥጋን በማቃለል መረዳዳት

ከሰውነት ድካም የኀሊና ድካም ይከፋል የሰውን ልጅ ኅሊና በብርቱ የሚያደክመው ደግሞ ፍትወተ ሥጋ ሲሆን ከፍትወትም አንዱ ሩካቤ ሥጋ ነው። ማንኛውም ሰው ያለበትን የፍትወተ ሥጋ ፈተና ለማቃለል ሲል በእግዚአብሔር ዘንድ የማይወደድ የራሱን መንገድ ወይም ከጋብቻ ውጪ የሆነ ሩካቤ ሥጋ (ዝሙት) ቢፈጽም ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት የሚያመጣበትን ሥራ ሠራ ማለት ነው። ንጽሕ ጠብቆ ከሴት ርቄ መኖር አይቻለኝም የሚል ሰው በሚገባ መልኩ ጋብቻውን ፈጽሞ የምኞት ትኩሳቱን ማብረድ ይችላል። መጽሐፋችንም "በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉም ያግቡ" ፩ኛ ቆሮ. ፯:፱ ብሏልና። ይህም ባልና ሚስት የምኞት ሸክማቸውን በማቃለል የሚተጋገዙበት የውሳጣዊ መረዳዳት አንዱ ክፍል ነው። ከዚህም በተጨማሪ የጋብቻ ዓላማዎች በሚለው ዐቢይ ርእስ ውስጥ ቁጥር ፩ን ይመልከቱ

### ፪. የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ ለማድረግ

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከሌሎቹ ፍጥረታት በሙሉ አክብሮ እና አልቆ ከፈጠራቸው በኋላ ያሳደረባቸው የመጀመሪያ በረከት "ብዙ ተባዙ በማለት ልጅ እንዲወልዱ እና እንዲበዙ ሲሆን ይህም ከሦስቱ የጋብቻ ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ ነው። ይህ በረከት



ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ከጥፋት ውኃ ለተረፉ ለኖኅ እና ለቤተሰቦቹ ተሰጥቷል። ዘፍ. ፩:፳፰ ፤ ፱:፩ የሰው ልጅ በምድር ላይ መብዛቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በክፉ ሥራችን ምክንያት ሲቆጣንና ሲጣላን ደግሞ "ብዙ ተባዙ "በማለት የሰጠንን በረከት ይነሣንና በደዌ ፣በድንገተኛ አደጋ፣ በመቅሠፍት እና በተለያዩ መንገዶች ቁጥራችን እንዲቀንስ እና እንድንጠፋ ያደርጋል። እኛ ሰዎች ልጅ ላለመውለድ (ላለመብዛት) ብለን የምንቀይሰው ዘዴ እና የምንጥረው ጥረት ምናልባትም እግዚአብሔር እኛን የመጣላቱ እና የቁጣው ምልክት ሊሆን ይችላል በማለት መስጋት ብልህነት ነው።

የሰውን መብዛት የማይፈልግ ሰው የእግዚአብሔርን መልካም ፈቃድ የሚቃወም እና የመልካም ነገር ጠላት የሰይጣን ባልንጀራ ነው። ነብዩ ሚልክያስ "እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታል" ሚል. ፪:፲፭ በማለት እግዚአብሔር ከሰዎች የሚፈልገው በመንፈሳዊ ሥርዐት በሕግ ተጋብተው መብዛታቸውን መሆኑን በግልጽ ነግሮናል። በተጨማሪም "በጋብቻ የሚፈጸም የተቀደሰ ሩካቤና የእግዚአብሔር ፈቃድ" በሚለው ርእስ ውስጥ የመጨረሻዎቹን ሦስት አንቀፆች ወደፊት ተመልከት።

## ምዕራፍ ፬

## እርግዝናንና ወሊድን መከላከል በተዋሕዶ ሃይማኖት እንዴት ይታያል ?

ተምረው በተማሩት ትምህርት አለመጠቀም፣ ተሹሞ አለማገልገልና አግብቶ አለመውለድ አንድ ናቸው። ከጋብቻ ሦስት ዋናዋና ዓላማዎች አንዱ ዘር መተካት በመሆኑ ወደ ትዳር ዓለም የሚገባ ማንኛውም ሰው ይህን አውቆ ማግባት አለበት። መውለድን የማይፈልግ ሰው አለማግባት ይጠበቅበታል፤ ጋብቻ ፈቃድ ያለው ዝሙት አይደለምና ። ላይነግዱና ላያተርፉ መክሊትን ተቀብሎ መቅበር እጅ እና እግርን አሳስሮ ለቅሶና ዋይታ ጥርስ ማፏጨትም ወዳለበት ወደገሃነም እሳት ያስጥላል። ማቴ. ፳፭:፳፬-፴ ይህን ማለት ግን ያገባ ያለ ምንም ገደብ በግድ መውለድ ይገባዋል ማለት አይደለም። አንድ ሰው የፈቀደውን ያህል ልጅ ከወለደ እና ራሴንም መግዛት እችላለሁ ካለ በንጽሕና ሆኖ ባይወልድ አይገደድም። በተጨማሪም የተጋቡ ሰዎች ባይወልዱ ቢቀሩ ኃጢአት ሠርተዋል ማለት አይደለም። ተጋብተው

ያልወለዱ ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው ማለት በምናኔ (በምንኩስና)፣ በመካንነት ወይም በሌላ ምክንያት ያለልጅ የሚኖሩ ሰዎች በደለኞች ናቸው ያሰኛል።

ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና ሰው እርሱ በፈቀደው ጊዜ ልጅ ላያገኝ ይችላል፡ መካንን ብዙ ልጆች እንድትወልድ የሚያደርጋትና ብዙ የወለደችውንም የሚያደክማት ወይም ልጅ አልባ የሚያደርጋት ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው እንጂ ጊዜ አይደለም፡ ልጅ በማጣት (በመካንነት) ጥቂት ጊዜ ተንገላተን ቢሆን ኖሮ "ልጅ ላለመውለድ የሚደረግ የወሊድ መቆጣጠሪያ አትጠቀሙ" የሚል ስብከት ባላስፈለገንም ነበር።

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ነቢዩ ዳዊት "እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፡ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።" መዝ. ፩፻፳፯:፫ በማለት ተናግሯል። የሰው ልጅ ግን የእግዚአብሔርን ብርቅ ስጦታ እንደ ኢምንት በመቁጠር ላለመቀበል እጁን ሲያጥፍ ይታያል፡ ማንም ቢሆን ያፈቀረውንና እርሱም የሚያፈቅረውን ሰው ስጦታ ላለመቀበል እጁን አይሰበስብም፡ እንዲያውም ወዳጁ የታጠፈ እጁን ዘርግቶ ስጦታ እንዲያበረክትለት በሥራና በቃል አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡ እኛም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር መልካም ልጅ እንዲሰጠን በእጃችን መልካም በመሥራት በቃላችን ደግሞ ፈጣሪያችንን በመለመን ደጅ መጥናት ይገባናል እንጂ ላለመውለድ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀምና የፍቅር ስጦታውን ረግጦ የጥላቻ መልስ መመለስ አይገባንም።

ልጆች ምንም እንኳን በእግዚአብሔርና በእኛ ዘንድ የሚወደዱ ቢሆኑም እርሱ በፈቀደ ጊዜ በተለያየ ምክንያት መውለድ የማንችል (መካን) ሊያደርገን ይችላልና ሳናጉረመርም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል ይገባናል፡ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው እንደሚገኙ ብዙ ሰዎች ልጅ ፍለጋ ከትዳራችን በመውጣት ዝሙት መፈጸም አይገባም፡ በባል ወይም በሚስት ወይም በሁለቱም መካን ሊኖር ስለሚችል እርስ በርስ መነታቀፍም ተገቢ አይደለም፡ ከባልና ከሚስት በአንዳቸው መካን ቢኖርና የመከነው ማን እንደሆነ ቢታወቅ እንኳ እስከ እስከሳመጣው ድረስ ጥላቻ ከማሳየት በተገቢ ሁኔታ ማጽናናት ሙሉ ክርስቲያንነት ነው፡ ደግሞም በመካንነት ችግር መፋታትና መጣላት እንደማይቻል በቤተክርስቲያን ተገኝተው ተጋቢዎች በመሐላ የሚገቡት ቃል ኪዳን መረጃ ነው፡ ባሎቻችንም ሆኑ ሚስቶቻችን ቢመክኑ እንደእኛ ሰዎች ናቸው እንጂ ልጅ በነሣቸው በእግዚአብሔር ቦታ አይሉምና እንኳንስ በእነርሱ ይቅርና በፈቃዱ ለጊዜው ልጅ ባሳጣን



በእግዚአብሔር ላይም መቆጣት ተገቢ አይደለም፡ ደግሞም ከልጆች ይልቅ ትዳራችን ይቀድማልና ከልጅ ይልቅ ለትዳራችን የበለጠ ክብር ልንሰጥ ይገባናል፡ ከቤት ስንወጣና ስንገባ በማልቀስ፣ በመበሳጨት፣ በመማረር፣ እህል አልቀምስም በማለትና ያልተለመደ አዲስ ዐመል በማሳየት ትዳርን ሰላም ማሳጣት ተገቢ ካለመሆኑም በላይ በሁለት መንገድ ራስን መጉዳት ነው፡ እናታችን ሐና ባሏን እንዲህ ታማርረው ነበር፡ ባሏ ሕልቃናም "ሐና ሆይ ለምን ታለቅሻለሽ? ለምንስ አትቀምሺም? ለምንስ ልብሽ ያዝንብሻል? እኔስ ከአሥር ልጆች አልሻልልሽምን?" ፩ኛ ሳሙ. ፩:፰ በማለት በፍቅር ሚስቱን ሲያጽናናት እንመለከታለን፡ እግዚአብሔርም ፍቅራቸውን ተመልክቶና የሐናን ጸሎት ሰምቶ ታላቁን ነቢይ ሳሙኤልን ሰጥቷቸዋል።

ለሌሎች መንፈሳዊ የጋብቻ ዓላማዎች ግድ ሳይኖረው ለፍትወት ብቻ ብሎ ወደትዳር የሚገባ ሰው እንዳለ ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ሲል ይተርካል፡ "ከእርሱ ወገን ስለተነገረች የዝሙት ጣዕም ብቻ ጋብቻን የሚሻት አለ፡ ከእርሷም በቀር ሌላን አያስብም ልጅን ወደማግኘትና ወደመረዳዳትም አይመለከትም ፤ በራሱ በኩልም ቢሆን ወይም በሚስቱ በኩል ጽንስንና መጽነስን ከሚከለክል ወገን የሚያደርግም አለ፡ ጣዕመ ፍትወትን በመመልከትና ለሩካቤ ሥራ ብቻ በእርሷ ተቋጥሮ የሚኖርም አለ፡ ፍትሐ. መን. አንቀጽ ፳፬:፲፪፩፪ ስለዚህ ለተጋቡ ሰዎችም ቢሆን በተለያየ መልኩ ወሊድን በመቆጣጠር መረን በተለቀቀ ዝሙት መኖር የክርስቲያኖች ሕግ ይከለክላል።

ቅዱስ ዳዊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ የዘር ሐረግ ሰው እንደሚሆን ያውቅ ስለነበር የጌታ እናት ድንግል ማርያም ምናልባት ከኔ ትወለድ ይሆናል በማለት ብዙ ሚስቶችን አግብቶ እንደነበር ሁሉ ብዙ ሴቶች ልጆች ያሏቸው ባለ ትዳሮችም ወንድ ልጅ ፍለጋ ብዙ ልጆች ቢወልዱ የጥሁነት በሚመስል ጥኝነት ራሳቸውን ለብዙ ድካም እያዉት መሆኑን ሊያውቁት ይገባቸዋል፡ ብዙ ልጆችን ወልዶ ማሳደግ ብዙ ድካም ይጠይቃል፡ በክርስትና ሃይማኖት ካገቡ በኋላ በተለያየ መንገድ ላለመውለድ የሚደረግ ጥረት የሚነቀፈው ብዙ እንውለድ እና ከሞት የተረፉት ይበቁናል ወይም በዕድላቸው ያድጋሉ እያልን ካትማችን በላይ ብዙ ልጆች እንድንወልድ ሳይሆን ራሳችንን መግዛት እንዳለብን ለማስገንዘብ መሆኑ መታወቅ አለበት፡ ስለዚህ ልጅ መውለድ የማይችሉ (መካኖች) ልጅ ለማሳደግ ከሚፈጠር ውጥረትና ድካም ነፃ ነንና በማለት እንደ ሰግና ፍትወት ማብዛት የለባቸውም።

በትዳር ውስጥ ልጅን ስለመውለድ እና ስለ አለመውለድ ሁለት መንገዶች ብቻ ይገኛሉ ከእነርሱም ውስጥ ፩ኛው ፈቃድን ፈጽሞ ልጅን

## በጋብቻ የሚፈጸም የተቀደሰ ሩካቤና የእግዚአብሔር ፈቃድ።

ሩካቤ የተቀደሰ የሚሆነው በባልና በሚስት መካከል ሲፈጸምና እነርሱም ቢሆኑ በተገቢ ሥርዓት ሲፈጽሙት ብቻ ነው። እግዚአብሔር የፈቀደው ሥርዓት የጠበቀውን የባልና የሚስት ግንኙነት ብቻ ነው እንጂ ዝሙትንና ሴሰኝነትን አይደለም።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር የጾታ መለያ የሆነ ንዑስ መሊሊት (ኃፍረተ አካል) ፈጥሮ የሰጠን ተገቢውን ተግባር እንድናከናውንበት ነው እንጂ ጌጥ ይሁናቸው ብሎ አይደለም። ለጌጥ ፈጥሮት ቢሆን ኖሮ እንደ አፍንጫና አፍ በግልጽ በሚታይ ቦታ ማኖር ለእግዚአብሔር ባልቸገረውም ነበር። ዳግመኛ ለወንድም ሆነ ለሴት ከልብስ ተራቁቶና ተገላልጦ መታየት መነቀፍ ባልተገባው ነበር። ነገር ግን የሰው ሁሉ ከልብስ ተራቁቶ መኖርና ተገላልጦ መታየት በእግዚአብሔር ዘንድ መነቀፉ ኃፍረተ አካል ለጌጥ እንዳልተፈጠረ እና የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ (ሙያ) እንዳለው ያሳያል። የዓይን ድርሻ ማየት የጆሮ ድርሻ ደግሞ መስማት እንደሆነና ይህንንም ተግባራቸው በሚገባ መልኩ ማከናወናቸው ኃጢአት እንደማይሆንባቸው ኃፍረተ አካልም በሚገባ መልኩ የሥራ ድርሻው የሆነ ሩካቤን መፈጸሙ ኃጢአት አይሆንበትም። እግዚአብሔር ሲፈጥረው ለዚህ ተግባር አስቦት ነውና እግዚአብሔር የራሱ ሙያ ያለው ኃፍረተ አካልን በመፍጠሩ ብቻ እንኳን በባልና በሚስት መካከል የሚፈጸም የተቀደሰ ሩካቤን የፈቀደ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ዳግመኛም ሐዋርያው "ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና ፤ ከዝሙት እንድትርቁ "በማለት ፈጣሪያችን የኛን ንጽሕና ቅዱስ መሆን እንደሚፈልግ ገልጦ በመቀጠልም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ዕቃ (ኃፍረተ አካሉን) ከዝሙት ጠብቆ ቢኖር እግዚአብሔር በንጽሕና የተጠበቀች (ክብረ ድንግልና) ያላትን ልጃገረድ እንደሚያዘጋጅለትና እንዲጋቡ እንደሚያደርጋቸው ነገር ግን እግዚአብሔር መልካም ትዳር የሚሰጠው እንደ አሕዛብ ሰውየው በፍትወተ ሥጋው በዘፈቀደ እንዲኖር ሳይሆን በክርስቲያን ሕግና ሥርዓት እንዲኖር እንደሆነ ሲገልጽ "እግዚአብሔርን እንደማያውቁ እንደ አሕዛብ አይደለም እንጂ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ (ኃፍረተ አካሉን) በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ ፤ … " ፩ተሰ. ፬:፫-፭ ብሏል። ይህም ከአሕዛብ በተለየ መልኩ በክርስቲያናዊ ሕግና ሥርዓት ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቅዱስ የሆነ ሩካቤአችንን እንደማይጠላብን ያሳያል።



በተጨማሪም "ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ "ዘፍ. ፪:፳፬ ፤ ማቴ. ፲፱:፭ በማለት አምላካችን የተናገረው ባልና ሚስትን የሚመለከት ቃል የሚፈጸመው በሩካቤ ነው። ምክንያቱም "አንድ ሥጋ" የሚለው ቃል እራሱ የሚያመለክተው የሥጋ አንድነትን ከመሆኑ በላይ የባልና ሚስት አካል በሩካቤ ተዋሕዶ የሚያስገኘው አንድ አካል ያለው ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን ነው። ሩካቤ ሥጋ እንኳን ሕጋዊ ተጋቢዎች ፈጽመውት ይቅርና ከትዳር ውጪም በኃጢአተኝነት ቢፈጸም እንንጎዳበታለን እንጂ የሥጋ አንድነትን መፍጠር ይችላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያብራራ "ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንደሚሆን አታውቁምን አንድ ሥጋ ይሆናሉ" ተብሏልና። ፩ቆሮ. ፮:፲፮ በማለት ጽፎልናል። ስለዚህ ሕጋዊነት ላላቸው ባልና ሚስት ለአዳምና ለሔዋን "ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" በማለት የተናገረው እግዚአብሔር ስለሆነና ይህ የሥጋ አንድነታቸው የሚፈጸመው ደግሞ በሩካቤ መሆኑን ሐዋርያው ከላይ ባስፈርነው ጥቅስ ስላረጋገጠልን እግዚአብሔር በትዳር ውስጥ የሚፈጸም በንጽሕና ያጌጠ ሩካቤን መፍቀዱ እሙን ነው።

ማንኛውም ቤተሰብ ያለው ሰው ቤተሰቡን የመመገብና የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት። "ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።" ፩ኛ ጢሞ. ፭:፰ ተብሏልና። እንኳን የቤተሰብ አውራ የሆነ ባል ይቅርና ልጆች እንኳን እንዳቅማቸው ቤተሰቦቻቸውን የመርዳት ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን ቅዱስ ጳውሎስ "ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሯት እነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔርን መምሰል ያሳዩ ዘንድ ይማሩ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ መልካምና የተወደደ ነውና" ፩ኛ ጢሞ. ፭:፬ በማለት ጽፎልናል። ስለሆነም ባል ለልጆቹና ለሚስቱ ትልቅ ኃላፊነት ያለበት የቤተሰብ ራስ ነው። ሚስት ደግሞ ከቤተሰብ አባልነቷ ሌላ የማይመረመር ምሥጢር ለባል የገዛ አካሉ ሆናለች። ባል ቤተሰቡ፣ አካሉ ለሆነችና የገዛ ሥጋውን ለምትመስል ለሚስቱ ሊያደርግላት የሚገባውንና ያለበትን ኃላፊነት ሲገልጽ ሐዋርያው እንዲህ ብሏል "እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደገዛ ሥጋቸው አድርገው ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና። ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል ይንከባከበውማል ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም

ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" ኤፌ. ፭፥፳፰-፴፩ ሐዋርያው በዚህ ምንባብ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ሥጋውንና ደሙን እንደመገባትና እንደተንከባከባት ባል ራሱ ደግሞ የገዛ ሥጋውን እየተንከባከበ እንደሚመግብ እንዲሁም ሚስቱን ይንከባከካት፣ ይመግባት በማለት ትዕዛዝ አስተላልፏል። "ይመግባት" የሚለውን ቃል የትርጓሜ መጽሐፋችን ሲያትተው ወጥቶ ወርዶ ያገኘውን ያካፍላት፣ ያብላት፣ ያጠጣት ማለት ብቻ ሳይሆን "ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት" ፩ኛ ቆሮ. ፯:፫ የሚለውን ትዕዛዝ ተቀብሎ ተገቢውን ሁሉ ያድርግላት ማለትም ፈቃደ ሥጋዋን በሩካቤ ይፈጽምላት ማለት እንደሆነ ይገልጻል። በዚህ ጽሑፍ "ይመግባት" በማለት እግዚአብሔር ባል የሚስቱን ፈቃደ ሥጋ እንዲፈጽም ማዘዙ ሩካቤን የፈቀደ እርሱ መሆኑን ያስረዳል።

ከጋብቻ ሦስት ዓላማዎች አንዱ በመዋለድ የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ መሆኑ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ይህንንም በረከት እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ግዟትም" ዘፍ. ፩:፳፰ በማለት እንደሰጣቸው እናነባለን። ከዚህም በኋላ ሰዎች በምድር ላይ በበዙ ጊዜ ምድር በግልሙትናዋ ምክንያት የተጠላች ሆነችና እግዚአብሔር በንፍር ውኃ (ማየ አይኅ) ፈርዶ እንድትጠፋ አደረጋት። ከጥፋቱም የተረፉት ኖኅና ቤተሰቦቹ እነርሱም ከተዋለዱና ከበዙ በኋላ ኃጢአት ቢሠሩ ተመሳሳይ ቅጣት እንደሚያገኛቸው አስቦ ኖኅ ስለስጋ መሥዋዕት ሰውቶ እግዚአብሔርን ተማጸነ እግዚአብሔርም መሥዋዕቱን ተቀብሎ ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋት ቃልኪዳን ገባለት። በመስጋትም ከመውለድና ከመብዛት ወደኋላ እንዳይሉ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም " ዘፍ. ፱:፩ በማለት በአዳምና በሔዋን በረከት እግዚአብሔር ዳግመኛ ኖኅንና ቤተሰቦቹን ባረካቸው። ይህ በረከት በሌላ ስፍራ ረዥም ጊዜ ቆይቶ ለያዕቆብ ሲሰጥ እንመለከታለን። "እግዚአብሔርም አለው ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ ብዛ ተባዛ" ዘፍ. ፴፭:፲፩ ይህን የእግዚአብሔር በረከት ያዕቆብና ልጆቹ ስለፈጸሙት "የእስራኤል (ያዕቆብ) ልጆች አፈሩ እጅግም በዙ ተባዙም እጅግም ጸኑ ምድራቱም በእነርሱ ተሞላች።" ዘጸ. ፩:፯ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይዘግብልናል። እስራኤላዊያን የበዙት ከእግዚአብሔር ለበረከት በተሰጠ መልካም ሩካቤ ነው እንጂ በሌላ መንገድ አይደለም።

አፍአዊ (ውጫዊ) መራባት በጥቂት ነፍሳትና እንስሳት የሚታይ እንጂ ለሰው በተፈጥሮ የተሰጠ ጸጋ አይደለም። ምንም እንኳ በዘመናዊ



ዘዴ ያለሩካቤ የሚፈጠር የጋንና የብልቃጥ ፅንስ እንዳለ ቢታወቅም በክርስቲያኖች ዘንድ ግን ይህ የተነወረ ተግባር ነው። እግዚአብሔር የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ የፈቀደው በመልካም ሩካቤ ብቻ ነው እንጂ በሌሎች ሰው ሠራሽ መንገዶች አይደለም። ይህንንም ከሚከተለው ዐረፍተ ነገር መረዳት ይቻላል። ዛሬ በዓለማችን የሚገኙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ የሰው ልጆች በሙሉ የሩካቤ ውጤቶች ናቸው። ስለዚህ በተቀደሰ ጋብቻ የሚደረግ ሩካቤ የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ ከፈጣሪ ዘንድ በቡራኬ እንደተሰጠን እናስተውል።

ከላይ "ብዙ ተባዙ" በሚል ዓረፍተ ነገር የተገለጹት አራት የበረከት ጥቅሶች እግዚአብሔር በምድር ላይ መብዛታችንን እንደፈቀደ የሚያሳዩ ብቻ አይደሉም። ያ ቢሆን ኖሮ "ብዙ" የሚለው ቃል ብቻ በቂ በሆነ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር በቃሉ 'ብዙ' ካለና ካዘዘ እንኳንስ አስቦ መሥራት የሚችል የሰው ልጅ ይቅርና ግዕዛን የሌላቸው አፈርና እንጨት፣ ውኃ እና እሳትም ይበዛሉና። ነገር ግን እግዚአብሔር ብዙ በሚለው ቃል ላይ 'ተባዙ' የሚል ቃል ጨምሮ መናገሩ ባልና ሚስት በአንድነት ሆነው ለመውለድና ለመብዛት የሚፈጽሙት ተግባር እንዳለ ለማመልከት ነው። ይኸውም በጋብቻ የሚፈጸም የተቀደሰ ሩካቤ ነው። በዚህም ማለትም "ተባዙ" በሚለው ቃል መሠረት ባልና ሚስት ሩካቤ እንዲፈጽሙ የፈቀደና ያዘዘ እግዚአብሔር መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል።

## የባልና የሚስት አለመፈታታድ

በብዙ ባለትዳሮች መካከል ብዙ የሐሳብና የፈቃድ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። በትዳር መካከል የሚገኝ ማንኛውም ልዩነት የማይናቅ ቢሆንም ከሁሉም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ግን ባልና ሚስትን መኝታ እንዲለዩ የሚያደርጋቸው ችግር ነው። ይህ እንደ ነፍስና ሥጋ መለያየት ትዳርን ምውት የሚያደርግ ነውና።

ሁለት ባለትዳሮች በመኝታ እንዳይስማሙ የሚያደርጉዋቸው ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም አንኳር ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት ግን የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ) የትዳር ምሰሶ ፍቅር ቢሆንም የፍቅር ዓይነቱ ብዙ ስለሆነ ባልና ሚስት ከመጋባታቸው በፊት መፋቀራቸውን ብቻ ሳይሆን በምን መልኩ እንደተፋቀሩ ማወቅ አለባቸው። ምክንያቱም በወንድምና በእኅት መካከልም ፍቅር አለና። ነገር ግን በመሀከላቸው ሩካቤ የለም። ስለሆነም በዚህ መልኩ የተዋደዱ ሰዎች በምን መልኩ እንደተፋቀሩ ሳይመረምሩ ወደ ጋብቻ ቢያመሩ ሰውነታቸው ተነሣሥቶ ሩካቤን ለመፈጸም ይቸገራሉ። ምክንያቱም የዝምድናና የቤተሰባዊነት ፍቅር ወደ ሩካቤ

የሚሠሩትን እንዳልወደድነውና ኃጢአትም እንደሆነ በግልጽ ልናስረዳቸው ይገባል።

ረ) አብሮ ከመኖር የተነሣ የሐሳብ ልዩነቶችና መጠነኛ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ማንም አይስተም ፡፡ ይህ አይነቱ እድል በባለ ትዳሮችም መሃል ይገጥማል ምክንያቱም እንኳን ከሁለት የተለያየ ቦታ ተገኝተው የተጋቡ ባልና ሚስት ይቅርና በአንድ አንጓል የሚመሩ ሁለት እግሮቻችንም የሚጋጩበት ጊዜ አለና ፡፡ አባቶቻችንም ሲተርቱ "ጉልቻና ጉልቻ እንኳን ይጋጫሉ"የሚሉት ለዚህ ነው ታዲያ ይህን አይነት አለመግባባት ሲገጥመን ምንም አይነት መቋጫ ሳናበጅለት በቀጥታ ወደ ፍቺ መሄድ የራሱ የሆነ ጎጂ ገጽታ ቢኖረውም የተፈጠረውን መለስተኛ አለመግባባት ምክንያት በማድረግ የትዳር ግዴታ የሆነውን ሩካቤን መከልከል ግን ጥፋት ያዩበትን ሰው እንዲታረም በማለት በእሳት እንደመግረፍ ነው። ይህ ደግሞ ለትዳር ዘለቄታዊ ሰላም አደገኛ እርምጃ ነው። ስለዚህ በባልና ሚስት መሃከል የሚፈጠር ማንኛውም ግጭት ውሎ ሳያድር መፍትሄ ማግኘት አለበት። ሐዋርያው "ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ለዲያቢሎስም ፈንታ አትስጡት " ይላልና ኤፌ. ፬:፳፮-፳፯ ፤ ያዕ. ፩:፳።

አንዳንድ ጊዜ ምንም እንኳን ደስ ያላለን ብንሆን ስለባለቤቶቻችን ብለን ልንፈጽማቸው የሚገቡን ብዙ ነገሮች እንዳሉ ማወቅና ከእኛ ተድላና ደስታ ይልቅ የእነርሱን ስሜት በመጠበቅ ለባለቤቶቻችን ያለንን ፍቅር ማሳየት ይጠበቅብናል። "ፍቅር ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝምና።" ፩ቆሮ. ፲፫:፭ በፈቃደ ሥጋ የተንገበገበ አካላችን (ባለቤታችን) እንደውኃ ጉድጓድ ሲናፍቀን ረግጠነው ብናልፍ አንድን ድሃ በውኃ ጥም ሲሞት እያዩ ጥርኝ ውኃ ላለመስጠት እንደመጨከን ይቆጠርብናል።

ሰ) ከፍተኛ የሆነ የዕድሜ ልዩነት በሩካቤ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው አስቀድመን ገልጸናል። የባልና የሚስት የዕድሜ ልዩነት ከልክ በላይ መሆን በፈቃደ ሥጋችን ላይም ከልክ ያለፈ ልዩነት እንዲኖር ያደረጋል። ይህ እውነተኛ የዕድሜ ልዩነት ሲኖር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በባልና በሚስት መካከል እውነተኛ የሆነ ከፍተኛ የዕድሜ ልዩነት ባይኖርም በባል ላይ በጣም ልጅ ሳይሆን ልጅ፣ በጣምም ሽማግሌ ሳይሆን ሽማግሌ እንደዚሁም ደግሞ ሚስትን ጁጁ (አሮጊት) ሳትሆን አሮጊት የሚያስመስሏት ምልክቶችና ድርጊቶች ዘወትር የሚታዩባቸው ከሆነ ምንም እንኳ እውነተኛ የዕድሜ ልዩነት ባይኖርም በመካከላቸው ከፍተኛ የዕድሜ ልዩነት እንዳላቸው እንዲያምኑ የሚያደረጋቸው የሥነ



ልቦና ችግር ስለሚፈጠርባቸው በሩካቤ ጊዜ ሊስማሙ የማይችሉበት ሁኔታ ሊከሠት ይችላል።

ሸ) አንዳንድ ጊዜ የአስተዳደግ ዓይነትና ጎጂ ልማዶች የሰውን ልጅ ስሜት በብርቱ ሊጎዱት ይችላሉ። ለምሳሌ፡- ሴቶች ልጆች በበዙበት ቤት በማደግና ከብዙ ሴቶች ጋር ተቀራርቦ በመኖር የምንወርሳቸው ጠባያት ወደ ትዳር ከገባን በኋላ በብዙ መንገድ እነርሱን እንድንመስልና በሚስቶቻችንም የማንፈልግ እስከንሆን ድረስ ተጽእኖ ሊያሳድሩብን ይችላሉ። ሴቶች ሴቶችን አያገቡምና በባላቸው ላይ የወንድነት መገለጫዎች ናቸው የሚባሉ ነገሮች በሙሉ እንዲታዩበት ይፈልጋሉ። በተመሳሳይ መልኩ ሴቶቹም ወንዳገረድ መሆናቸው በባላቸው ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው። ምክንያቱም ማንኛውም ወንድ ወንድን አያገባምና ሚስቱ በማንኛውም መንገድ ሴትነትን ይዛ እንድትገኝለት ይፈልጋል። ሆኖም የቤት በተለያዩ ድርጊቶች ወንድን ለመምሰል መሞከር ወንድም ሴትን ለመምሰል መሞከሩ ሲጀምሩት ተራ ቀልድ ይመስላል ውሎ አድሮ የሚያሳድረው ተጽእኖ ግን ከአሸዋ ሽክም ይጸናል። ስለዚህ ወንድ ወንድነቱን ሴትም ሴትነቷን ጠብቀው ቢኖሩ ከዚህ ጫና ነፃ ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስ "ሴት ልጅ የወንድን ልብስ አትልበስ" ዘዳ. ፳፪:፭ ማለትም ሴት ልጅ በማንኛውም መንገድ የወንድን ባሕርይ ልባበስ አትበል በማለት ትዕዛዙን ያስፈረልን ከእንደዚህ ዓይነቱ ችግር እንድንድን ለማድረግ ነው።

ቀ) አምኖን በትእግርት ላይ እንዳደረገው አስገድዶ መድፈርና ሕፃናትን አፍኖ በመውሰድ ለልዩ ልዩ አደጋዎች ማጋለጥ የዘመናችን ትልቅ ችግር እየሆነ መጥቷል። ፪ሳሙ. ፲፫:፲፬ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለውድ በግድ ሩካቤ እንዲፈጽሙ የተገደዱ ሰዎች ትልቅ የሥነ ልቦና ችግር ይፈጠርባቸውና ወደው በገቡበት ትዳር የሚፈጽሙትን ሩካቤንም የመፍራትና የመጥላት ምልክት ሊያሳዩ ይችላሉ። ይህ ዓይነት የሥነ ልቦና ችግር ያለባቸው ሰዎችን በግልጽ በማዋየት አስቀድሞ የተፈጠረባቸውን ችግር እንዲረሱና ዛሬ የሚፈጽሙት ሩካቤ ቀድሞ ከደረሰባቸው በግድ መደፈር ጋር ያለውን ልዩነት አውቀው በደስታ እንዲፈጽሙት ማበረታታት ያስፈልጋል እንጂ ችግራቸውን ሳንረዳ ለራሳችን ብቻ ዘብ ቆመን "ስሜታችን አልተጠበቀልንም" በማለት እየተቆጣንና እየተጣላን ችግሮችን ማባባስ ተገቢ አይደለም።

በ) ከላይ እንደተገለጸው በማፈንና በማስገደድም ሆነ በፈቃድ በሚፈጸም ሕጋዊ ጋብቻ ሴቶች ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ የሚፈጸም ሩካቤ ያለፈቃዳቸውና ያለ ጊዜው በመፈጸሙ ምክንያት ከሚያገኙት ደስታ ይልቅ የጤና መታወክና ሕመም ስለሚያጋጥማቸው ለሩካቤ

ያላቸው መነሣሣት ዘገምተኛ ይሆናል። ይህም ዕድሜአቸው ለትዳር በደረሰና በራሳቸው አነሣሽነት አግብተው ሩካቤን መፈጸም በፈለጉ ጊዜ በስሜታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማድረጉ አይቀርም።

ተ) ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሩካቤ ጊዜ ለሚፈጠር የባልና የሚስት አለመግባባት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ አንድ ወንድ የሚስቱን ክብረ ንጽሕና በጉጉት የሚጠብቅ ይሆንና በሩካቤ ጊዜ የጠበቀውን ባያገኝ ሚስቱን ክፉኛ ሊጠላትና ዳግመኛ አብሯት ለመተኛት ዕድሉን ላይሰጣት ይችላል። ይህ ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ሴቶች ከወንድ ጋር ግንኙነት ሳይፈጽሙ በልዩ ልዩ ምክንያቶች እና በግድ በመደፈር ድንግልናቸውን ሊያጡ ስለሚችሉ ሳይቸኩሉ ነገሩን ሁሉ በእርጋታ ማጤን ተገቢ ነው። አውቀውና ፈልገው ባላመጡት ነገር ተወቃሽ ሊሆኑ አይገባምና። ለዚህ ዓይነት ችግር ከጋብቻ በፊት ክህደትና ውሸት ያልተቀላቀለበት ግልጽ ውይይት ማድረግ መጠነኛ መፍትሄ ነው። ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ሩካቤና ድንግልናን ማጣት በጋብቻ ለሚፈጠር አለመግባባት በመንስኤነት ተጠቃሽ የሚሆነው በሴት በኩል ብቻ አይደለም። ወንዶችም ቢሆኑ ከጋብቻ በፊት ሴትን ልጅ በሩካቤ የሚያውቁ ከሆነ የቀደመችውን ሴት ጥብቅነት ካሁኗ ሚስታቸው ጋር በኀሊናቸው በማወዳደር በሚስታቸው የማይደሰቱ እንዲሆኑ ሰይጣን ሊፈትናቸው ይችላልና የወንዶችም ንጽሕናን ጠብቆ መኖር ለትዳር ሰላም ድጋፍነት አለው። ይህ ዓይነቱ ችግር ከባሏ አስቀድማ ሌላ ወንድ በምታውቅ ሴት ላይም መፈጠሩ የማይካድ ሐቅ ነው።

ቸ) ሌሎች በትዳር መካከል ለሚፈጸም ሩካቤ አለመስማማትን ሊፈጥሩ ይችላሉ የሚባሉት የባልና የሚስት መንፈሳዊ ግንዛቤ እጅግ የተራራቀ መሆን፣ በሰከሩ ጊዜ ብቻ ሩካቤን መሻት፣ ከልክ በላይ ሴሰኛ መሆን (ሩካቤን ማብዛት)፣ ከልክ በላይ ቀዝቃዛ መሆንና ሩካቤን ቸል ማለት፣ በሕጋዊነት የሚፈጸም ሩካቤን እንደረከሰ ድርጊት መቁጠርና ስለጋብቻና ሩካቤ የሚሰጠውን የቤተክርስቲያን ትምህርት በውል አለመረዳት ናቸው። ከዚህ በላይ ለጠቀስናቸው ችግሮች መፍትሔዎቻቸውን በዚሁ መጽሐፍ ቀደም ብሎና ወደፊት የሠፈረ በመሆኑ ልብ ብለው ይመርምሩ። ሌሎች ያልተጠቀሱ ችግሮች ደግሞ መተሳሰብ ባለበት ፍቅር በምክረ ካህን የሚፋቱ በመሆናቸው ችግሩ የገጠማቸው ባለትዳሮች መምህረ ንስሐቸውን እንዲያነጋግሩ ይመከራሉ።



## የባልና የሚስት ሩካቤን መከላከል

የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በሚገባ ባለማጤን ብዙ ሰዎች ካገቡ በኋላ የባልና የሚስትን ወግ አልፈጽምም በማለት ባል ሚስትን ፣ ሚስት ደግሞ ባልን እንደሚያስቃዩዋቸው ይደመጣል። በዚህም የብዙ ሰዎች ትዳር ተበጥብጧል። ያለማጋነን ለብዙ ሰዎች ትዳር መፍረስ ምክንያት የሚሆነው ይኸው ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። የጉዳዩ ባለቤቶች ግን በማፈርና በተለያዩ ምክንያቶች እንኳን ሌላ ሰውን በጉዳያቸው ጣልቃ አስገብተው ማማከር ይቅርና እርስ በርሳቸው እንኳን እንጃ! እንጃ! ከመባባል በቀር ጊዜ ሰጥተው አይወያዩበትም። ለወላጆች ለመምህራንና ለካህናት የልብ ቁስል የሆነባቸው ይህ ችግር በይበልጥ የሚታየው አዘውትረው ቤተክርስቲያን በሚመላለሱ ነጋ ለኪዳን፣ ጠባ ለቁርባን በማለት ለጸሎት፣ ለትምህርትና ለቅዳሴ በሚተጉ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን ላይ መሆኑ ነው። ስለሆነም ፈቃዳቸውን እንዳይፈጽሙላቸው ሚስትን በባል ባልን ደግሞ በሚስት ላይ የምታነሣሣው ቤተክርስቲያን እንደሆነች በማሰብ ብዙዎች ቤተክርስቲያንን በመቀየም ባለጋራዋ ሆነው ቀርተዋል። ይህን ሐሳብ የሚያጎላ ታሪክ በሐዋርያት ዘመንም ተፈጽሞ እንደነበረ ከዚህ በታች የምናነበው ታሪክ ያመለክታል።

የሮማ መኳንንት ግን አለብን በማለት ብዙ ሴቶችን በአንድ ጊዜ አግብተው ይኖሩ ነበር ፊት አይተው የማይፈሩ እውነተኛ መምህራን ሐዋርያት ደግሞ እነርሱን ከመገሠጽ ወደኋላ አላሉም። ቃላቸውንም ከመስማት ጆሮአቸውን በከደኑ ጊዜ የሰሟቸውን የመኳንንቱን ሚስቶች ባሎቻቸው በአንድ ሚስት እስካልተወሰኑ ድረስ እሺ በጀ ብለው እንዳይተኙ ያስተምሯቸው ነበር። ይህም ትምህርት ወንጌል ነውና ተገቢ ነበር። የመኳንንቱ ሚስቶችም በሐዋርያት ቃል አምነው የባሎቻቸውን ፈቃድ ነሱ። አልታብዮስና አክርጶስ የተባሉ መኳንንትም የዚህ ትምህርት የመጀመሪያ ገፈት ቀማሾች ስለነበሩ ሚስቶቻችንን የሚያነሣሣብን ጴጥሮስ የሚሉት መምህር ነው በማለት ሊገሉት ተማከሩ ጴጥሮስም ሊገሉት እንደተማከሩ በሚስቶቻቸው አማካኝነት ሰምቶ ልብሱን ቀይሮ ስደት ሲጀምር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንቀጸ ሮም ታየው ጴጥሮስም አንተ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለህምን? ሲል ጠየቀ ጌታም አዎን ነኝ አለው። በኢየሩሳሌም እንደተሰቀልክ ዳግመኛ በሮም ልትሰቀል ነውን? አለው ታዲያ አንተ ፈራህ ምን ላድርግ? ሲለው ተሰቀል እንጂ ሲለኝ ነው ብሎ ተመልሶ ወደሮም ገብቶ ሊሰቅሉት ሲሉ "ወአስተብቀያሙ ከመ

ይስቅልዎ ቁልቁሊተ" እንደጌታዬ ሽቅብ አትስቀሉኝ ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ ብሎ ለምናእቸው ቁልቁል ተሰቅሎ ሞቷል።

ቅዱስ ጴጥሮስ ተገቢውን ትምህርት አስተማረ እንጂ ግለሰቦችን ለመበደል ሆን ብሎ ያደረገው አንዳች ነገር አልነበረም። አልታቢዮስና አክርጳስም ከሚስቶቻቸው የለያቸው የልቦናቸው ሁሉ-አማረኝ መሆን ነው እንጂ በአንድ ሚስት ቢወሰኑ ኃጢአት ሆኖባቸው አይደለም። ቤተክርስቲያን ከዘማውያን ጋር አትተባበሩ በሥርዓት ከማይሄድ ባል ጋር የኃጢአቱ ተባባሪ አትሁኑ በማለት ማስተማሯ ሐዋርያዊ ተልዕኮዋ ነውና ያለ ስሟ ስም በመስጠት ባልና ሚስትን እንደምታለያይና የባልና የሚስት ወግ እንዳይፈጽሙ አንዱን በአንዱ ላይ እንደምታነሣሣ አድርጎ መናገር ባላጠፋው ጥፋትና ባልተናገረው ንግግር ጌታን የከሰሱ አይሁድን መምሰል ነው።

ዛሬም ቢሆን በአንድ ሚስት ወይም ባል የማይወሰኑ ሰዎች ቢኖሩና ሚስቶች ይህን እያወቁ ባሎቻቸው በፈረቃ ከእነሱ ጋር ለማደር ሲመጡ ባይቃወሙ እንደእነርሱ ዝሙት ወዳጆችና አመንዝራዎች መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። በተጨማሪም የትዳር አጋሮቻችን ከእኛ ተለይተው ከሌላ ሰው ጋር እንደማያመነዝሩ ብናውቅና ነገር ግን ከቤተክርስቲያን ቀኖና እና ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ ሩካቤ ሥጋን ከእኛው ጋር ለመፈጸም ቢሞክሩ መቃወማችን ያስመሰግነናል።

አለማግባት መብትህ ነው። ካገቡ በኋላ ሩካቤ መፈጸም ግን ግዴታህ ነውና መቃወም አትችልም። ባታገባ የተሻለ አድርገሃልና ኃጢአት አልሠራህም ይህንንም ስታደርግ ከዝሙት ርቀህ መሆን አለበት። "የዘማዊ ሰውነት እንደውሻ ርኩስ እንደኩስም የሚያጸይፍ ነውና።" (ገድለ ተክለሃይማኖት) ብታገባ ግዴታህንም ብትወጣ መልካም አድርገሃል። ፩ኛ ቆሮ. ፯:፳፰።

ከማግባትህ በፊት ምንአልባት ለጋብቻ አልበቃ ይሆንን? በማለት ራስህን ጠይቅ የጠገበ፣ በደዌ ወይም በጾም ምክንያት የማይመገብ ሰው ከበላተኞች ጋር በማዕድ ዙሪያ ለምን ይቀመጣል? የማትበላ ከሆነ ወደግብዣ ድንኳን አትግባ። ጋብቻም እንደማይሆንልህ ከታሰበህ ተገቢውን እርምጃ ውሰድ። "የጠመኛ ምቀኛ" እንዲሉ ለእኔ ካልሆነልኝ በማለት የሌላውን ሰው ሕይወት አታጥፋ ወይም ከማግባትህ በፊት ለጋብቻ ለመረጥከው ሰው ለትዳር ብቁ አያደርገኝም ብለህ የምታስበውንና የምትጠራጠረውን ችግር በሙሉ ያለ ምንም ማመንታት ግልጽልጽ አድርገህ ተናገር። አምኖና ተቀብሎ ከገባበት ዕዳ የለብህም። ይህ ካልሆነ ግን ወንጀለኛ መሆንህን እወቅ።



በብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናነበው ንጽሕናቸው የተመሰከረላቸው ደጋግ አባቶቻችን ለምሳሌ አባ ዜና ማርቆስ፣ አባ ሊባኖስ፣ገብረ መርዓዊ ከቤተሰብና ከቤተዘመድ ከልዩ ልዩ ክፍሎችም ወደ ትዳር እንዲገቡ ብዙ ተጽዕኖ ቢደርስባቸውም ካገቡ በኋላ ኃላፊነታቸውን ሳይወጡና ግዴታቸውን ሳይፈጽሙ ቀርተው በደል እንዳይሆንባቸው በመስጋት ጋብቻውን ከመነሻው ይቃወሙትና ይሸሹት ወይም የታጨችላቸውን ሴት በአንዳች ነገር ሳያስነውሩ ከጫጉላ ቤት ወጥተው ይሄዱ ነበር። ይህ ካለማግባት እኩል ነውና አብርሃም መርዓዊ የተባለ ደግ አባት ከሙሽርነት ዕድ ብርሀት (የምታበራ እጅ) እየመራች ወደገዳም እንደወሰደችው በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል። በእርሱ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ነበረና። ሁለት እጮኞች ምንም ለብዙ ዓመታት ተጫጭተው ቢኖሩ መጪው የጋብቻ ጊዜ ይበልጣልና አስጊ ነገር በመሀከል ካለ ወደፊት እየተቋሰሉ ከመኖር በግልጽ ተወያይቶ በጊዜ መለያየት ብልሃት ነው። ሁለቱም እጮኞች በመለያየታቸው ካሙኑ ጫጉላ ቤት እስኪገቡ ድረስ የመለያየት መብት እንዳላቸው ሊያውቁ ይገባቸዋል።

ከላይ የገለጽነውን ሐሳብ በሕይወታቸው ያሳዩ አባቶች ብዙ ቢሆኑም ከእነርሱ ውስጥ አንዱ አቡነ ሀብተማርያም ናቸው። አባታችን አቡነ ሀብተማርያምን ወላጅ አባታቸው ያለፈቃዳቸው እንዲያገቡ ባስገደዷቸው ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለተቃወሙና የልጃቸውንም ጻድቅነት አውቀው ስላላከበሩ እግዚአብሔር ተቆጥቶ በመብረቅ እንዲሞቱ እንዳደረገ ገድላቸው ይተርካል። እርሳቸውም ፈጣሪያቸውን በንጽሕናና በድንግልና አገልግለውታል። አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖትም እንዲሁ እርሳቸው ማግባትን ሳይሹ ወላጆቻቸው ባጩላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱ አልነበረምና ለዓይናቸው እንቅፋት የነበረችዩቱን ሴት በሞት ከፊታቸው አርቆላቸዋል። ከዚህ በኋላ አባታችን ያለምንም ነውር በንፅነት ሆነው ፈጣሪያቸውን አገልግለው አርፈዋል።

ገብረ መርዓዊ ወይም ገብረ ክርስቶስ ከብዙ ሰማዕታት ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ገድል ያለው ታላቅ አባት ነው። ሥርዓተ መርዓዊ ወመርዓት በሚፈጸምበት ቤት (ጫጉላ ቤት) የታጨችለትን ሴት ትቶ እኔ የክርስቶስ ሙሽራ ነኝ በማለት አካባቢውን ጥሎ የተሰደደና የለመነው ሁሉ የተፈጸመለት ደግ አባት ሲሆን በአባቱ ደጃፍ በልመና ረጅም ጊዜ ኖሮ በሚሞትበት ጊዜ "አነ ውእቱ ወልድከሙ ገብረ መርዓዊ" ማለትም "እኔ ልጃችሁ ገብረ መርዓዊ ነኝ" በማለት ጽፎ እንዳረፈ ተጽፎለታል። ይህም ካገቡ በኋላ ከባለቤቱ ጋር አብሬ አልተኛም ከማለት ጋር ፍጹም

## የባልና የሚስት መንፈሳዊ ጥንካሬ

በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ የሚገኘው ፈቃደ ሥጋ መጠኑ ይለያያል፡፡ አንዱ ለከን ያለ ሲሆን ሌላው ደግሞ ፈቃዱ በዓይኑ እስኪታወቅበት ድረስ ራሱን መግዛት የማይችል ሴሰኛ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ዳዊት ያን ሁሉ ሠራዊት ለጦርነት አዝምቶ እንኳን ከሚስቱ ጋር ይቅርና የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ ከማመንዘር ወደ ኋላ ባላለበት ሰዓት ከሠራዊቱ መሀል ያለ አንዱ ጭፍራ ኦርዮ ግን በጾምና በጸሎት ሰንበተ እንጂ ከሚስቱ ጋር እንኳን ለማደር ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ይህንንም "ታቦቱና እስራኤል ይሁዳም በድንኳን ተቀምጠዋል ጌታዬ ኢዮአብና የጌታዬ ባሪያዎች በሰፊ ሜዳ ሰፍረዋል እኔ ልበላና ልጠጣ ወይስ ከሚስቴ ጋር ልተኛ እሄዳለሁን? በሕይወትህና በሕያው ነፍስህ እምላለሁ ይህን ነገር አላደርገውም" ፪ኛ ሳሙ. ፲፩:፲፩፡፡ በማለት የተናገረው ቃል ያስረዳል፡፡ ይህ የኦርዮን መንፈሳዊነትና ደግነት የሚያስረዳ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሚስቱ ቤርሳቤህ እንደባልዋ ብዙ ወገኖቻችን ለጦርነት በሰፊ ሜዳ ላይ በሰፈሩበት በዚህ ጊዜ ከባሌ ሌላ ከባዕድ ሰው ጋር ይቅርና ከባለቤቴ ጋር እንኳን ቢሆን አብሬው አልተኛም በማለት ተመሳሳይ ጨዋነት አላሳየችም፡፡ ከንጉሡ ከዳዊት ጋር አመንዝራች እንጂ፡፡ እንዲያውም ሳይሳካላት ቀረ እንጂ በዚያው፣ ቅጽበት ፅንስ ለማሳሳት ከዳዊት ጋር ከተማከረች በኋላ ከባሏ ጋርም አብራው ለማደር ዝግጁ ነበረች ዳዊትን ከኦርዮ፣ ኦርዮን ደግሞ ከባለቤቱ ከቤርሳቤህ ጋር በማነጻጸር በሰዎች መካከል ያለውን የፈቃደ ሥጋ ልዩነት መረዳት ይቻላል፡፡ በተፈጥሮ፣ በዕድሜ፣ በጾታ ልዩነትና በጤና መታወክ ምክንያት የሚፈጠረውን የፈቃደ ሥጋ ልዩነት ማስወገድ ባይቻልም ባአኗኗራችን ምክንያት ግለትም አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት ከመንፈሳዊነት ውጭ በመሆንና በመሳሰሉት ነገሮች የሚፈጠረውን ሰፊ የፈቃድ ልዩነት አንድ ዓይነት መንፈሳዊ አቋም በመያዝና አኗኗርን በማቀናጀት ልዩነቶችን ቀንሶ ወደተቀራረበ ፈቃድ መድረስ ይቻላል፡፡

በባልና በሚስት መካከል ፍጹም መግባባት እንዲኖር የሁለቱም ባለትዳሮች መንፈሳዊ ጥንካሬ ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ የአንዳቸው መንፈሳዊ ሕይወት ሚዛን ከደፋ ግን ፍቅራቸውን ከማቀዝቀዙም በላይ በፈቃደ ሥጋ ፍጹም የማይመጣጠኑ እንዲሆኑ ዓይነተኛ ተጽዕኖ ያደርጋል ምክንያቱም በየጊዜው ንስሐ የሚገባ የሚጸምና የሚጸልይ መንፈሳዊ ነገርን በብርቱ የሚከታተል ሰው እግዚአብሔር መንፈሱን ያሳድርበትና የመንፈስ ፍሬ እንዲያፈራ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ፈቃደ ሥጋውን በቀላሉ ሊገዛ ይችላል፡፡ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ 'ራስን መግዛት' ነውና፡፡ ገላ. ፭:፳፫፡፡ በአንጻሩም በመንፈሳዊነቱ ድካም ያለበት ሰው



ራሱን ለመግዛት ይቸገራል፡፡ ከእግዚአብሔር እንደመራቁ መጠን ኃይለ እግዚአብሔር እንደ አጥርና እንደቅጥር አይቆምለትምና በዚህ የተነሣ ከፍተኛ የፈቃደ ሥጋ ልዩነት በባልና በሚስት መካከል ሊከሠት ይችላል፡፡ ውቀ ይህ ሆና ሳለ አንዳንድ ጊዜ በተለየ ረቂቅ ምክንያት መንፈሳዊነቱ ከተመሰከረለት ወገን ሴሰኝነቱ ሊያይልና ራሱን መግዛት ያልቻለው መንፈሳዊ ነው ተብሎ የተመሰከረለት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን የመሰለ አጋጣሚ ሲፈጠር የእግዚአብሔር ሥራ አይመረመርምና ከከንቱ ልፍለፋ፣ ፍርድና ሐሜት ርቆ የራስን ኃጢአት ብቻ እየተመለከቱ መኖር መልካም ነው፡፡ መጽሐፍ እግዚአብሔርን በማምለክ የታወቁ እስራኤላዊያንን ሴት ካዩ አያልፉም ነበር በማለት ሲገልጻቸው አሕዛብን ደግሞ ለዝሙት አይቸኩሉም በማለት ይገልጻቸዋል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፡፡" በማለት የመንፈሳዊያን ሰዎች ኃጢአት ከሥጋውያን የክርስቲያኖች ኃጢአት ደግሞ ከአረማዊያን ሰዎች ኃጢአት ብሶ የሚገኝበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ገልጸልናል፡፡ ፩ኛ ቆሮ. ፭:፩፡፡

ብእሲተ ሎጥ ከባሏና ከልጆቿ ተለይታ የጨው አምድ ሆና የቀረችው የሰዶምና የገሞራ ኃጢአት እንደጨው ያምራት ስለነበርና ባሏ ሎጥ በፍጹም ትሕትና የተቀበላቸው ሰማያዊ እንግዶች መላእክት ወደቤቷ በገቡ ጊዜ እንደባለቤቷ በትሕትና በመቀበል ፈንታ ጨው ለመበደር ጎረቤቶቿ ዘንድ ሄዳ "ይህን ዓይነት ሰዎች በእንግድነት ወደ ቤቴ ገብተዋል" በማለት መላእክትን በምኞቷ አሳልፋ ለከፉ ሰዎች ከመስጠቷም በላይ ለቃላቸው ባለመታዘዟ ነው፡፡ ባሏ ሎጥ ግን የሰዶምና የገሞራን ኃጢአት ጠልቶ ነፍሱን እያሳዘነ ይኖር ነበር "ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና እየሰማ ዕለት ዕለት በዓመጸኛ ሥራቸው ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበር፡፡" ፪ኛ ጴጥ. ፪:፯-፰ በማለት የሎጥን ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ ይተርካል በእነዚህ ሁለት ባለትዳሮች ይህን ያህል የሰፋ ልዩነት የምንመለከተው የሁለቱ መንፈሳዊ ጥንካሬ የሰማይና የምድር ያህል በመራራቁ ነው፡፡ ስለዚህ የባልና የሚስት መንፈሳዊነት ተመጣጣኝ መሆን ተስማምቶ ለመኖር የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ እንኳን በመንፈሳዊ አመለካከት ይቅርና በፖለቲካ፣ በሙያ ፣ በፍላጎት፣ ላይ የተመረኮዙ ተራ የሆኑ የዓላማና የአቋም ልዩነቶች የትዳርን ሰላም ለማናጋት የሚወዳደራቸው አይገኝም፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን የመንፈሳዊነት ደረጃ ልዩነት ለማስወገድና ፍጹም መግባባትን ለመፍጠር በአንድነት መጸለይ፣ በአንድነት ቤተክርስቲያን በመሄድ ፀበል እየተጠመቁ ቅዳሴ እያስቀደሱ መንፈሳዊ ነገር በሙሉ በኅብረት መከታተል፣ ንስሐ እየገቡ ሥጋ ወደሙን

መቀበል፤ ከእነዚህም የሚቀድመው ትምህርት ነውና የቤተክርስቲያንን መንፈሳዊ ትምህርት በግንባር በመገኘት በኅብረት መከታተል፤ ይህም ባይሳካ ለየብቻ የተማሩትን ትምህርት በተለያዩ ምክንያቶች በመንፈሳዊ የትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ላልቻለው (ላልቻለችው) የኑሮ አጋራችን የሚደርስበትን መንገድ ማመቻቸትና ተግባራዊ ማድረግ፤ ነገር ግን አብረው ይጸልዩ ሲባል ሁለቱም ያለማቋረጥ ተግተው ይጸልዩ ማለት ነው እንጂ ባንድ ቦታ ቆመው ባንድ ወንበር ተቀምጠው ያስቀድሱ ይማሩ ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የወንድና የሴት መቆሚያና መቀመጫ በቦታ ልዩ ነውና።

የታላቁ መስፍን የሶምሶን እናት እንትኩይ መካን በነበረችበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ተገልፆ ታላቁን መስፍን ሶምሶንን እንደምትወልድና ከመውለዷም በፊትና በኋላ ማድረግ ያለባትን ነገራትና ተሰወረ። እርሷም ሄዳ ለባሏ ለማኑሄ የተገለጠላትንና መልአኩ የነገራትን በሙሉ ሳትሸሽግ ነገረችውና ተመለሰች። በጸሎታቸው መሠረት መልአኩ ዳግመኛ ወደርሷ በመጣ ጊዜ ባሏ ወደነበረበት ሄዳ ከጠራችው በኋላ ተያይዘው ወደ መልአኩ መጡ። ማኑሄም ወደ መልአኩ ቀረብ ብሎ "ከዚህች ሴት ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህን" በማለት ሚስቱ የነገረችውን እራሱም ጠይቆ እንደተረዳ እናነባለን። እኛም የምናየውንና የምንሰማውን በመገባበዝ በአንድነት ማድረግ መመካከርና በግልጽ መወያየት ይልቁንም መንፈሳዊ ነገርን በኅብረት መከታተል እንዳለብን እነዚህ ሁለት ባለትዳሮች ማኑሄ እና እንትኩይ ምሳሌ ሁነውናል። መሳ. ፲፫:፩-፲፬።

ንጹሑን የክርስትና ኑሮ መኖር የማይፈልጉና ለሃይማኖታቸው ግድየለሽ የሆኑ ሰዎችን ስለ ሃይማኖታችን ብዙ ባልተገነዘብንበት ጊዜ አግብተን የምንኖር ከሆነ መንፈሳዊነት ይቀረቀረናል የምንል እኛ ወደ ቅራኔ በማምራት መጸየፍንና ጥላቻን ሳናሳይ በትሕትና ሆነን የኑሮ አጋራችንን ወደ መንፈሳዊነት ለመለወጥ ጥረት ማድረግ አለብን። ይህ ጥረት ግን ብርቱ ድካምና ሰፊ ትዕግሥት እንደሚጠይቀን መገንዘብ ያስፈልጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባልና የሚስትን በአንድነት ወደርሱ መቅረብ ይወዳል። ሳምራዊቷ ሴት "ጌታ ሆይ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ" ባለችው ጊዜ "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽው ነይ" ያላት ባልና ሚስት ማንኛውንም መንፈሳዊ ነገር በአንድነት እንዲፈጽሙ ለማስተማርና አብረው ወደርሱ መቅረባቸውን እንደሚወድ ለማሳወቅ ነው። ዮሐ. ፬:፲፩-፲፯።



## በኀዘን ምክንያት ሩካቤን ስለመከላከል

ማንኛውም ሰው በወዳጅ በዘመድ ሞት ምክንያት በተለያየ ጊዜ ኀዘን ይገጥመዋል በዚህ አጋጣሚ ኀዘናቸውን ከልክ በላይ በማድረግ ለትዳራቸው ሰላም እንቅፋት እስከ መሆን የሚደርሱ ብዙዎች ናቸው። ስለዚህ ለጊዜው በደረሰብን ኀዘን ምክንያት እያማረርን በትዳራችንና በወደፊት ኑሮአችን የማይድን በሽታን መትከል አይገባንም። ለምሳሌ:- አንዲት ሴት እናት ፣ አባት፣ ወንድሞችና እኅቶች ወይም የገዛ ልጆቿ በሞት ቢለዩዋት ኀዘኗን በልክ በማድረግ የልቦናዋን ገጽ ወደ ባሏ መመለስ አለባት እንጂ ኀዘንተኛ ነኝና ምንም መጠየቅ የለብኝም በማለት ምሪቷን በባሏ ላይ መወጣት እና ባሏን ፊት መንሣት አይፈቀድላትም። ይህ ድርጊት ቀድሞ በባሏ ላይ ጥላቻ ኖሯት ዛሬ ባጋጠማት ኀዘን ምክንያት የቀድሞ ጥላቻዋን ለመግለጽ እንደሞከረች ያስጠረጥራል። ስለዚህ በኀዘን ሰበብ የቀደመ ሐሳብን ለማሳካት መኝታ መለየት መብት አይደለም ሚስት ቤተሰቦቿ በሕይወት እያሉ እንኳን ስለባሏ ስትል እንደተለየቻቸው መዘንጋት የለባትም። ይህ ከሆነ ደግሞ በሞታቸው ጊዜ ቤተሰቦቿንም አጥታ ባሏንም አስቀይማ ብቻዋን የሚያስቀራትን እሰጥ አገባ መፍጠር ምን ይባላል? እንዲያውም እንዲህ ያለ ኀዘን ሲገጥም ሚስት በባል ባልም በሚስት መጽናናት ይገባቸዋል። በኀዘን ጊዜ ከባለቤቱ ጋር አልተኛም በማለት መኝታን መለየት ትልቅ ስሕተት ነው። ሟች ወገናችን የሚጠቀመው ቢጸሙለት፣ ቢጸልዩለት፣ ቢመጸውቱለት ፣ ፍትሐት ቢያስፈቱለት እንጂ መኝታ ለይተው ባልና ሚስት ሲነዛነዙለት አይደለም ስለዚህ "ሙት ዓመታቸውን ሳላወጣ እንተኛ የምትለኝ ሰው ሞተብኝ እንጂ ግንድ የረበረብኩ መሰለህ እንዴ?" በማለት ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር የወጣ ስድ ንግግር ትተን ትዳራችንን ለማቃናት ደፋ ቀና ማለት ይገባናል። ከሞት ሥርግ ፤ ከሟችም የኑሮ አጋር ይበልጣሉና።

ከሦስቱ አርዕስተ አበው አንዱ ይስሐቅ በእናቱ ሞት ቢያዝንም ከማግባት ግን አልተከለከለም። እንዲያውም በእናቱ ሞት ምክንያት ከደረሰበት ኀዘን የተጽናናው ሚስቱ ርብቃን ካገኛት በኋላ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠቅስ "ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት ርብቃንም ወሰዳት ሚስትም ሆነችው ወደዳትም ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና " ዘፍ. ፳፬:፷፯ በማለት ያብራራል ።

የቀኖና መጽሐፍቶችን ፍትሐ ነገሥት ሴት ልጅ ባሏ ከሞተ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዳግመኛ ማግባት ከፈቀደች የማግባት መብት እንዳላት እየገለጸልን ባለቤት ያልሞተብን እኛ ስለሁለተኛ እና ሦስተኛ ወገን ሞት ባላችንን ወይም ሚስታችንን በምንጣፍ ለመገናኘት ከዓመት

ተሳምደው በሚሠሩት ሥራ ውስጥ የሁለቱም ፈቃድ ተጠቃሽ መሆኑን እንመለከታለን። እንደዚሁም ከሆነ አንዱ ወገን ፈቃደኛ ሌላው ወገን ከልካይ መሆን አይገባውም ማለት ነው።

በተጨማሪም የሴት ልጅ ፈቃድ እንደወንድ ፈቃድ ተጠቃሽ መሆኑን "ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል" ዘፍ. ፫:፲ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል። በሌላ መልኩ በጋብቻ ጊዜ የሴቲቱና የወንዱ የሁለቱም ፈቃደኝነት ይታያል እንጂ በአንደኛው ወገን ፈቃድ ብቻ ጋብቻ አይፈጸምም። ለዚህም የርብቃ ወላጆች ይስሐቅን ለማግባት ትፈቅድ እንደሆነ በማለት ልጃቸው ርብቃን መጠየቃቸው አሳባችንን ግልጽ ያደርገዋል። ዘፍ. ፳፬:፶፯-፶፰ ሴት ልጅ ለማግባት መፍቀድና አለመፍቀዷ በትድሚያ የሚጠየቅ ከሆነ ፈቅዳ ካገባች በኋላ ለሚከናወነው ማንኛውም ድርጊት ፈቃደኝነቷን መጠበቅ እንዳለበት ጥርጥር የሌለው ነገር ነው።

ምንም እንኳን አዳምና ሔዋን በሠሩት ስሕተት እግዚአብሔር ስላዘነባቸው እርስ በእርሳቸው ተወነጃጅለው ቢለያዩም የእግዚአብሔር መልአክ አዳምን ያለሔዋን ከውድቀቱ እንደማይነሣና ራሱም ሄዶ ከሔዋን ጋር መታረቅ እንዳለበት ስለነገረው እራሱ ሄዶ ታርቋታል። ከዚህ መንፈሳዊ ትውፊት በመነሣት ወደ ሴት ቤት ሽማግሌ (አማጭ) በመላክ ለጋብቻ የሚጠይቅ ወንድ መሆኑ ቢታወቅም ሴት ልጅ ግን ጋብቻውን የመቀበል ወይም ያለመቀበል ሙሉ መብት እንዳላትና የፈቀደችውን ወንድ ለጋብቻ መጠየቅ እንደምትችል መታወቅ አለበት። ርብቃ ይስሐቅን ስታገባ በመጀመሪያ ሙሉ ፈቃደኝነቷ ተጠይቆ ነበርና። ዘፍ. ፳፬:፶፰ ።

ሴት ልጅ ከማግባቷ አስቀድሞ ስለጋብቻው ፈቃዷ ከተጠየቀ ካገባች በኋላ በቤቷ እና በባሏ ላይ ሥሉጥ (ሥልጣን) ያላት በመሆኗ ባሏ ፈቃዷን እንዲፈጽምላት መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በሰውነቱ ለማዘዝም ሥልጣን አላት "ሚስት በገዛ ሥጋዋ ሥልጣን የላትም ሥልጣን ለባሏ ነው እንጂ እንዲሁ ባል በገዛ ሥጋው ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ" ይላል ፩ኛ ቆሮ. ፯:፬ ሌሊትና መዓልት ዘመንን እኩል እንደሚካፈሉት ባልና ሚስትም በሁሉም ነገር መብታቸው እኩል ነው።

ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ የሚያስፋፋ መረጃ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ እናገኛለን። የንጉሥ ዳዊት ሴት አያት ለሆነች ለሩት አማትዋ ኑሐሚን እንደእድሜ ባለጸግነቷ በደረጃ ዕውቀት ባሏ ለሆነው ለቦዔዝ ማድረግ ያለባትን ለሩት ስታስረዳት "በተኛም ጊዜ የሚተኛበትን ስፍራ ተመልከቺ ገብተሽም እግሩን ግለጪ ተጋደሚም የምታደርጊውንም እርሱ ይነግርሻል" ሩት 3:4 በማለት መከረቻት፤ እሷም እንደተመከረች



አደረገች። "ቦዔዝም ማን ነሽ አለ እርሷም እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ ዋርሳዬ ነህና ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ አለችው" ሩት. ፫:፱ ይላል። ይህም ታሪክ ሴት ልጅ እንዲያገባት የፈለገችውን ወንድ ለጋብቻ መጠየቅና ያገባችውንም ደግሞ ፈቃዷን ይፈጽምላት ዘንድ ፍላጎቷን መግለጽ መቻሏንና መብቷ መሆኑን ያሳያል።

ሴቶች ፍትወት ሲቀሰቀስብን ሳናመነታና ሳናፍር ባሎቻችንን መጠየቅ እንችላለን። ይህ ይሉኝታ ቢስ መሆን ሳይሆን ሙሉ ሰው መሆንን ማረጋገጥ ነው። ባለቤቴ ይታዘበኝ ይሆን በማለት እየተጨነቁ ወደኋላ በማለት እራስን መበደል ተገቢ አይደለም። ባለቤታችንን መውደዳችን የሚታወቀው እርሱ በፈለገን ጊዜ ፈቃዱን ለመፈጸም ዝግጁ ስንሆን ብቻ ሳይሆን እኛም እንደምንፈልገው ገልጸን ስንናገርም ጭምር ነው። ማንም እራሱን አይታዘብም በባልና በሚስት መካከልም በግልጽ መወያየት እንጂ መተዛዘብ መኖር የለበትም። ሁለቱም አንድ ሥጋ ናቸውና። ሴት ልጅ የምትሻውን ነገር በነፃነት ገልጻ ስትናገር የማያስደስተው ወንድ ካለም ስለ ሥጋው ደካማነት ያልተገነዘበ አላዋቂ በመሆኑ ስለ እርሱ ሲባል የሴት ልጅ የፈቀደችውን ገልፃ የመናገር መብት እንደማይገፈፍ ማወቅ አለበት።

"ሮቤል ስንዴ በሚታጨድበት ወራት ወጣ በእርሻም እንኮይ አገኘ ለእናቱም ለልያም አመጣላት። ራሄልም ልያን የልጅሽን እንኮይ ስጪኝ አለቻት። ባሌን መውሰድሽ በውኑ ጥቂት ነገር ነውን? አሁን ደግሞ የልጄን እንኮይ ልትወስጂ ትፈልጊያለሽን? አለቻት። እንኪያስ ስለልጅሽ እንኮይ በዚህች ሌሊት ካንቺ ጋር ይተኛ አለቻት። ያዕቆብም ሲመሽ ከዱር ገባ ሊያም ልትቀበለው ወጣች እንዲህም አለችው ወደ እኔ ትገባለህ በልጄ እንኮይ በእርግጥ ተከራይቼሃለው። በዚያችም ሌሊት ከርሷ ጋር ተኛ" ዘፍ. ፴:፲፬-፲፮። ልያ የያዕቆብ ሕጋዊ ሚስት ናት ስለሆነም ከእርሷ ጋር እንዲያድር ባሏን በግልጽ መናገሯ ኃጢአት አልሆነባትም። ዛሬም ቢሆን እውነተኛ ባለትዳር የሆኑ ሚስቶች ልያ ባሏን "ዛሬ ወደእኔ ትገባለህ" እንዳለችው ሁሉ እነርሱም ባላቸውን ዛሬ አብረን ፈቃዳችንን እንፈጽማለን ማለት መብታቸው ነውና ኃጢአት አይሆንባቸውም።

ቤተክርስቲያን በሚስት እንደምትመሰል ክርስቶስ ደግሞ በባል እንደሚመሰል በብዙ ቦታ ተደጋግሞ ተጽፏል። ቤተክርስቲያን በየዕለቱ የሚያሻትን ሁሉ ገልጻ ጌታዋ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትጠይቀው (እንደምትለምነው) ሁሉ ሚስትም ባሏን የምትሻውን እንዲፈጽምላት መጠየቅ ትችላለች።

በየሰው ሰውነት ውስጥ የሚገኘው የፈቃደ ሥጋ አምሮት መጠን እንደሚለያይ ግልጽ ነው። በተለይም የሴቶች ስሜት ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሦስት እጅ ብልጫ እንዳለው ይታመናል። ይህን ለማመጣጠን እግዚአብሔር የወንዶችን ፈቃደ ሥጋ አሳንሶ ነገር ግን የወደዱትን እንደልባቸው መጠየቅ የሚችሉ ልባሞችና ደፋሮች ሲያደርጋቸው ሴቶችን ደግሞ የፈቃደ ሥጋ አምሮታቸውን ከወንዶች በሦስት እጅ ከፍ በማድረግ በኀፈረ ገጽ (በግፈር) እና በጭምትነት ምግባር አስጊጧቸል። ስለዚህ ምንም እንኳን ሴት ልጅ የፈቀደችውን ገልጻ የመናገር መብት እንዳላት ብንናገርም ሁሉን በልቧ በማመቅና በዝምታ ራሷን የምትበድል እንዳትሆን ነው እንጂ የሴት ልጅ ዝግተኛነትና ጭምትነት በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ እጅግ ተወዳጅ መሆኑን በመዘንጋት አይደለም። ከወንድ በሦስት እጅ ከሚበልጥ ፍትወት ጋር በልባምነት ደርሶ እንደ ወንዶች የመናገር መብት በተፈጥሮ ለሴቶች ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ በወንዶች ላይ የሚደርሰውን ችግር መገመት ባልቻልንም ነበር። እስኪ ይህን ሐሳብ የሴቶች እንደ ወንድ በልበ ሙሉነት ሐሳባቸውን ገልጾ መናገር እንደባሕል በሚታይባቸው አህጉራት ማለትም በአውሮፓ እና በሌሎችም አህጉራት ከሚገኙ ሴቶች ጋር የአገራችንን ሴቶች በማነጻጸር ልብ ብለው ይመርምሩት።

## ምዕራፍ ፯

### ቅድመ ሩካቤ የሚደረጉ ዝግጅቶች

በጋብቻ ውስጥ ለሚከናወነው ሕጋዊ ተላጽቆ (ሩካቤ ሥጋ) ሕሊናዊ እና አካላዊ ዝግጅቶች ያስፈልጉታል። እነዚህንም ዝግጅቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች መመልከትና ማወቅ በግድ ያስፈልጋል እነርሱም

፩. ራስን መግዛት

፪. ሩካቤ የምንፈጽምበትን ዕለትና ሰዓት ማወቅ

#### ፩. ራስን መግዛት

ቅድመ ሩካቤ የሚደረጉ ዝግጅቶችን ማመቻቸት ከፈለግን በጥምቀት አማካኝነት ያገኘነውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተገን አድርገን ራሳችንን መግዛት ያስፈልገናል። ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ራስን መግዛት ነውና። ገላ. ፭:፳፫ ራሱን መግዛት የማይችል ሰው ግን ፍትወተ ሥጋው በተቀሰቀሰበት ጊዜ ቅድመ ሩካቤ ለሚደረጉት ዝግጅቶች ጊዜ ስለማይሰጠው ያለምንም አካላዊና ሕሊናዊ ዝግጅት ተንደርድሮ ወደሩካቤ እንዲያመራ ያደርገዋል። በዚህ ጊዜ የሁለቱንም ደስታ



ሊቀንሱ የሚችሉ ልዩ ልዩ ነገሮች ሊከሠቱ ይችላሉ። ቅድመ ሩካቤ የሚደረግ ዝግጅት ለባልና ለሚስት በሩካቤያቸው መርካት ወደር የማይገኝለት አስተዋጽኦ ያደርጋል።

#### ፪. ሩካቤ የምንፈጽምበትን ዕለትና ሰዓት ማወቅ

ማንኛውም ሰው የማያውቀውና ተስፋ ያላደረገውን ነገር ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ሊጠብቀው አይችልም። እንደዚሁም ሁሉም ቅድመ ሩካቤ መደረግ ያለበትን ሕሊናዊና አካላዊ ዝግጅት ለማድረግ ባልና ሚስት ሩካቤ የሚፈጽሙበትን ዕለትና ሰዓት ቀደም ብለው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ለዚህ ደግሞ ሳይፈራሩና ሳይተፋፈሩ መነጋገር ይገባቸዋል። ምንም እንኳን ባልና ሚስት አንድ ሥጋ እንደመሆናቸው መጠን ባይተፋፈሩም እርስ በርሳቸው እንደልብ መወያየት የማይችሉበት ብዙ አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል የራሳቸው የሆነ መግባቢያ ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ለምሳሌ በቀላሉ ሊግባቡ የሚችሉ ባልና ሚስት ይሆኑና ሚስት ከባሏ ጋር ማታ ሩካቤን ለመፈጸም ትፈልጋለችና ባሏን ለማዘጋጀትና ለማነሣሣት አሰበች እንበል ገና ጠዋት ከቤት ሲወጣ አምሽቶ የማያውቅ ባሏን "ማታ እንዳታመሽ እሺ የኔ ቆንጆ!" ብትለው ባሏ በቀላሉ ፍላጎቷን ሊረዳ ይችላል። ባልም በበኩሉ ውድ ሚስቱን ማታ ለሩካቤ ተዘጋጅታ እንድትጠብቀው ለማድረግ ከፈለገ አንዳች ያልተናገረችውን ሚስቱን "ምነው በጠዋት ነገር ነገር አለሽ? ሥራ ልታስረፍጂብኝ ነው አይደል? ማታ ልምጣ ብቻ እሠራልሽ የለ!" ቢላት ባሏ ምን ለማለት እንደፈለገ በቀላሉ ይገባታል። ይህ ለምሳሌ ተነገረ እንጂ ባልና ሚስት የየራሳቸው ሌላ መግባቢያ እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው። በተለያዩ ምልክቶች ፈቃድን መግለጽና ሌላውን አካል ማነሣሣት ድንቅ ነገር አይደለም። አውራ ዶሮም ያደርገዋልና የእንስቲቱን ፈቃድ ወደርሱ ለመሳብና ለማነሣሣት ክንፉን እንከርፍፎ በእንስቲቱ ዶሮ ይዞርባት የለምን? ታዲያ በእኛ በሰዎች ሲፈጸም ድንቁ ምኑ ላይ ነው? በሥጋዊ ተፈጥሮአችን በብዙ ነገር እንስሳትን እንመስላቸዋለንና።

ሕሊናችንና አካላችንን አዘጋጅተን ሩካቤን መፈጸም እንዳለብን ማስተማሪያ ምሳሌ የተወለን ጋብቻን ባርኮ የሰጠን አምላካችን ነው። እግዚአብሔር ረዳት እንደምታስፈልገው አውቆ ሔዋንን ለአዳም ከመፍጠሩ በፊት እንግዳ እንዳትሆንበትና በሁሉም ነገር ራሱን አዘጋጅቶ ሚስቱን ሔዋንን እንዲቀበላት "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" ዘፍ. ፪:፲፰ በማለት ሔዋንን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ለአዳም ተስፋ እንደሰጠው

እናነባለን አዳም በዚህ ቃል መሠረት ራሱን አዘጋጅቶ ሔዋንን ተቀብሏታል። ስለዚህ ባልና ሚስት ሩካቤ ከመፈጸማችን በፊት አስቀድመን ተስፋ በመስጠት ባለቤቶቻችንን በሰዓቱ ራሳቸውን አዘጋጅተው እንዲጠብቁ ማድረግ ሩካቤያችንን እጅግ አስደሳች ያደርገዋል።

ቅድመ ሩካቤ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ሕሊናዊና አካላዊ ዝግጅቶች ሲሆኑ ሁለቱም በየራሳቸው ባለብዙ ዘርፎች ናቸው። ለተሻለ ግንዛቤ እንዲረዳን እያንዳንዱን በየተራ እንመለከታቸዋለን።

## ፩. ሕሊናዊ ዝግጅት

የሕሊና ዝግጅት ሩካቤ የምንፈጽምበትን ዕለት ከማወቅ ይጀምራል። ሕሊናዊ ዝግጅት ሰውነታችንን በፈቃደኝነት ተነሣሥቶ ሩካቤ እንዲፈጽም ከማድረጉም በላይ ቅድመ ሩካቤ ለሚደረግ አካላዊ ዝግጅት መሠረት ነው። ሕሊናችን ካልፈቀደና ካልተዘጋጀ አካላችን ለሩካቤ መዘጋጀት አይችልምና።

### ፩.፩ ፈቃደኝነት

በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጸም ሩካቤ ዐቢይ ነገር ፈቃደኝነት ነው። አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸውን በተለያዩ መንገዶች በማስገደድ እንደሚገናኟቸው ይደመጣል። ይህ ድርጊት ፍጹም አብደት ነው። ምክንያቱም በምንም መንገድ ካልፈቀደችና ሩካቤን ለመፈጸም ካልተነሣሣች ሚስት ጋር በማስገደድ ማደር ግንድ አቅፎ እንደማደር ምንም ስሜት የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ ማስገደድ በራሱ ወንጀልና የወይፈት ኑሮአችንን ሰላም የሚያደፈርስ ድርጊት ነው። ማስገደድ ይቅርና ፍላጎት ሳይኖራቸው በምን ቸገረኝነት ከአንገት በላይ በመፍቀድ ባልና ሚስት አብረው ለመተኛት መነሣሣታቸው እንኳን ትልቅ ጉዳት አለው። ስለዚህ እኛ ሩካቤን በፈቀድንበት ዕለት ባለቤቶቻችን ካልፈቀዱ የተከላከሉበትን ምክንያት በመመርመር ወይም በግልጽ በመጠየቅ በእኛ በኩል ጥፋት ተፈጥሮ እንደሆነ ከስሕተታችን መታረም እነርሱም ከተሳሳቱ ወይም በሚገባ ምክንያት ተከላክለውም ከሆነ ተወያይቶ ወደስምምነት መድረስ ተገቢ ነው። በአንድ ፈቃድ የሚፈጸም ሩካቤ እርኪነቱ በበረሃ እንደሚገኝ ውኃ ነው ፈቃደኝነትም ከሕሊና ዝግጅቶች አንዱ ነው።

✱ በተጨማሪም "የባልና ሚስት አለመፈቃቀድ" ከሚለው ጀምሮ "ፈቃደኝነት" እስከሚለው ንዑስ ርዕስ ድረስ ይህን ሐሳብ የሚያስፋፉ ብዙ ነጥቦች ሰፍረዋልና ያንን በድጋሚ ይመልከቱ።



### ፩.፪ ከሥጋት ነጻ መሆን

በሩካቤ ጊዜ ሥጋት ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች በሩካቤያችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖራቸው ከሩካቤ በፊት እልባት በመስጠት ሕሊናችንን ከማንኛውም ዓይነት ሥጋት ነጻ ልናደርገው ይገባል።

ለምሳሌ ባልና ሚስት በቂ ልጆችን እግዚአብሔር ሰጥቶናል ከአሁን በኋላ መውለድ አንፈልግም ብለው ከወሰኑ ወይም ለጊዜው ልጅ መውለድ የማይፈልጉበት በቂ ምክንያት ካለ እፀንስ ይሆን? እወልድ ይሆን? ቢሚል ሥጋት ስሜታቸውን ቋጥረውት ሩካቤን ከሚፈጽሙ መተው ይሻላቸዋል። በተጓዳኝም ምንም በትዳራችን ቢሆን ሩካቤን ሕገወጥ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉና እነርሱን በመፈጸም ጨንገር እንዳሳዩት የሕፃን ልጅ ዓይን እግዚአብሔር ይቀጣን ይሆን? በማለት ሕሊናችን በሥጋት እንዳይባክን ከሕገወጥ ሩካቤ በመቆጠብ ሕሊናችንን ለተቀደሰ ሩካቤ ብቻ ልናሰናዳው ይገባናል። በሌላም በኩል በሩካቤአችን ሰዓት በመታወስ ሕሊናችንን እንዳይረብሹት ልናከናውናቸው የሚገባን በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮቻችንን በሙሉ ከፍጻሜ በማድረስ ወይም በታ ቦታ በማስያዝ ልባችንን በእነርሱ ምክንያት ከሚፈጠር ሁከት ነጻ በማድረግ ሕሊናችንን በዚያች ውስን ሰዓት ለአንድ ሥራ ብቻ ማሰለፍ ተገቢ ነው። በተጨማሪም ከበር መከፈት እስከመኝታችን መንሳጠጥ (ሲጢጥ) ማለት ድረስ ያሉት ነገሮች ምንም በትዳራችን ቢሆን ታየን? ወይስ አልታየንም? በማለት ሕሊናን ሊያውኩ ስለሚችሉና በሩካቤ ጊዜ የሚፈጠር ድንጋጤ ጤናን በእጅጉ ሊጎዳ እንደሚችል በመረዳት ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ከባልና ሚስት ይጠበቃል። ይህም ቅድመ ሩካቤ የሚደረግ የሕሊናዊ ዝግጅት አካል ነው።

### ፩.፫. የሕሊና ወቀሳን ከሚያመጣ ተግባር መሸሽ

በሩካቤ ሰዓት የምናከናውናቸው ተግባራት ሕሊናችን በፍትወት ስለተጋረደ ለጊዜው ላንጠላቸው እንችላለን ነገር ግን ያ ሁሉ በስሜት መታወር ሲነጋ ከምሽቱ ጨለማ ጋር አብሮ ስለሚሸሽ ልብ በገዛንና ሥራችንን ማስተዋል በጀመርን ጊዜ እርስ በርሳችን ለመተያየት እንኳን እስከንተፋፈር ድረስ አንገት የሚያስደፉና የሚያስጸጽቱ ይሆናሉ። ስለዚህ መወጣት የማንችለው የሕሊና ወቀሳና ጸጸት እንዳይደርስብን ምንም በትዳራችን ቢሆን ነውር የሆነ ሩካቤ (ግብረ ሰዶም) ፤ከሥርዓትና ከጊዜ ገደብ ውጭ የሆነ ግንኙነት፤ ልጅ ላለመውለድ በሚደረጉ ሰው ሠራሽ የእርግዝና መከላከያ መሣሪያዎች በመታገዝ የሚፈጸም ሩካቤና የወንድ ዘርን ከማኅጸን በአፍአ (በውጭ) በማፍሰስ ከሚፈጸም ሩካቤ

ፈጽመን መሸሽ ይጠበቅብናል። ማንኛውም ባለትዳር ባወቀና በተረዳ ጊዜ ከኀሊና ወቀሳ ለመዳን በሩካቤ ወቅት መፈጸም ያለባቸውንና የሌለባቸውን ነገሮች ለይቶ ማወቅ ይጠበቅበታል። ይህን ያደረገ ሰው ቅድመ ሩካቤ ሊደረጉ ከሚገባቸው ሕሊናዊ ዝግጅቶች ቢያንስ አንዱን ፈጽሟል ማለት ነው። በሩካቤ ጊዜ መከናወን ያለባቸውና የሌለባቸው ነገሮች ከሞላ ጎደል በዚህ መጽሐፍ ሰፍረዋል።

*፩.፬. ሩካቤ ንጽሕ መሆኑን ማመን*

በሁለት ሕጋዊ ተጋቢዎች መካከል ሕግና ሥርዓት ተከተሎ የሚፈጸም ሩካቤ ሁሉ ንጽሕ ነው። አንዳንድ ሰዎች ምንም እንኳን ለአፍ ክርስቲያኖች ነን ቢሉም በሕግ የተደገፈ ሩካቤን በመጸየፍና በመሸሸው ምክንያት ከመናፍቃንና ከአረማውያን ጎራ መቆጠራቸው አልቀረም። የሆነው ሆኖ ማንኛውም ሰው እንኳን አግብቶ ከሩካቤው በፊት ይቅርና ከማግባቱ በፊት እንኳን በሕጋዊ ሩካቤ ንጽሕናት አምኛለሁን? በማለት ራሱን ሊጠይቅ ይገባዋል። በሕግ የተደገፈን ሩካቤ ቅድስና የማያምን ማንም ቢሆን ለጋብቻ ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያንነትም ብቁ አይደለም። ከሩካቤም ሆነ ከጋብቻ በፊት የሚቀድመው ሕሊናን የባልና የሚስት ሩካቤ ንጽሕ እንደሆነና ከእግዚአብሔር ዘንድም ሽልማት እንጂ ምንም ዓይነት ቅጣት እንደማያመጣ ማሳማን ነው። ይህም ቅድመ ሩካቤ ሊደረጉ ከሚገባቸው ሕሊናዊ ዝግጅቶች አንዱ እና ዋነኛው ነው። በተጨማሪም 'ጋብቻ ንጽሕ ነው' በሚለው ርዕስ ውስጥ የተሰጠውን ሐተታ ይመልከቱ።

*፩.፭. መጸለይ*

ከሕሊናዊ ዝግጅቶች አንዱ ጸሎት ነው። ባልና ሚስት ከሩካቤ በፊት የሚጸልዩት በተለያዩ ምክንያቶች ሲሆን ጸሎቱም በውስጡ ብዙ ጠቀሜታዎችን አካቶ ይገኛል።

እግዚአብሔር የምንበላውንና የምንጠጣውን እንደሰጠን አምነን ካልሆነ በስተቀር ብንበላ እንደማንጠግብ ብንጠጣ እንደማንረካ የታወቀ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር እራሱ የሰጠንን እንዲባርክልን እና ባርኮ ስለሰጠንም እርሱን ለማመስገን በማንኛውም ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች ከማዕድ በፊትና በኋላ ጸሎት እናደርሳለን። በተመሳሳይ ሁኔታ ሩካቤም ለተጋቢዎች ብቻ የተለየ ምግብ ነውና ባለ ትዳሮች ሁሉ ከሩካቤ በፊትና በኋላ ጸሎት ማድረግ ይገባቸዋል።

ሰይጣን በትምህርታችን፣ በሥራችን፣ በምግባችን፣ በመጠጣችንና በእያንዳንዱ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴአችን እየገባ እንደሚፈታተነን ሁሉ ባልና ሚስትም ተላጽቆ (ሩካቤ) በሚፈጽሙበት



ጊዜ በመሃል እየገባ እንዳይስማሙ፣ እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩ፣ የሩካቤን ጣዕም እንዲያጡ እና ከዚህም በመነሣት፣ በቁጣ፣ ተስፋ በመቁረጥ እና በብስጭት ሌላ ኀጢአትንም እንዲሠሩ ሊያነሣሣቸው ይችላል። ይህንንም ከሣራ ወለተ ራጉኤል ታሪክ መረዳት ይቻላል። አስማንዲዮስ የሚባል ክፉ ጋኔን ጭኗ ላይ አርፎባት ሰባት ወንዶች ቢያገቧትም ሰባቱም በወንድና በሴት ልማድ ሳይቀርቧት እየታነቁ እንዲሞቱ አድርጎአቸዋል። መጽ ጦቢ. ፫:፯-፱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም" ዮሐ. ፬:፲፰ በማለት የተናገራት ሳምራዊት ሴት አምስት ባሎችን በየተራ ብታገባም የሣራ ወለተ ራጉኤል ዓይነት እድል ስለገጠማትና ስድስተኛውም እንዳይሞትባት በመስጋት ከቤቷ ውጪ ስንቅ እያቀበለችው በሩቅ ታኖረው ስለነበር ጌታ "አሁን ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም" በማለት ተናግሯታል ይህም ታሪክ ሰይጣን በትዳር ውስጥ ምን ያህል ያለማቋረጥ ፈተና እንደሚያመጣ ተጨማሪ መረጃ ነው።

ዳግመኛም በትንሣኤ ሙታን ጊዜ ማግባትና መጋባት እንደሌለ ያልተገነዘቡና ትንሣኤ ሙታንን ጨርሶ የማይቀበሉ ዝሁላን አእምሮ አይሁድ "ሰባት ወንድማማቾች በእኛ ዘንድ ነበሩ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች ሁሉም አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?" ማቴ. ፳፪:፳፭-፳፰ በማለት ጌታችንን በጠየቁት ጊዜ ትንሣኤ ሙታን መኖሩንና ከትንሣኤም ሙታን በኋላ ግን ማግባትና መጋባት እንደሌለ አብራርቶ መልስ ሰጥቶአል። ይሁን እንጂ አይሁድም ቢሆኑ በእውነት ከተፈጸመ ነገር ተነሥተው ነው እንጂ ከሌለ ነገር ተነሥተው የዚህ ዓይነት ጥያቄ አላቀረቡም። ስለሆነም ሰባቱም ባሎቿ ዘር ሳይተኩ የሞቱባት የዚች ሴት ሕይወት ከላይ የገለጽነው የሣራ ወለተ ራጉኤል ዓይነት ፈተና ገጥሟት እንደነበር መጽሐፍ ያትትልናል።

ታድያ በትዳራችን በሚፈጸም ሩካቤ ውስጥ ሰይጣን እንዲህ ያለ ፈተና ሊያመጣብን እንደሚችል ከተገነዘብን ከጸሎት በላይ ጋሻ የለንምና ከሩካቤያችን በፊት የሰይጣንን የፈተና መረብ ለመበጣጠስ ተግተን መጸለይ ያስፈልገናል። የጦቢት ልጅ ጦቢያ ሰባት ባሎች የሞቱባትን ሣራን ቢያገባትም ጸሎተኛ ነበርና ከሰባቱ ባሎቿ እንደ አንዱ አልሆነም ምንም እንኳን የሣራ አባት ራጉኤል እንደሰባቱ ባሎቿ ይሞትና ያድራል በማለት ጉድጓድ ቆፍሮ በማለዳ ለመቅበር ቢጠባበቅም መልአኩ

ቅዱስ ሩፋኤል (አዛርያ) ከጦብያ ጋር ስለነበርና ማድረግ ያለበትን በሙሉ ስላመለከተው አንዳች ጉዳት አላገኘውም ስርዓተ መርዓዊ-ወመርዓት ወደሚፈጸምበት ቤት (ጫጉላ ቤት) በገቡ ጊዜ ጦቢያ ብድግ ብሎ መልአኩ እንዳመለከተው የዓሣ ጉበትና ልብ አጢሶ ጸሎት ጀመረ። ሚስቱንም ከሩካቤ በፊት እንዲህ አላት እኅቴ ተነሽ እግዚአብሔር ይቅር ይለን ዘንድ እንጸልይ አላት "አቤቱ የአባታችን ፈጣሪ አንተ ምስጉን ነህ የከበረ ስምህም ይመስገን ለዘለዓለሙም ይመስገናል። የፈጠርካቸው ፍጥረትና ሰማዮችም ያመሰግኑሃል ይል ጀመር አባታችን አዳምን ትረዳው ዘንድ ሔዋንን እንፍጠርለት አንጂ አዳም ብቻውን ይኖር ዘንድ አንተ በጎ ነገር አይደለም አልክ አሁንም ይህቺን የማገባት በሚገባ ነገር ነው እንጂ ስለዝሙት አይደለምና አቤቱ እንረዳዳ ዘንድ ለእርሷና ለኔ ይቅርታህን ስደድልን አለ። እርሷም ከእርሱ ጋር በእውነት ይደረግልን አለች በዚያች ሌሊት ሁለቱም አብረው አደሩ። "ጦቢ. ፰፥፬-፱ ጦቢያ ይህን ጸሎት በጸለየ ጊዜ ሰይጣን እንደ ጢስ ተንኖ ጠፍቶአል መልአኩ አዛርያም(ሩፋኤልም) አስሮ አግዞታል። በተመሳሳይ መልኩ ወላጆቻቸውም ይጸልዩላቸው እንደነበር ሙሉ ታሪኩን ስናነብ እናገኘዋለን። ስለዚህ እኛም ተንደርድረን መኝታችን ላይ ከመውደቃችን ና ሩካቤ ከመፈጸማችን በፊት ራሳችንን ገዝተን መጸለይ ይጠበቅብናል በጸሎታችን ጊዜም ግር እንዳይለንና የምንለው ያልተለመደ ነገር እንዳይሆንብን የጦቢያና የሚስቱን ጸሎት በቃልና በመጽሐፍ ልንደግመው እንችላለን።

ጸሎት በፍጹም እምነት መደረግ አለበት። በፍጹም እምነት የሚደረግ ጸሎት ግዳጅ ይፈጽማልና አስቀድሞ ለትዳር የበቃነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው እንጂ በኛ ድካምና ጥበብ አይደለም። ከጋብቻ በኋላም በባልና በሚስት መሐከል ለሚፈጠር ማንኛውም ግጭትና ችግር መፍትሔው የሚገኘው በእግዚአብሔር እጅ ስለሆነ ምንም እንኳን የተፈጠረብን ችግር በእኛ አቅም ለማቃለል የማይታሰብ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ማንኛውም ነገር እንደ ኢምንት ነው መካኖችን እንዲወልዱ ያደረገና የሚያደርግ እርሱ ነው ዳግመኛም ሙቀት ልምላሜ የተለያቸውን (የጃጁ) ሰዎችን ሰውነት አድሶ በማስነሣት ልጅ እንዲታቀፉ የሚያደርጋቸው እርሱ ነው። የአብርሃም ባለቤት ሣራ "በውኑ ካረጀሁ በኋላ ፍትወት ይሆንልኛልን ባለቤቴም ፈጽሞ አርጅቷል" ዘፍ. ፲፰፥፲፪ በማለት የቀቢፀ ተስፋ ንግግር ተናግራ ነበር። ጌታን ግን የሙት አካል የሚመስል የቀዘቀዘ ገላዋን አሟሙቆ ከባሏ ከአብርሃም ደግ ልጅ ይስሐቅን እንድትወልድ አድርጓታል። ስለዚህ ተስፋ ሳይቆርጡና ሳይጠራጠሩ የሚጸልዩትን ጸሎት ከልኩ የማያሳፍር



ጌታ ሁሉን ለማድረግ ቻይ ነው። እንደዚሁም ሁሉ በትዳር ውስጥ በሚፈጸም ሩካቤ አለመግባባት ሲፈጠር ከጥንቆላና ከድግምት ወይም ከሌላ እግዚአብሔርን ከሚያስቆጣ ተግባር ርቀን ራሱን እግዚአብሔርን ደጅ ብንጠና ነገሮች ሁሉ በመልካም ተለውጠው የምናይበት ቀን እሩቅ አይሆንም አንዳንድ ሰዎች ከላይ የጠቀስነው ዓይነት ችግር በመሃላቸው ሲከሠት ጸበል እየተጠመቁና ንስሐ ገብተው ሥጋውንና ደሙን እየተቀበሉ በሽታቸውን እስኪድኑ ድረስ በማስታመም ፋንታ ከጋብቻ በፊት ሩካቤን መፈጸም እንደነበረባቸው በማሰብ ይቆጫሉ ይህ ሐሳብ ግን ዝሙትን እንድንለማመድ ሰይጣን የፈጠረው ዘዴ ነውና ፈጽሞ ሊቀበሉት አይገባም ።

"ቅዱሳን በክብር ይመካሉ በምንጣፋቸውም ላይ ሐሴት ያደርጋሉ።" መዝ. ፩፻፵፱፥፭ ይላልና እኛ ክርስቲያኖች ሩካቤአችንን ከመፈጸማችን በፊት የምንጸልየው እንደ ቅዱሳን ደስታን በልባችን ጨምሮ እንዲያስደስተንና ሁሉን ያዘጋጀና ፈቅዶ ለሰው ልጆች የሰጠ እርሱ ስለሆነ ፈጣሪያችንን ለማመስገን ነው። በተጨማሪም በተለያዩ አንጉል ሰብከቶችና ክስተቶች ምክንያት ጋብቻንና ሩካቤን የሚጸየፉ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሊፈጽሙት ስለተዘጋጁበት ሩካቤ በሚጸልዩበት ጊዜ ሕሊናቸው በጋብቻ ንጹሕነት እያመነና እየተወለወለ ይመጣል። ይህም የጸሎት ዓይነተኛ ጥቅም ነው።

ቅድመ ሩካቤ ጸሎት የምንጸልየው የኛ ግንኙነት የሠመረ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን የሩካቤያችን ውጤት ሆነው የሚወለዱት ልጆችም የተባረኩ እንዲሆኑ ጭምር ነው። ብዙ ቅዱሳን እናቶቻችንና አባቶቻችን በተቀደሰ ጋብቻ ሆነው እግዚአብሔር የተባረከ ልጅ እንዲሰጣቸው ነገር ግን የሚወልዱት ልጅ ብሩክ የማይሆን ከሆነ ማኅጸኔን ዝጋው በማለት ከሩካቤያቸው በፊት ይጸልዩ ነበር። ከእነሱም ውስጥ የአቡነ ተክለሃይማኖት እናት እግዚእኅረያ ለአብነት ትጠቀሳለች። ስለዚህ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ጸሎት እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ከሩካቤ በፊት ሳያቋርጡ መጸለይን ልንለማመድ ይገባናል በሕግ የተደነገገውን ድጋም ሳይደግሙና ሳይጸልዩ ወደ መቅደስ መግባት ምን ዓይነት ድፍረት ይሆን? ሳይጸልዩ ወደ ሩካቤ መኳዝም እንደዚሁ ነው።

## ፪ አካላዊ ዝግጅት

አካላዊ ዝግጅት ሕሊናዊ ዝግጅትን ተከትሎ የሚደረግ ሲሆን በቂ እረፍት ያገኘና የተረጋጋ ሰውነትን ገንዘብ ከማድረግ ጀምሮ ፍጹም ንጹሕ መሆንንና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው በዚህ ርእስ ንጹሕ መሆን የሚለው ቃል ከእድፍና ከተለያዩ ነገሮች ፀድቶ መገኘትን የሚያመለክት ሲሆን ጥርስን መፋቅና ጥፍርን መቁረጥ የሚሉ ዝርዝር

መግለጫዎች ሳይሰጡበት በሁለንተናችን ጸድተን መገኘት እንዳለብን ያሳያል።

### ፪.፩ ንጽሕና

"የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ እርጉም ይሁን" ኤር. ፵፰:፲ በማለት የተናገረውን ቃል ወደጎን ትተው ልጅን ያህል ድንቅ ፍጡር የሚፈጠርበትን ታላቁን የእግዚአብሔር ሥራ ሩካቤን በቸልተኝነት ከማዕድ ቤት ላበትና ጥላሸት እንዲሁም የሰነበተ የራስ ቂቤአቸው ጋር ሆነው የሚፈጽሙት ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ለዚህም ሥራቸው በእግዚአብሔር ፊት ከመወቀሳቸውም በላይ የራሳቸውን ስሜት ይበድላሉ ለመብላት የምግብ ፍላጎት እና ንጽሕና ወሳኝ እንደሆኑ ሁሉ ለሩካቤም ሕሊናዊና አካላዊ ዝግጅቶች ወሳኞች ናቸው። ከአካላዊ ዝግጅቶች አንዱ ደግሞ ንጽሕና ነው።

ብዙዎች ሁሉም ማለት ይቻላል የቤተክርስቲያን ምሥጢራትን ለመፈጸም ከሌላ ዝግጅቶች በተጨማሪ መተጣጠብ እና ከሥጋዊ እድፍ ጸድቶ መገኘት ያስፈልጋል። የጋብቻ ምሥጢር ሩካቤም ሲፈጸም እንዲሁ ሊሆን ይገባል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ስማቸው የገነነ እናቶችና አባቶች በሩካቤ ጊዜ ጽዳት እንደሚያስፈልግ በተግባር በማሳየት ምሳሌ ሆነውናል ። እስራኤላውያን ከእርሷ የተገኙባት ሣራ ለጌታዋ ለአብርሃም ልጅ እንዳልወለደችለት ባየች ጊዜ በማዘን ከገረዷ ከአጋር ልጅ እንዲወልድ ገረዷን አሳልፋ ለአብርሃም ስትሰጣት ፀጉሯን ላጭታ ጥፍሯን ቆርጣ ገላዋን አጥባ ካዘጋጀቻት በኋላ እንደነበር በአራት መጽሐፍት ትርጓሜ ተጽፎ እናነባለን።

እናታችን ሣራ የሠራችው ሥራ ምንም ዓይነት ሕግና ሥርአት ባልተሠራበትና ሰዎች ሁሉ በልቦናቸው ባለ ሕግ በሚራመዱበት ጊዜ ቢሆንም በኋላ ዘመን እግዚአብሔር የሣራን ተግባር "... ከተማረኩት መካከል የተዋበች ሴት ብታይ ፣ ብትመኛትም ሚስት ልታደርጋት ብትወድ ወደ ቤትህ ታመጣታለህ እርሷንም ራሷን ትላጫለች ጥፍሯንም ትቆርጣለች የተማረከችበትንም ልብስ ታወልቃለች በቤትም ተቀምጣ ስለእናትና አባትዋ አንድ ወር ሙሉ ታለቅሳለች ከዛ በኋላ ትደርስባታላህ ባልም ትሆናታለህ እርሷም ሚስት ትሆንሃለች። "ዘዳ. ፳፩:፲፩-፲፫ በማለት አጽንቶላታል። ስለዚህ ሩካቤን በንጽሕና ሆኖ ማከናወን ተገቢ ነው።

ነገር ግን ስለ ጥፍር መቆረጥ ስንናገር በአንዳንድ ብሔረሰብእ እንደሚደረገው መቀፈፍ (ጥፍርን ከነሥጋው በማንሣት ሴት ልጅን ማቁሰል) ተገቢ ነው ማለታችን እንዳልሆነ ተገንዘቡልን። በተመሳሳይ ሁኔታ ሴቲቱ ባሏን እንዳታደክም በሚል ፈሊጥ ሴትን ልጅ ከሩካቤ



በፊት ለተወሰኑ ቀናት ኮሶ እያጠጡና ምግብ እየከለከሉ ማጎሳቆልም እንደሃይማኖት ሥርዓት አይቆጠርም ።

ሁል ጊዜም ባይሆን በዕድሜ የቀደሙት ሰዎች ብዙ መልካም ነገሮች ሊያስተምሩን ይችላሉ። ኑኃሚን የልጇ ሚስት የነበረችውን ደጓን ሩትን ለባሏ ለቦኤዝ ማድረግ ያለባትን ስትመክራት "እንግዲህ ታጠቢ ፣ተቀቢ ፣ልብስሽንም ተላበሺ ወደ አውድማውም ውረጂ ነገር ግን መብሉንና መጠጡን እስኪጨርስ ድረስ ለሰውየው አትታይው በተኛም ጊዜ የሚተኛበትን ስፍራ ተመልከቺ ገብተሽም እግሩን ግለጪ ተጋደሚም የምታደርጊውን እርሱ ይነግርሻል" ሩት. ፫:፫-፬ ለማለት ከሩካቤ በፊት መፅዳት ብቻ ሳይሆን አቅም ካለ መቀባባት እና ሽቶ መንዛት (መነፍነፍ) እንደሚቻል "ተቀቢም" በማለት የመከረቻት ምክር ያስረዳናል።

### ፪.፪ ሽቶ መቀባት

መልካም መዓዛ ለስሜት ድጋፍ ነው። ይህን ሐሳብ ጋለሞቶች በይበልጥ የተረዱት ይመስላል ጭሳጭስና ሽቶ በብዛት የሚዘግቡ እነርሱ ናቸውና ነገር ግን ምንም ከክርስትና ጎዳና የወጡ ጋለሞቶች በብዛት ቢጠቀሙበትና በሳይንስም ሽቶ በስሜት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ብንሰማም በቤተክርስቲያን ግን ሽቶ አትቀቡ የሚል ሕግ የለምና እንጠቀምበታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የአንዷት ጋለሞታን ሥራና ንግግር እንዲህ በማለት ያትታል "ስለዚህ እንድገናኝህ ፊትህንም በትጋት ለመሻት ወጥቼሀሉ አግኝቼሃለውም በአልጋዬ ላይ ማለፊያ ስርፍ ዘርግቼበታለሁ የግብፅንም ሸመልመሌ ለሀፍ ለመኝታዮም ከርቤና ዓልሙን ቀረፋም ረጭቼበታለሁ። ና! እስኪነጋ ድረስ በፍቅር እንርካ በተወደደ መተቃቀፍም ደስ ይበለን ። ባለቤቴ በቤቱ የለምና ወደ ሩቅ መንገድ ሄዷልና በእጁም የብር ከረጢት ወስዷል ሙሉ ጨረቃ በሆነች ጊዜ ወደ ቤቱ ይመለሳል።" ምሳ. ፯:፲፮-፳ ከዚህም ለሩካቤ የሚደረገው ዝግጅት ምን እንደሚመስል ስናይ ፤ በአንፃሩ ደግሞ ይህ ሁሉ ዝግጅት የተደረገው ለውሽማ መሆኑን ስናይ ልባችን ይደማል። ይህች ሴት ይህን ሁሉ ዝግጅት ከሕጋዊ ባሏ ጋር ለምትፈጽመው ሩካቤ ብታደርገው ምንኛ ባማረባት ብቻ ምን ያደርጋል ሁሉ በሁሉ ዘንድ አይገኝምና ዋልጌ ሴቶች ዝግጅቱን ያውቁበታል መልካምና ጨዋ ሴቶች ደሞ ማድረግ ያለባቸውን አንዱንም የማያውቁ ይሆናሉ ።

በመጨረሻም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምንም እንኳ የመልእክቱ ምሥጢር ጋብቻን እንደረከሰ ነገር እንዳንቆጥረውና

እንድናከብረው ቢሆንም በሰሙ ግን ከሩካቤ በፊት ንጽሕና እንደሚያስፈልግ የሚያስረዳ ቃል እንዲህ በማለት ጽፏልና "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን" ዕብ. ፲፫:፬ ስለሆነም በሕሊናችን በሕጋዊ መንገድ የሚደረግ ሩካቤን ሳንጸየፍ መቀበላችንንና አክብሮታችንን በተግባር ለመግለጽ መኝታችንና ሰውነታችንን ማፅዳት ይገባናል ። ምንም እንኳን ለሩካቤ አስባ ባታደርገውም ዳዊት ቤርሳቤህን የተገናኛት ከተጣጠበችና ከፀዳች በኋላ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ፪ሳሙ. ፲፩:፪-፭ ስለዚህ ከሩካቤ በፊት መተጣጠብ ከተቻለ ደግሞ መልካም መዓዛ ያለው ሽቱ ገዝተን (ረጭተን) ልንፈጽመው ይገባል።

### ፪.፫ ምርዓት

ባልና ሚስት ከሩካቤ አስቀድሞ ሰውነታቸውን በማሟሟቅ ለሩካቤ የሚዘጋጁበት መነካካትና መሳሳም መዳራት ወይም ምርዓት ይባላል። ይህም የሩካቤ ዋዜማ ነው። ነገር ግን ሕጋዊ ጋብቻ በሌላቸው ሰዎች መካከል መዳራት ቢፈጸም ለበለጠ ስሕተት ወደ ዝሙት ይዟቸው ከመሄዱም በላይ በመዳራት ብቻ ቢወሰኑም እንኳን ፍፁም ኃጢአት ነው። ጥበበኛው ሲራክ መዳራትን በሚነቅፍበት ግዜ "ፈቃዷ እንዳያስትህ ድንግልን አትቆንጥጣት" ሲራ. ፱:፭ ብሏል። አንድ ሰው ምንም የተማረና ለክህነት የታጨ ቢሆን ሳይሾም ታቦትን መዳሰስ እንደማይችል ሁሉ ያላገባ ሰውም እጮኛውን በዝሙት መንፈስ ሊነካት አይፈቀድለትም። እግዚአብሔርም ዕፀበለስን እዳይበሉ አዳምና ሔዋንን ሲያዛቸው "እንዳትሞቱ ከእርሱም አትብሉ አትንኩትም" ዘፍ. ፫:፫ በማለት አዘዛቸው እንጂ "አትብሉ"ብቻ ብሎ እንዳላለፋቸው ተመልከት። እኛንም እንዲሁ ፈጣሪያችን "አታመንዝር" ዘፍ. ፳:፲፬ በማለት ብቻ አላለፈንም መዳራትም እንደማንችል በተለያየ መንገድ አስተማረን እንጂ። ገላ. ፭:፳ ፤ ቲቶ. ፩:፮ ፤ ፪ኛ ጴጥ. ፪:፬ ምክንያቱም ማመንዘር ዕፀበለስን እንደመብላት ሲሆን መዳራት ደግሞ እንደመንካት ነውና። ይህንን ምዕዳን (ምክር) ተላልፈን እርስ በእርሳችን ለመዳራት ብንሞክር ማናችንም ከቅጣት አናመልጥም። "የሚነካትም ሳይቀጣ አይቀርም " ምሳሌ. ፮:፳፱ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናልና። ሳይሾም ታቦተ ጽዮንን በእጁ የነካ ዖዛ ከእግዚአብሔር መቅሠፍት እንዳላመለጠ አልተማርከንምን? ሳያገባ የሚዳራም ዕድሉ እንዲሁ ነው። ፪ሳሙ. ፮:፮-፰።



ብዙ ሰዎች መዳራትን በአሉታዊ ገጽታው ብቻ ይመለከቱታል። ነገር ግን ይህን መፈጸም በሚገባቸው ባልና ሚስት መካከል ከተፈጸመ አዎንታዊ ገጽታም እንዳለው ልንረዳ ይገባናል። ምክንያቱም ቅድመ ሩካቤ አካላዊ ዝግጅት መደረግ እንዳለበት የታመነ ነው ከአካላዊ ዝግጅቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ ሰውነትን ለሩካቤ በማነሣሣት ማድራት (ማሞቅ) ሲሆን ይህም ሊፈጸም የሚችለው ባልና ሚስት ከሩካቤ አስቀድሞ በሚያደርጉት መነካካት (መተቃቀፍና) መሳሳም ወይም ምርአት ስለሆነ ነው።

ምርዓት (መዳራት) ሰውነትን ማሞቅና ማነሣሣት ለሩካቤ ማዘጋጀት መሆኑ ከላይ ተጠቅሷል ነገር ግን ለማንኛውም ሰው ቢሆን ከማግባቱ በፊት ነገ ከሚያገባት ሴት ጋር ቢሆን እንኳን ዛሬ ለመዳራት አይፈቀድለትም። ይህን ለመረዳት ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ልብ ብለው ያንብቡ "ይስሐቅም በጌራራ ተቀመጠ የዚያም ስፍራ ሰዎች ስለሚስቱ ጠየቁት እርሱም እኅቴ ናት አለ የዚህ ስፍራ ሰዎች ስለርብቃ ሲሉ እንዳይገድሉኝ ብሎ ሚስቴ ናት ማለትን ፈርቷልና። እርሷ ውብ ነበረችና በዚያም ብዙ ቀን ከተቀመጠ በኋላ የፍልስጥኤም ንጉሥ አቤሜሌክ በመስኮት ሆና ጎበኘ ይስሐቅም ሚስቱን ርብቃን ሲዳራት አየ አቤሜሌክም ይስሐቅን ጠራ እንዲህም አለው።እነሆ ሚስትህ ናት እንዴትስ እርሷን እኅቴ ናት አልህ? ይስሐቅም በእርሷ ምክንያት እንዳልሞት ብዬ ነው አለው።" ዘፍ. ፳፮:፯-፱።

ይስሐቅ ስለራሱ ከመፍራቱ የተነሣ ሚስቱን እኅቴ ናት ቢልም ንጉሡ አቤሜሌክ ግን ይስሐቅ ሚስቱ ርብቃን ሲዳራት በግልጽ በመመልከቱ በእርግጠኝነት እነሆ ሚስትህ ናት ለምን እኅቴ ናት አልከን በማለት መናገሩ መዳራት(ምርዓት) ከሚስት ጋር ብቻ የሚፈጸም ተግባር መሆኑን ያረጋግጥልናል። በተጨማሪም እነሆ ሚስትህ ናት አለው እንጂ የሴት ጓደኛህ(እጮኛህ)ናት አለማለቱን ልብ እንበል። መዳራትን ከእኅትና ከዘመድ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእጮኛም ጋር መፈጸም ክልክል ነው። ያ ባይሆን ኖሮ ንጉሡ አቤሚሌክ በእርግጠኝነት ሚስትህ ናት ከማለት ይልቅ እነሆ እጮኛህ ወይም ሚስትህ ናት ለምን እኅቴ ናት አልከን ባለው ነበር።

## ምዕራፍ ፯

## ሩካቤና ሥርዓቱ

ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው እግዚአብሔር በሰጠው ሕግና በሠራው ሥርዓት የሚሄዱ ሰዎች የተመሰገኑ ናቸው። በረከትንና

ድኅነትንም ያገኛሉ፡፡ "በመንገዳቸው ንጹሐን የሆኑ በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ ምስጉኖች ናቸው።" መዝ. ፩፻፲፰:፩:1 በማለት ጽፎልናል። እግዚአብሔር ክርስቲያኖች የሚሄዱበትን የሕግ መንገድ ሠርቶ ሰጥቷል። ጋብቻ አንዱ መንፈሳዊ ጎዳና ስለሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ 'ኑ እናንተ የአባቴ ቡሩካን' ተብሎ ለመመስገን ጋብቻችንንና በውስጡ የምንፈጽመውን ሩካቤ በንጹሕ መንገድ ማከናወን ይጠበቅብናል።

በክርስትና ሃይማኖት ሁሉም ነገር ሥርዓት አለው። ብዙ ሰዎች ባለማወቅና ለሕግ ተገዢ ባለመሆን ሲፈጽሙት አይታይ እንጂ በክርስትና ሥርዓት የሌለው ነገር የለም በመንፈሳዊ ሥርዓት ጋብቻቸውን በፈጸሙ ሰዎች መካከል የሚከናወን ሩካቤም የራሱ የሆነ የአፈጻጸም ደንብና ሥርዓት እንዳለው መታወቅ አለበት። ሐዋርያው "ሁሉ በእናንተ ዘንድ በሥርዓት ይሁን" ብሏል። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫:፵

አንዳንድ ሰዎች ከትዳራችን አንውጣ እንጂ ልባችን እንደፈቀደው ብንሆን ወይም ብናደርግ ምን አለበት? በማለት ሰዶምና ገሞራ በእሳት የጠፉበትን አስጸያፊ ሥራ በትዳራቸው ለመፈጸም ሲሟገቱ ይደመጣሉ። ይህም ድርጊት እንስሳዊ ተግባር ስለሆነ ሰብአዊ ሕሊና ያላቸው ሰዎች የትዳራቸውን መኝታ በዚህ ምክንያት ሲሸሹ ይገኛሉ። እንዲህ ዓይነቱን መረን የተለቀቀ የወሲብ እንቅስቃሴ እንኳን ከትዳራችን አንደኛው ወገን ተጸይፎትና ተቃውሞት ይቅርና ወሲብ ሳይንስ ነው፣ ወሲብ ጥበብ ነው እያልን በአንድ ልብ ተስማምተን ብናደርገው እንኳን ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ቅጣትን ያስከትልብናል።

የሰው ልጅ ከመጀመሪያውም የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው። በኋላም በኃጢያቱ ምክንያት የዲያብሎስ ተገዥ ቢሆን እግዚአብሔር ራሱ በወርቀ ደሙ ስለዋጀው የሰው ልጅ ለሁለተኛ ጊዜ የእግዚአብሔር ገንዘብ ሆኗል። ቅዱስ ጳውሎስ "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" ፩ኛ ቆሮ. ፮:፳ ሲል የጻፈልን ስለዚህ ነው። በዚህ ቃል መሠረት ነው የእግዚአብሔር ንብረት እንደመሆናችን መጠን በሰውነታችን የሚያዝበት እግዚአብሔር ነው እንጂ እኛ ራሳችን አይደለንም። "ከንፈራችን የኛ ነው ጌታችን ማን ነው?" መዝ. ፲፩:፬ በማለታቸው እንደተጎዱ ሰዎች በመሆን እኛም መላ ሕዋሳችን የኛ ነው አልተዋስነውም ወይም አልተበደርነውም በትዳራችን ይህን አድርጉ ይህን ደግሞ አታድርጉ የሚለን ማን ነው? በማለት ልባችን የፈቀደውን



ለመሆን መብት የለንም። በሰውነታች በሥርዓት እንድንኖር የሚያዝበት ፈጣሪያችን በመካከላችን አለና።

በሕግና በሥርዓት ካልተፈጸመ በቀር ከትዳር ውጪ ባለመፈጸሙ ብቻ ሩካቤ ንጹሕ ሊሆን አይችልም። በትዳር ውስጥ በሚፈጸም ሩካቤም ሥርዓትን በመተላለፍ ብዙ ኃጢአት ሊፈጸም ይችላልና ውጤቱም ጥፋት ይሆናል፤ ሕግና ሥርዓት በመተላለፍ ተፈጽሟልና። "ዘርዕ ዘይወጽእ እምስካበ ተዓዳዌ ሕግ ይከውን ለትጥቃጤ ወለሙስና" ይህም ማለት "ከሕግ ተላላፊ መኝታ (ሩካቤ) የሚወጣ (የሚገኝ) ዘር ለኀዘንና ለጥፋት ይሆናል" በማለት መጽሐፍ የሕግ ተላላፊዎችን ግንኙነት ያወግዛል። መጽሐፈ ጥበብ. ፫:፲፮።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ" ፪ኛ ተሰ. ፪:፫ በማለት የገለጸው ሐሳዌ መሲሕ በተልከሰከሰ የመቃብር ሥፍራ በሚከናወን ዝሙት እንደሚፀነስ መጻሕፍት ተናግረዋል። እንደ ሐሳዌ መሲሕ "የጥፋት ልጅ" ዮሐ. ፲፯:፲፪ የተባለ የአስቆሮቱ ይሁዳም ሽማግሌና ነቢይን ከሚያቃልል ሰው በስካር መንፈስ ከተፈጸመ ሩካቤ የተገኘ 'የስካር ፅንስ' እንደመሆኑ መጠን "ከሕግ ተላላፊ መኝታ የሚወጣ ዘር ለኀዘንና ለጥፋት ይሆናል" የሚለው የመጽሐፍ ቃል ሲፈጸምበት እንመለከታለን።

ሕግና ሥርዓትን በማፍረስ ያለልክ በመብላትና በመጠጣት በመስከርም ወይም እንደ አደንዛዥ ዕፅ ያሉ ነገሮች በሚፈጥሩት ጫና የሚፈጸም ሩካቤ የተወገዘ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ሕግና ሥርዓትን በመጠበቅ በእውነተኛ ማንነታችን የምንፈጽመው ሩካቤ የተወደደ ነው። ጥንታዊያኑ ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ሕጋዊ ያልሆነ ሩካቤን ከመፈጸም የራቁ ነበሩ። በንጽሕና የሚፈጸም ሩካቤ ውጤቱ እጅግ አስደሳች ነው። መጽሐፍ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጽንስ ሲናገር "አ! ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተፀንስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ"ይህም ድንግል ሆይ በልተው ጠጥተው በሚያመጡት የፈቲው ጽንት የተፀነሽ አይደለሽም በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐና እና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ" ማለት ሲሆን እመቤታችን "ብዙ ተባዙ" የሚለውን የእግዚአብሔር ፈቃድ በሐቅ ለመፈጸም በተደረገ ንጹሕ ሩካቤ መገኘቷን ይገልጻል። ይህም ታሪክ "በንጽሕናና በሥርዓት የሚፈጸም ሩካቤ አስደሳችና ታላቅ ጸጋን የሚያሰጥ ነው" በማለት ከላይ ለገለጽነው ሐሳብ አንድ በቂ መረጃ ነው።

## ሩካቤ በስውር መፈጸም አለበት

ፍጹም ሰብእናቸውን ወደ እንስሳነት ለውጠው አእምሮአቸውን ካጡ ሰዎች በስተቀር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳን ነውር ነውና" ኤፌ. ፭:፲፪ በማለት እንደተናገረው ዝሙትን በግልጽ በአደባባይ ላይ የሚፈጽም አይገኝም። ለዚህም ሥራው ሁሉ ዝሙት የነበረና ደናግላን ሴቶችን በመሰብሰብ በግድ ይደፍራቸው የነበረ ሞተለሚ እንኳን ምንም ንጉሥ ቢሆን ማን አለብኝ በሚል ጭፍን ሐሳብ ሩካቤን ይቅርና መዳራትንና መሳሳምን እንኳን በሰው ፊት በአደባባይ ለመፈጸም አልደፈረም። የገዛ ሹማምንቱ የቅዱስ ተክለሃይማኖትን እናት እንዲያገባት ይዘው ባመጡለት ጊዜ "ወሦበርእያ ንጉሥ ተፈስሐ ጥቀ ወተንሥአ ሦቤሃ ወፈቀደ ይስዐማ ወኀደጋ እምፍረሃተ ሰብእ ወተመይጠ ወነበረ ዲበመንበሩ" ይህም ማለት "ንጉሥም ባያት ጊዜ ፍጹም ደስ አለው ። ሊስማት ወደ ፈጥኖ ተነሣ ሰውን ስላፈረ ብቻ ትቷት ተመልሶ ተቀመጠ " ማለት ሲሆን ሞተለሚ ምንም እንኳን እግዚአብሔርን የማይፈራና ሴሰኛ ሰው ቢሆንም የሰውን ገጽ በማፈር ብቻ ማድረግ የፈለገውን ከማድረግ እንደተከለከለ እናያለን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሴሰኞችና አመንዝሮች እንኳን ዝሙትን ብቻ ሳይሆን መዳራትንም በአደባባይ ከማድረግ ከተከለከሉ ሕግና ሥርዓት ያላቸው ክርስቲያኖች ሕጋዊነት ያለውን ሩካቤ እንዴት ባለ ጥንቃቄና በስውር ማድረግ እንዳለባቸው ማብራራት አያስፈልግም። ከዚህ ላይ ማለፍ የማያስፈልገው ይህን መማሪያ ታሪክ የተወልን ሞተለሚ በፍጹም ንስሐ ተመልሶ በአባታችን በአቡነ ተክለሃይማኖት እጅ መጠመቁንና ሥጋወደሙንም መቀበሉ ነው።

ምንም እንኳን በጋብቻችን ቢሆንና ሕጋዊነት ቢኖረንም ሩካቤያችንን በስውር መፈጸም ይገባናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በደጋግ ቅዱሳን ሰዎች መሐከል ይደረጉ የነበሩ ሕጋዊ ግንኙነቶች በጨለማና በኀቡእ(በስውር) ሲፈጽሙ እንመለከታለን። ያዕቆብ ከሕግ ባለቤቱ ከልያ ጋር ተኝቶ ልያ አምስተኛ ልጇን ይሳኮርን በፀነሰች ጊዜ ግንኙነታቸው በሌሊት እንደነበር በግልጽ ተጽፏል። ዘፍ. ፴:፲፭-፲፮ በተመሳሳይ መልኩ የትዕግሥት መምህራችን ጻድቁ ኢዮብ መከራ በጸናበት ጊዜ አፉን ከፍቶ የተወለደበትንና የተፀነሰበትን ዕለትና ሰዓት ሲረግም "ያ የተወለድኩበት ሰዓት ይጥፋ ያም ወንድ ልጅ ተፀነሰ የተባለበት ሌሊት" ኢዮ. ፫:፫ ብሏል። በዚህም ቃል የኢዮብ ወላጆች ለኢዮብ መፀነስ ምክንያት የሆነችውን ሩካቤ ያደረጉት በሌሊት እንደነበር እንረዳለን ሩካቤን በስውርና በምሽት መፈጸም የሚገባው



"ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃኑን ይጠላል።" ዮሐ 3:20 እንደተባለው በሁለት ተጋቢዎች መካከል በሚፈጸም ሩካቤ ክፉነት ወይም ኃጢአት ኖሮበት ሳይሆን ሩካቤ የጋብቻ ምሥጢር ስለሆነ ምሥጢርነቱን ለመጠበቅ ነው።

ማንኛውም ሰው የለበሰውን ልብስ የሚገፈፍበት አጋጣሚ ቢፈጠር በአንደኛ ደረጃ ለመሸፈን የሚጥረው ኀፍረተ አካሉን ነው። አዳም አባታችንም የአምላኩን ትእዛዝ አፍርሶ የጸጋ ልብሱን በተገፈፈ ጊዜ የመጀመሪያ ሥራው በበለስ ቅጠል ለራሱ ግልድም ማገልደም ነበር። ዘፍ. ፫:፯ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉንን በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን" ፩ኛ ቆሮ. ፲፪:፳፫ ይለናል። ታዲያ ኀፍረተ አካላችን እንኳን እንዳይታይ ይህን ያህል ጥንቃቄ የሚደረግ ከሆነ በአባለ ዘራችን አማካይነት የሚፈጸም ተላጽቆ (ግንኙነት) ለማንም በግልጽ እንዳይታይ ምን ያህል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገን ይሆን?

ባል ሚስቱን ስለማክበርና ከነቀፋ ለማዳን ሲል ያለ አስተማሪ በልማድ ብቻ ከሚስቱ ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በግልጽ እንደማይፈጽመው:- "ወዓዲ ኢትገብር ከመዝ በብእሲትከ በእንተ ክብረ ዚአሃ ዘኀቤከ" በማለት ቅዱስ ዮሐንስ የተናገረው ቃል ያስረዳል። ትርጓሜውም "ዳግመኛም ከሚስት ጋራ ሁነህ በአንድነት የምትሠራውን ሥራ ሥጋዬ ናትና አስነቅፋታለሁ ብለህ ባደባባይና በገበያ አትሠራውም" ተግሣፅ 13 ገጽ 153።

በሀገራችን በኢትዮጵያ 'ነውር ነው' በሚል ጥሩ ባሕልና በልማድ ብቻ እንኳን ሩካቤ በአደባባይ እንደማይፈጸም ይታወቃል። ዳግመኛም ልብ ካልን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን?' ፩ኛ ቆሮ. ፲፩:፲፬ እንዳለው ሰዎች ሩካቤን በሚፈጽሙበትና በሚሳሳሙበት ጊዜ ዓይናቸውን መጨፈናቸው (መከደናቸው) ብቻ እንኳን ሩካቤ ከውጭ ላሉ ተመልካቾች ብቻ ሳይሆን ድርጊቱን ከሚፈጽሙት ከራሳቸውም ከእይታ ውጭ መሆን እንዳለበት ያስተምረናል። አዳምን የምትረዳው ሔዋን ስትፈጠርም እግዚአብሔር በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ እንዲወድቅበት ማድረጉ አዳምና ሔዋን ሩካቤያቸውን በምሽትና በስውር መፈጸምእንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። እንቅልፍ የምሽት ተግባር ነውና።

በየአደባባዩ መሳሳምና እንደ እንስሳት መሆን በኢትዮጵያዊ አኩሪ ባሕላችን ብቻ ሳይሆን በሃይማኖታችንም የተወገዘ ነው። ቅንዝረኛ ነትና መዳራት የበዛበት ግልጽ ወሲብ ምንም እንኳን ፈረንጆችና

በሌሎችም አህጉራት የሚኖሩ ሰዎች እንደ ባሕል አድርገው ቢያዙትም እንደ ሥልጣኔ በመቁጠር ግብራቸውን ከመከተል ይልቅ ከነጂ ባሕሎች አንዱ መሆኑን በማስረዳት ድርጊታቸውን አጥብቀን ልንቃወመው ይገባል። ከሁሉ የሚያሳዝነው አኩሪ ባሕልና ሃይማኖት ያላቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን ይህን ርካሽ ተግባር ከሌሎች ቀድሞ በመፈጸም አንደኛ ለመሆን ሲጣጣሩና በዚህም ድርጊታቸው ራሳቸውን እንደ ጥሩ አርበኛ ሲቆጥሩ ማየታችን ነው። አንዳንዶች ደግሞ ምንም እንኳን በፊልምና በትያትር መልክ ለሕዝብ በሚቀርብበት መንገድ ባይሆንም እያመነዘሩ እየተዳሩና እየተሳሳሙ በቪዲዮና በፎቶግራፍ ለመቀረጽ መሽቀዳደማቸውን ስናይ ባሕልና ሃይማኖታችንን የምንወድ ሁሉ ልቡናችን መድማቱ አልቀረም።

ሩካቤን ስውር ማድረግ የሚገባው ድርጊቱን ከምንፈጽመው ከራሳችንም ነው እንጂ ከኛ ውጭ ካሉ ሰዎች ብቻ አይደለም። አዳምና ሔዋን በሠሩት ስሕተት ምክንያት የጸጋ ልብሳቸው በተገፈፈ ጊዜ ከኛ ሌላ የሚመለከተን ሌላ ሰው በዙሪያችን የለም በማለት እንደልባቸው አልሆኑም፤ ከሚጠብቃቸው መልአክ የተነሣ በመፍራትና በማፈር እርስ በእርሳቸውም በመተፋፈር የበለስ ቅጠልን አገለደሙ እንጂ ዘፍ. ፫:፯ ስለዚህ ባልና ሚስትም ቢሆኑ በሩካቤ ጊዜና ከዚያ ውጭ እርስ በእርሳቸው ምልምል ግንድ መስለው ዕርቃናቸውን መተያየት አይገባቸውም። ይህ ድርጊት ለጊዜው የሚያስደስት ቢመስላቸውም እያደር ግን ከባድ መንፈሳዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ያስከትልባቸዋልና።

የባልና የሚስት ግንኙነት በስውር ከብርሃን ውጭ መፈጸም እንዳለበት የሚያስረዳ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል። ይኸውም ቅዱስ ያዕቆብ ወደ ጫጉላው በገባ ጊዜ የተፈጸመ ነው። ያዕቆብ ከሁለቱ የላባ ልጆች ማለትም ከራሔልና ከልያ ራሔልን መርጦ ለማግባት ለአባቷ ሰባት ዓመት ከተገዛለት በኋላ ላባ ሠርግ አደረገ። "በመሸም ጊዜ ልጁን ልያን ወስዶ ለያዕቆብ አገባለት ያዕቆብም ወደ እርስዋ ገባ፤ ... በነጋም ጊዜ እነሆ ልያ ሆና ተገኘች። ላባንም ምነው እንደዚህ አደረግኽብኝ? ያገለገልኩህ ስለ ራሔል አልነበረምን? ለምን አታለልኸኝ ?" አለው ዘፍ. ፳፱:፳፩-፳፯ ላባም ራሔል ታናሽ ናትና ታላቅን አቀይቶ ታናሽን መዳር ሥርዓት አይደለም ብዬ ነው በማለት መለሰለት። ያዕቆብ በጫጉላ ቤት ሳለ አብራው ያለችው ራሔል አለመሆኗን ለመለየት ለምን ተቸገረ? አባቱ ይስሐቅ እርሱን ከኤሳው ለመለየት እንዳቃተው በሽምግልና ምክንያት ዓይኑ ፈዞ ነበር እንዳንል በዚያን ሰዓት ለዐቅመ አዳም የደረሰ ወጣት ነበርና ወይም ሁለት ሴቶች ልጆቹ በየተራ ከእርሱ ጋር ተኝተው ሲነሡ ልጆቹ መሆናቸውን መለየት እንዳቃተው እንደ



ሎጥም ያዕቆብ በስካር አማካይነት ልቡን አላጣም ነበር። ይህ ካልሆነ "ታዲያ ያዕቆብ ልያን ከራሔል መለየት ያቃተው ለምንድን ነው?" መጽሐፍ ቅዱስ ድርጊቱ የተከናወነበትን ጊዜ ሲጠቅስ 'በመሸም ጊዜ' ይላልና ዳግመኛ በእስራኤላዊያን ሙሽሮች ልማድ ተከናንበ በምሽት ወደ ጫጉላ ቤት ስለገባችና ሩካቤ የሚፈጸመው በስውር ስለሆነ ተገላልጣ በብርሃን ስላልተመለከታት ነው ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ሐተታ ብናቀርብም መጨረሻችን ያዕቆብ ልያን ከራሔል መለየት ያቃተው እርሱ አባቱ ይስሐቅን እኔ ኤሳው ነኝ በማለት የታላቅ ወንድሙን በረከት ለመውሰድ ፈልጎ ስላታለለው እግዚአብሔር ብድሩን በዚህ መንገድ ሊመልስለት ስለወደደ ነው። ዘፍ. ፳፯:፩-፴

ንጉሥ ዳዊት በግልጽና በስውር መሥራት ያለበትን ሥራ ለይቶ የሚያውቅ ጥበበኛ ንጉሥ ነበር ለምሳሌ:- ስለታቦተ ጽዮን ክብር በገዛ ሚስቱ እስኪናቅ ድረስ ሲዘምርና ሲያሸበሽብ በግልጽ ታይቷል ፪ኛ ሳሙ. ፮:፲፮ ይህ መሰወር ያለበት ነገር አይደለምና። ሩካቤን ግን በፍጹም ጥንቃቄና በስውር ይፈጽም ነበር። ይህንንም "አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል" ፪ኛ ሳሙ. ፲፪:፲፪ በማለት እግዚአብሔር ዳዊትን የኦርዮ ሚስት በመቀማቱ ምክንያት ሲገሥጸው በተናገረው ቃል መረዳት ይቻላል። ዳዊት ሩካቤውን በስውር ያደረገው ሰርቆ ስላመነዘረ ነው። የሚል ሰው ቢኖር ከሕጋዊ ባለቤቱ ጋር ቢሆን በግልጽ ሩካቤን ይፈጽም ነበርን? በሚል ጥያቄያዊ መልስ አፉን እንዲይዝ ማድረግ ይቻላል። አዎን! ይፈጽም ነበር እንዳይለንም መጽሐፍ ቅዱስ ዳዊትን በአንድም ስፍራ በግልጽ በሚፈጽም ሩካቤ አይተቸውም።

እንዲያውም ንጉሥ ዳዊት ከሚስቱም ጋር ቢሆን እንኳን በምንጣፍ አንድ ሆኖ ይቅርና ተቀምጦም ለመታየት ፈቃደኛ አልነበረም ይልቁንም ዳዊት ነቢያትንና ካህናትን እንደ አባት ያከብራቸው እንደ መምህር ደግሞ ያፍራቸው ስለነበር ከሚስቱም ጋር ተቀምጦ ሊታያቸው አይደፍርም። መጽሐፍ ቅዱስ በ፩ኛ ነገ. ፩:፲፭ ላይ ቤርሳቤህ የዳዊት ሕጋዊ ሚስት ከሆነች በኋላ ስለልጇ ሰሎሞን በዳዊት መንበር መተካት ዳዊትን ለማነጋገር "ቤርሳቤህ ወደ ንጉሥ" እልፍኝ ገባች" ይላል በቁ ፳፪ ላይ ደግሞ "እነሆም ለንጉሡ ስትናገር ነቢዩ ናታን ገባ" ይላል። እዚህ ላይ ነቢዩ ናታን ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር ሳለች ወደ እነርሱ መግባቱን ልብ ይበሉ። ጥቂት ከተወያዩ በኋላ በቁ 28 ላይ ደግሞ "ንጉሡም ዳዊት ቤርሳቤህን ጥሩልኝ ብሎ መለሰ ወደ ንጉሡም ገባች በንጉሡም ፊት ቆመች" ይላል ቤርሳቤህ ከባሏ ከዳዊት ጋር

እየተነጋገረች ነቢዩ ናታን ወደ እነርሱ መግባቱ ተገልጿል። ነገር ግን ገና ነቢዩን ስታይ ፈጥና መውጣቷን ዳዊት በድጋሚ "ቤርሳቤህን ጥሩልኝ" በማለት ያዘዘው ትእዛዝ ያስረዳል። ይህም ንጉሥ ዳዊት እንኳን በወንድና በሴት ግብር ላይ ሆኖ ይቅርና በሌላም ጉዳይ ከሴት ጋር ሆኖ መታየት አይደፍርም ነበር ላልነው በቂ መረጃ ነው። ባልና ሚስት በአንድነት ሆነው አይታዩ የሚል ሕግ በክርስትና ባይኖርም በግላቸውና በስውር ማከናወን ያለባቸውን ተግባር ለማንም ተገልጦ የሚታይ እንዳይሆን የማያቋርጥ ጥንቃቄ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን በብዙ መንገድ ከተጠያቂነት አያመልጡም።

ከላይ እንደጠቀስነው በገሃድ የሚደረግ ሩካቤና መዳራት ምንም እንኳን በትዳራችን ውስጥ ብንፈጽመው ክቡር ገላችንን እንደ እንስሳት ማርከስና ተመልካችንም በመናቅ እንደ ኢምንት መቁጠር መሆኑን ማወቅ አለብን። ስለሆነም ክብራችንን እንዳንጠብቅ ፍትወት ልብ ቢነሣን እንኳን የሚመለከቱንን ሰዎች መናቅ አይፈቀድልንም ዳዊት በንጉሥነት ማዕረግ ተቀምጦ ነቢያትንና መምህራንን አልናቀም ነበርና።

ሰዎች ዕርቃናቸውን ሲጥሉ ዝሙትንና መዳራትን በየአደባባዩ ሲፈጽሙ እግዚአብሔር የተጣላቸው ለመሆናቸው ልዩ ምልክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መቆጣቱንና ፈጽሞ እንደተጣላቸው ለማሳየት ነቢዩ ኢሳያስን ዕርቃኑን እንዲሄድና ትንቢት እንዲናገርባቸው አድርጎታል በተጨማሪም ንጉሥ ዳዊት ሸሽጎ የጎለማሳን ሚስት በመቀማት ባመነዘረ ጊዜ "አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ" ፪ሳሙ. ፲፪:፲፪ በማለት ዳዊት በጎብዕ የጎልማሳ ሚስት በመቀማቱ የእርሱንም ሚስቶችና ቁባቶችን የገዛ ልጁ አቤሴሎም በደፋ እንዲነጥቀው አድርጎታል። በዚህም "በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ" ብሎ በዳዊት ላይ የተናገረውን የጠብ ቃል በገዛ ልጁ እንዲፈጸምበት አደረገ። ዝሙት በአደባባይ ሲወጣ እግዚአብሔር እኛን ለመጣላቱ ምልክት ነው ያልነው ስለዚህ ነው። ከላይ የዘረዘርናቸውን በእንክሮ በማጤን ምንም በሕጋዊ ጋብቻ የምንፈጽመው ቢሆን በስውርና በጨለማ ለተመልካች ሳይጋለጡ ሩካቤን መፈጸምና በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ከልብስ ተራቁቶ ላለመታየት መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ሰብአ ትካት (የቀድሞ ሰዎች) በንፍር ውኃ ከጠፉ በኋላ ከጥፋቱ የተረፈው ኖኅ ከዚያ በኋላ በስካር አማካይነት የሠራው ስህተት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል። ዘፍ. ፱:፳-፳፪ ድርሳነ ሚካኤል ይህን



በይበልጥ ሲያብራራ "ዝ ውእቱ ሚካኤል ዘመሀበ በረከተ ለሴም እም አቡሁ ኖኅ አመ ሰከረ ወይነ ወኖመ ምስለ ብእሲቱ ወተከሥተ ኀፍረቱ ወሰሐቀ ወልዱ ለካም ወሴምስ ከደነ ኀፍረቱ " ይላል ይልቁንም "ወኖመ ምስለ ብእሲቱ ወተከሥተ ኀፍረቱ" በማለት ከሚስቱ ጋር በተኛ ጊዜ ከልብስ እንደተራቆተና ዕርቃኑን እንደጣለ በስውርም አላደረገውምና ልጁ አይቶ ስለሳቀበት እንደረገመው ያትታል።የኖኅ ልጅ ካም ለእርግማን የበቃው በግልጽ በተፈጸመ ሩካቤ ምክንያት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። ስለዚህ ማንኛችውም ባለትዳሮች የሚፈጽሙትን ግንኙነት በስውር ባያደርጉት እንደ ኖኅ ልጅ በመሳቅና በመቀለድ ብቻ ሳይሆን ያለቦታውና ያለጊዜው ፍትወት እንዲቀሰቀስባቸው በማድረግ ተመልካቾቻቸውን ሊጎዱዋቸው ይችላሉ። ይህንንና ሌሎችንም ነጥቦች ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሩካቤን በስውር መፈጸም ብልህነት ነው።

በስሜት የማንረዳቸው ነገር ግን ተገልጸው በዓይነ ሥጋ ስናያቸው በስሜታችን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ የአንድ ሰው የቀዳው ቀለም ጥቁር ወይም ቀይ መሆኑ በሩካቤ ጊዜ ምንም ጫና አይፈጥርም። ነገር ግን የሚስቱን ጥቁረት የማይወድ ባል ሚስቱ ተገላልጣ በግልጽ በምትታይበት ሁኔታ ሩካቤን ለመፈጸም ቢሞክር ስሜቱ ከፉኛ ሊጎዳ ይችላል። ይህን ሐሳብ በሌላ መንገድ ለመግለጽ ሲባል ከመንፈሳዊ ጎዳና እንዳይወጣ በመስጋት ለምሳሌ ይህ ተባለ እንጂ ባልና ሚስት ግልጽልጽ ብለውና በብርሃን እየተያዩ የሚፈጽሙት ሩካቤ የሚፈጥረው ችግር እጅግ ብዙ ነው። ራሔል ያላትን ሴትነት ልያም ምንም ሳታንድል ይዛዋለች። ለዚህም ያዕቆብ ራሔል መስላው አብሯት ከልያ ጋር ማደሩና በምንም ለይቶ ሊያውቃት አለመቻሉ ብቻ በቂ ማስረጃ ነው። ያዕቆብ አብራው ያደረችው ልያ መሆኗን ቢያውቅ ከራሔል ጋር ያደረ መስሎት ያገኘውን ደስታ ባላገኘም ነበር። ምክንያቱም ያዕቆብ ከራሔልና ከልያ ራሔልን አብልጦ ይወዳት ነበርና። ይህም የሆነው ራሔልና ልያ በሴትነት ልዩነት ኖሮባቸው ሳይሆን ራሔል ከልያ ይልቅ ልጅነት ስላላትና ለያዕቆብ ዓይን መልከመልካም ስለነበረች ነበር። በዚያን ሰዓት ያዕቆብ በመኝታ አብራው ያለችው ከራሔል ይልቅ በስሜቱ ዝቅተኛ ደረጃ የሰጣት ልያ መሆኗን አለማወቁ በጊዜው የሚያገኘው ደስታ እንዳይቀንስ እንደረዳው አወቅህን? ምንም እንኳን በባለቤቶቻችን ያለውን ነውረሥጋ እና ደስ የማያሰኙንን ነገሮች ብናውቃቸውም በሩካቤያችን ጊዜ እነርሱን አለማስታወሳችንና አለመመልከታችን ግንኙነታችን በፍቅርና በሙሉ ስሜት ስለሚሆን እጅግ አስደሳች ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ስወር ባለ

ሌላ የምትመኘው ወንድ ነበረ ለማለት እንደፍራለንን? በፍጹም እንደፍርም ምክንያቱም ከሁለቱ ውጪ በምድር ላይ የሰው ዘር ስላልነበረ ከአዳም ሌላ የምትመኘውና ከጎኗ ሊገኝ የሚችል ወንድ አልነበረምና። ይህን ማብራሪያ በአንክሮ በማጤን ከላይ ያሰፈርነውን ሐሳብ ባልና ሚስት ለጸብና ለንዝንዝ መነሻ እንዳያደርጉት አደራችን ጥብቅ ነው።

## በሩካቤ ጊዜ ዘርን ከማኅፀን በአፍአ ማፍሰስ አይገባም

አንድ ገበሬ ለዘር የሚያስቀረው ዘር ለምግብነት ከሚጠቀምበት የተሻለና ምርጥ ዘርን ነው። ስለሆነም ከዘር ወቅት በፊት በጥንቃቄ በረት (በጎተራ) ያስቀምጠዋል። በዘር ወቅት ደግሞ ከጎተራው አውጥቶ በመልካም ማሣ ላይ ይዘራዋል እንጂ እንዲሁ በሜዳ ላይ አይበትነውም። እንደዚሁም ሁሉ ከገበሬ ምርጥ ዘር የሚበልጥ የሰው ዘር ከሩካቤ በፊት በመልካም ጎተራ ማለትም በሰውነታችን ተጠብቆ መቆየትና በሩካቤም ጊዜ በመልካሟ ማሳ በሚስታችን ማኅፀን መዘራት አለበት፤ እንጂ ልጅ ላለመውለድ በሚል ሰበብና በሌሎችም ተገቢ ያልሆኑ ምክንያቶች ክቡር ዘርን እንደ እዳሪ ከማኅፀን ውጭ ያለቦታው ማፍሰስ በትዳራችን የምንፈጽመውን ሩካቤ ሕገወጥ የሚያደርግ ከባድ ወንጀል ነው።

ለእግዚአብሔር በሕይወት ካለን ከኛ ይልቅ የመፈጠር ዕድል የነበራቸው ነገር ግን እኛ በሜዳ ያፈሰስናቸውና በዘርነት በወገባችን የነበሩ ልጆች ይበልጡበታል። ምክንያቱም እኛ ዘራችንን በሜዳ ከማፍሰስ ጀምሮ በኃጢአት ጭቃ ስንጨማለቅ እነርሱ ግን ምንም ካለመበደላቸውም ሌላ ቢወለዱ ጳጳስና ንጉሥ የመሆን ዕድል ነበራቸውና። ስለሆነም ዘራቸውን በምድር ላይ ያፈስሱ የነበሩትን ሰዎች እግዚአብሔር ደግሞ እንደ ኢምንት ስለቆጠሩት ዘራቸው ራሳቸውን ቤዛ አድርጎ ጊዜ ሳይሰጥ ይቀሥፋቸው ነበር። ዘፍ. ፴፰:፱–፲ ይህም የሰው ዘር በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ክቡር እንደሆነ ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ አውናን የተባለ የይሁዳ ልጅ ዘሩን ከማኅፀን በአፍአ (በውጭ) በማፍሰሱ ምክንያት የደረሰበትን መቅሠፍት እንዲህ ሲል ይገልጻል "አውናንም ዘሩ ለእርሱ እንዳይሆን አወቀ ወደ ወንድሙ ሚስት በገባ ጊዜ ለወንድሙ ዘር እንዳይሰጥ ዘሩን በምድር ያፈስሰው ነበር ይህም ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ ሆነበት እርሱንም ደግሞ ቀሠፈው።" ዘፍ. ፴፰:፱–፲ ይህን የመጽሐፍ ማስጠንቀቂያ ልብ በማድረግ በማንኛውም ምክንያት ሕሊናችን እያወቀ በሩካቤ ጊዜ ዘራችንን ከማኅፀን ውጭ ከማፍሰስ መጠንቀቅ አለብን።



## ሩካቤን በቁም (በመቆም) መፈጸም

የእግዚአብሔር ነቢይ ዳዊት "በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጉሟቸው ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።" መዝ. ፴፩:፱ በማለት ሰውን ሁሉ ይመክራል የሰው ልጅ በባሕርየ ሥጋ ምንም እንኳን እንስሳትን ቢመስልም በአንፃሩ ደግሞ መላእክትን የምታስመስለው ነፍስ በውስጡ ስለምትገኝ በኑሮው ሁሉ እንስሳትን መምሰል የለበትም። እንስሳት እንደተወለዱ ወዲያውኑ በእግራቸው ቀጥ ብለው መቆምና መንቀሳቀስ ይችላሉ። ይህም ለመወለዳቸው ምክንያት የሆነው ሩካቤ በቁም(በመቆም) መፈጸሙን ያመለክታል። እንስሳት ግንኙነታቸውን ቆሞ ለመፈጸም ምቹ ተፈጥሮ ስላላቸው ድርጊታቸውን የሚቃወም መጽሐፋዊና ተፈጥሮአዊ ሕግ የለም። የሰው ልጅ ግን ሩካቤን በመቆም እና በመቀመጥ እንዳይፈጽም ተፈጥሮው ምቹ ካለመሆኑም ሌላ የእግዚአብሔር ሕግ አይፈቅድለትም።

የሰው ልጅ በተወለደ ጊዜ ወዲያውኑ በእግሮቹ ቀጥ ብሎ መቆምና መንቀሳቀስ አይችልም ይህም ለእርሱ መወለድ ምክንያት የሆነው የእናቱና የአባቱ ግንኙነት በመተኛት እንደተፈጸመ (መፈጸም እንደነበረበት) እንዲሁም የማንኛውም ባልና ሚስት ሩካቤ በመኝታ መፈጸም እንዳለበት ያመለክታል። ይህ የራሳችን ተፈጥሮ ከሚያስተላልፍልን ትምህርት በተጨማሪ የአዳም ረድኤት ሔዋን ስትፈጠር እንዴት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ "እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ዘፍ. ፪:፳፩" ይላል። እግዚአብሔር አዳምን ካስተኛውና ከባድ እንቅልፍ ከጣለበት በኋላ ሔዋንን መፍጠሩ ግብራቸው (ግንኙነታቸው) በመተኛት መፈጸም እንዳለበት ሥርዓት ለመሥራት ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ "ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይሆናሉ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል።" ሉቃ. ፲፯:፴፬ በማለት የባልና የሚስት በግብር መተዋወቅ የሚፈጸመው በመኝታ መሆኑን ገልጾ ነገር ግን ከሁለቱ አንዳቸው በድንገት በሞት መነጠቃቸው ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ምልክት እንደሆነ ነግሮናል። በሌላም ስፍራ ነቢዩ ናታን ስለኦርዮ ሚስት በበግ እየመሰለ ለዳዊት በነገረው ጊዜ "በብብቱም ትተኛ ነበር" ፪ኛ ሳሙ. ፲፪:፫ በማለት ገልጿል። በመጽሐፍ ቅዱስ በአንድም ስፍራ ሩካቤን እንደ እንስሳት ቆመው የፈጸሙ ሰዎች ታሪክ አናገኝም።

## ሩካቤና ስካር

በተጋቡ ሰዎች መካከል የሚፈጸም ሩካቤ ስካር ማብረጃ አለመሆኑን ማወቅ አለብን። ሲጠጡና ሲሰክሩ ብቻ ማግባታቸውን የሚያስታውሱ ከስካር ውጭ ግን ሚስቶቻቸውን ፈጽመው በመኝታ የማያውቋቸው ባሎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ይህ ደግሞ ለትዳር ሰላም ትልቅ እንቅፋት ነው። ምክንያቱም መጠጥ ባልጠጣንበት ሰዓት የጠጣና የሰከረ ሰው አፍ እንዴት እንደሚሸተንና እንደሚጎፈንነን ካወቅን አንዲት ሴት ልቡን ካጣ ሰካራም ጋር ተቃቅፋ ማደሯ እንዴት እንደሚቀፍ ለመገመት አያስቸግርም። በተጨማሪም በተለያዩ አደንዛዥ ዕፅዎችና በሚያሰክር መጠጥ ወይም በሌሎች ኬሚካላዊ ይዘት ባላቸው ንጥረ ነገሮች ምክንያት ፍትወት እንደ ረመጥ ከሚፈጀው ሰው ጋር በነዚህ የሥነ ምግባር ጉድለቶች ተጠቅታ የስሜት ጉዳት የደረሰባትና የተቀየመችን ሴት በአንድ አልጋ አስማምቶ ለማኖር መሞከር እሳትና ውኃን በአንድ ጋን አስማምቶ ለማኖር እንደመድከም ያለ ነው። ስለዚህ ምንም እንኳን ለአንዴና ለሁለተኛ ጊዜ ያለችግር በስካር ከባለቤቶቻችን ጋር ብናድር ለወደፊት ግን መንቀል የማንችለውን የጥላቻ እሾኽ በትዳራችን ላይ እየተከልን መሆኑን አውቀን በስካር ከሚፈጸም ሩካቤ መቆጠብ አለብን።

የተጋቡ ሰዎች የሚፈጽሙት ሩካቤ ሕጋዊ ነው። ነገር ግን በትዳራቸውም ቢሆን የሚፈጽሙት ድርጊት ከሥርዓት ውጭ ከሆነ ከትዳራቸው ሳይወጡ መፈጸማቸው ብቻ ከጥፋተኝነት ነፃ አያወጣቸውም ስለሆነም ያለምንም ይሉኝታና ፍራቻ ተገቢውን ሩካቤ መፈጸም አለብን። ይህንንም ያለመጠጥ ድጋፍ ማድረግ ይገባል።

አንዳንድ ሚስቶች ባሎቻቸው በሩካቤ ሰዓት ተገቢ ያልሆነ ቁጥብነት ሲያሳዩዋቸውና እንደ ልባቸው የማያገኟቸው ሲሆኑ ቁጥብነታቸውን አስወገደው እነርሱ እንደሚፈልጉት እንዲሆኑላቸው የባሎቻቸውን መጠጣትና መስከር ይመኛሉ። ወደኋላ የሚያዝኑበት ነገር እስኪከሠት ድረስ በዚህ ድርጊታቸው ደስተኞች ናቸው። ሰዎችን በማስከር ከእነርሱ የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚደረግ የተሳሳተ ጥበብ ሁለቱ የሎጥ ልጆችን አባታቸው ሎጥ ጎሊናው እያወቀ በምንም መንገድ አብሮአቸው እንደማይተኛ አውቀው ካጠጡና ካሰከሩት በኋላ በየተራ አብረውት እንዲተኙና ከአባታቸው እንዲፀንሱ ካስተማራቸውና ከእርጉዝ ሚስቱ ጋር በሩካቤ ለማሳደር አርዮን ማስከር ቀዳሚ ሥራው መሆን እንዳለበት ዳዊትን ካነሣሣው ሰይጣን የተቀዳ ነው። የዚህ ዓይነት ሙከራ ስካር ሲለመድ የሚያስከትለውን ችግር ሳያጠኑ የሚሞከር ነውና ሚስቶች ባለቤታቸውን በማስከር ከባሎቻቸው የሚፈልጉትን ለማግኘት ከመሞከር ይልቅ ባሎቻቸው ለምን



ወደ ኋላ እንደሚያፈገፍጉባቸው በማጥናት መፍትሔ ለማግኘት ቢሞክሩ ብልህነት ነው።

ስካር በቁሙ ኃጢአት ከመሆኑም በላይ ሰዎችን ወደ ዝሙት በመውሰድ ተፎካካሪ ያልተገኘለት ነገር መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ይቻላል። ዘፍ. ፲፱:፴፫ ፤ ምሳ. ፳፫:፴፫ ስለሆነም በጤናማ አእምሮ መብታቸው የሆነ ሩካቤን ለመፈጸም ያልቻሉ ሰዎች በመጠጥ ኃይል ታግዘን እንሞክር ቢሉ ካሰቡት ውጭ ወደ ጥፋት መንገድ ሊወስዳቸውና የከፋ ስሕተት ላይ ሊጥላቸው ይችላል። ስካር ወደ ዝሙት የሚመራ ዐቢይ ነገር ከሆነ ባለትዳሮችን ልቅ ወሲብ እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል ቢባል ምንም አያስደንቅም። ለምሳሌ ኖኅ በሰከረ ጊዜ ልጁ ሊያየው በሚችልበት ዓይነት ሁኔታ ከሚስቱ ጋር ተኝቷል። ባይሰክር ግን ይህን ባላደረገም ነበር። ኖኅ በመጠጥ አማካይነት በሕግ የማይደገፍ ግልጽ ሩካቤን እንደፈጸመ ሁሉ ትውልዳችንንም መጽሐፍ በማይፈቅደውና ተፈጥሮ በማይደግፈው ጎብሩ ብዙ በሆነ የሩካቤ መንገድ ሲያሯሩጠው ይገኛል። የሚያስደንቀው ደግሞ ይህ የረከሰ ተግባር ከሰይጣን መገኘቱን ሳይረዳ እንደ ጥበብ ሲማረውና ሲከታተለው መገኘቱ ነው። በዚህም "ለእከይስ ጠቢባን እሙንቱ" "ለክፋት ግን ጥበበኞች ናቸው" የተባለው የመጽሐፍ ቃል በራሱ ላይ እንዲፈጸም ያደርጋል።

መቅደስ ለሕጋዊ ሚስት ምሳሌ ስትሆን ካህን ደግሞ ለሕጋዊ ባል ምሳሌ ይሆናል ስለሆነም ካህን ሲሾም ከመቅደስ ጋር ተጋቡ ይባላል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ካህን በምንም ምክንያት መጠጥ ጠጥቶ ወደ መቅደስ መግባት እንደሌለበት ያዛል። ዘሌ. ፲:፱። ሚስት በመቅደስ ባል ደግሞ በካህን እንደሚመሰሉ መጻሕፍት ያመሰጥራሉ። ታዲያ ካህን ጠጥቶ ወደ መቅደስ መግባት ከተከለከለ ባል ሰክሮ ከሚስቱ ጋር ሩካቤን መፈጸም እንደ[illegible]ነበት አያሳይምን? ስለዚህ ሰው ሆይ ሰውን ያህል ክቡር ፍጥረት የሚፈጠርበትን ታላቅ ሥራ ለሥጋ በመገዛትና በማን አለብኝነት በቸልታ አትሥራ "የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ ርጉም ይሁን።" ኤር. ፵፰:፲ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ፍራ።

ምንም በትዳራችን ቢሆን በስካር የሚፈጸም ሩካቤ ትርፉ ጸጸት ውጤቱ ጥፋት ነው። የአስቆሮቱ ይሁዳን ለምሳሌ ብንወስድ ዕንባቆም የተባለ ነቢይ በመንገድ ሲያልፍ የይሁዳ አባት እንደ ባልንጀሮቹ አክብሮ ላለመነሣት ገጹን በምናምን ሸፍኖ እንዳልታየ ሰው አርፎ በተቀመጠ ጊዜ ንቀቱን የተረዳ ነቢዩ ዕንባቆም "ዕብን ዲበ ዕብን ነቢሮ" ማለትም"ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተቀምጧል ከዚህም ሰው የሚወለደው

ገላቸን እንደ ገል እስኪደርቅ ድረስ ፍትወት ብናበዛ ሕግ ተላላፊዎች ነን። ሩካቤ እንደ ገበጣና ሰንጠረዥ ጫወታ ፣ሩጫና ውኃ ዋና እንደ ነፃ ትግልና የእግር ኳስ ጫወታ ተጋጣሚን ለማሸነፍ የሚፎካከሩበት የፍራሽ ሜዳ ሳይሆን በስምምነት አንዳችን የአንዳችንን ደስታ በማየት የምንረካበት መንፈሳዊ ሥርዓት ያለው ዓለም ነው። ስለዚህ ተሸነፍን በማለት እልክ ውስጥ ሳንገባ በመልካም ጨዋነትና በተገቢ ቁጥብነት ፈቃዳችንን መፈጸም ይገባናል።

## ሩካቤና የአምስቱ ሕዋሳቶች ትይዩነት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በኀቱም ድንግልና ተወልዶ ዓለምን ለማዳን የመጣ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን በተለያየ ምክንያት ብዙዎች እንዳላመኑበት በምሳሌ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል:- "አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ በእራትም ሰዓት የታደሙትን አሁን ተዘጋጅቷልና ኑ እንዲላቸው ባሪያውን ላከ ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር። የፊተኛው መሬት ገዝቻለሁ ወጥቼም ላየው የግድ ያስፈልገኛል ይቅር እንድትለኝ እለምንሀለሁ አለው። ሌላውም አምስት ጥማድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው። ሌላውም ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው።" ሉቃ ፲፬:፲፮–፳ በዚህ ታሪክ "ታላቅ እራት ያደረገው አንድ ሰው" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ታዳሚዎቹም ሰብአ ዓለም (በዓለም ያሉ ሰዎች) በሙሉ ናቸው። 'ታላቅ እራት' የተባለውም ጥሪም ሰዎች ሁሉ ጌታችን ያለዘር ያለ ሩካቤ መወለዱን እንዲያምኑ መጠራታቸውን የሚያመለክት ነው። ሆኖም ሁሉም በተለያየ ምክንያት ጥሪውን አክብረው አልተገኙም። እንዲያውም አንደኛው በጥሪው ያልተገኘበትን ምክንያት ሲያቀርብ "አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ" በማለት ነበር። ይህም ሲፈታ አንተ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ በኀቱም ድንግልና ተፀንስሁ በድንግልናም ተወለድሁ እመኑብኝ ትላለህ እኔ የማውቀው ደግሞ ፍሬ የሚገኘው ማሣ በጥምድ በሬዎች ታርሶ ዘር ተዘርቶ እንደሆነ ሁሉ የሰው ልጅም የሚገኘው በአምስቱ በሬዎች የሚመስሉ አምስቱ የባልና የሚስት ሕዋሳት ተጠምደው ተጋጥመው በሚፈጸም ሩካቤ ነውና ይቅር በለኝ በልደትህ አላምንም እንደማለት ነበር።

እኛ ክርስቲያኖች ምንም እንኳን ከላይ እንደገለጽነው ሰው የሚወለደው በአምስቱ ጥምድ በሬዎች የሚመስሉ አምስቱ የወንድና የሴት ሕዋሳት ተጠምደው (አንድ ሆነው) በሚፈጸም ሩካቤ አማካኝነት



እንደሆነ ብናውቅም ጌታችን ግን አምላክ እንደመሆኑ መጠን በግብረ መንፈስ ቅዱስ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በኀቱም ድንግልና እንደተወለደ እናምናለን።

"አምስት ጥማድ በሬዎች ገዝቼአለሁ" የሚለው አረፍተ ነገር ፍቹ ልጅ ለመውለድ በባልና በሚስት መካከል ለሚፈጸም ተራክቦ ትክክለኛ ምሳሌነት አለው። ይህንን ቃል በመናገር በጌታ እራት ላይ ላለመገኘቱ ምክንያት የሰጠው ሰው የተሳሳተው የጌታን ልደት እንደ ማንኛውም ሰው (ዕሩቅ ብእሲ) ልደት አድርጎ በመቁጠር ጌታን ያለዘር ያለሩካቤ በድንግልና መወለዱን ስላላመነ ነው እንጂ "አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ" በማለት ለሩካቤ በሰጠው ምሳሌያዊ ገለጻ አይደለም። ይህ ዐረፍተ ነገር በወንድና በሴት መካከል ለሚደረግ የተፈጥሮ ሕግንና የመጽሐፍ ሥርዓትን የጠበቀ ሩካቤን በትክክል መግለጽ የሚችል መንፈሳዊና ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው። ስለዚህ በዚህ ቃል መሠረት በባልና በሚስት መካከል ሩካቤ መፈጸም ያለበት ትይዩ በመሆንና አምስቱ ሕዋሳቶቻቸውን አንድ በማድረግ ነው።

ቅዱስ መጽሐፍ የሚደግፈው ተፈጥሮአዊ የሩካቤ አፈጻጸም ባልና ሚስት ፊት ለፊት (ትይዩ) ሆነው የሚፈጽሙትን ነው። በዚህ ጊዜ እያንዳንዱ ሕዋሳቶቻቸው በተቃራኒ ጾታ ካለው ባለቤታቸው አካል ላይ በተገቢው ቦታ ማረፍ አለበት እንዲህ ከሆነ አምስቱ ሕዋሳቶቻቸው ማለትም አፍ ከአፍ፣ እጅ ከእጅ፣...ጋር አንድ ይሆናሉ (ይጋጠማሉ)። ከዚህ የወጣ የሩካቤ አፈጻጸም ግን ከሰይጣን የተገኘ ነው።

እንስሳት ሩካቤ ሲያደርጉ ፊትና ኋላ በመሆን ነው። የሰው ልጅ ግን ከእንስሳት ይለያልና ትይዩ ሆኖ ሩካቤን ይፈጽማል። ብዙ እንስሳት እንደተወለዱ ዓይናቸውን አይገልጡም (አያዩም) ይህም ለፅንሰታቸውና ለልደታቸው ምክንያት የሆነው ሩካቤ ባለመተያየት (ፊትና ኋላ በመሆን) መፈጸሙን ሲያመለክት የሰው ልጅ ደግሞ እንደተወለደ ወዲያውኑ ዓይኑን መግለጡና ለማየት መቻሉ ምንም እንኳን የተፈጥሮ ነገር ሆኖ በሩካቤ ጊዜ ዓይንን መጨፈን(መክደን) ባይቀርም ሴትና ወንድ ትይዩ ሆነው ተራክቦ እንደሚያደርጉ ያመለክታል።

## ሩካቤና ሥርዓት አልባ እንቅስቃሴ

እስክንድስ በአርምሞ የታወቀ ጻድቅ አባት ነው። ለመንፈሳዊ ትምህርት አንቱ ዘንድ ሄዶ ሳለ አባቱ ይሞታል ትምህርቱንም እንደጨረሰ ወደ እናቱ ለመመለስ ሲያስብ መምህሩ ባሏ ስለሞተ እስከ አሁን እናትህ ሌላ ወንድ ትለምድ ይሆናል። አብሮ መኖር አይሆንልህምና አትሂድ እዚሁ ተቀመጥ አለው። እርሱ ግን የእኔ እናት

አታደርገውም በማለት ከመምህሩ ጋር ሙግት ገጠሙ። በመጨረሻም መምህሩ መሄዱን ሂድ ነገር ግን ወንድ ሲርቃት የሴት ባሕርይዋ ደካማ ነውና እናትህን ፈትናት ብሎ አሰናበተው። እስክንድስም እናቱ ዘንድ ተመለሰ። ወደቤት ሳይገባ እንደውጭ ሰው ሠራተኛዋን አባብሎ እመቤትዋን እንድትጠራለት ላካት ሄዳም ይህን የሚመስል ሰው ሊያናግርሽ ከደጅ ቆሟል ብላ አድንቃ አወራችላት። እመቤቲቱም እንዲህ ያለ ነገር ልማዴ ነውን? ስትል በያዘችው ምናምን እናቷን ብላ ሰደደቻት። በዚህ መንገድ ያልሆነለት እስክንድስ የመሸበትና በመንገድ ዝናብ የያዘው ሰው መስሎ ወደ ቤት ገባና ተጠለለ። ልጇ መሆኑን ያለወቀች እመቤትም በእንግዳ መልክ አስተናገደችው። ቆይቶም በገናውን አሳምሮ ይደረድረው ጀመር። እመቤቲቱም ማድነቅ ያዘች ገረዲቱም መግቢያ ስታገኝ ቀድሞም ይፈልግሻል ያልኩሽ ሰው ይህ ነበር። አሁንም በእጅሽ ነውና የወደድሽውን አድርጊ አለቻት። ከዚህ በኋላ በዘዴ ቀርበው መጫዋወት ጀመሩ በዚህ መንገድ ሐሳቡ የተሳካለት እስክንድስ ፈተናውን ከግብ ለማድረስ እናቱን ወደ መኝታ ይዟት ወጣ። ተኝተው ሳሉ የማይደርስባት ሆነ ለፈተና እንጂ ሩካቤን ሽቶ አልመጣምና። እርሷ ወደታች ስትተኛ እርሱ ወደላይ ወደላይ ስትሆን ደግሞ ወደታች እየሆነ አስቸገራት። በመጨረሻም ምነው ፈቃዴን ሳትፈጽም ትጫወትብኛለህ? ሥርዓትስ ለምን ለወጥክብኝ። አለችው። ከባሏ ጋር ሳለች እንዲህ ያለ እንቅስቃሴ አይታ አታውቅምና። እርሱም ፈተናውን ፈጽሟልና እናቴ ነሽና በወጣሁበት አልገባም ብዬ ነው በማለት በግልጽ ነገራት። እርሷም ልጇ መሆኑን ስታውቅ ከማንም ጋር ቢሆን ይኸው ነበርኩኝ ይህ ደግሞ ከዚያ ይባስ ብላ ታንቃ ሞታለች። እርሱም እናቱን የገደለው አንደበቴ ነው በማለት እስኪሞት ድረስ ከፉና ደግ ሳይናገር ኖሯል። ታሪኩን ስንጀምር በአርምሞ የታወቀ ጻድቅ አባት ነበር። ያልነው ለዚህ ነው።

ከላይ የጠቀስናት ሴት በመኝታ ጊዜ ያልለመደችውን ነገር ስትመለከት መመርመሯን ልብ ማድረግ ይገባናል። በዚህም ላይ አብሯት የተኛውን ወንድ ወደ ለመደችውና ወደምታውቀው ሥርዓት ለመመለስ ጣረች እንጂ የፈለገው ቢሆን ምን አገባኝ በማለት በቀጥታ ወደ ሩካቤ አልሮጠችም። ከባሏ ውጭ ሩካቤን ለመፈጸም መነሣቷ ኃጢአት ቢሆንም ሥርዓት አልባ ሩካቤን ከመፈጸም መቆጠቧና መመርመሯ ግን ያስደንቃታል በዚህ መልኩ ከትዳራቸው ውጭ ዝሙትን የሚፈጽሙ ሰዎች እንኳን ከመጽሐፍ ሕግና ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጭ የሚፈጸም ሩካቤን ከተቃወሙ ሕጋዊ ሩካቤን በጋብቻቸው የሚፈጽሙ ባለትዳሮችማ እንዴት የሥርዓት ሰው መሆን ይጠበቅባቸው ይሆን? ልጂም ቢሆን ጻድቅ ነውና የማያደርገው ስለሆነ



የመኝታ አቅጣጫውን እያዞረ ፈተናት እንጂ ሩካቤን ለመፈጸም አስቦ ቢሆን ኖሮ እንዲህ እንደ እንዝርት ራስ በመኝታው ላይ ባልተሽከረከረም ነበር።

እንግዲህ እኛ ባለትዳሮች በመኝታችን ላይ ያልለመድነውን ከሥርዓት የወጣ አዲስ ነገር ስንመለከት መመርመር እልፍም ሲል መቃወም ይገባናል እንጂ እንደ አሻንጉሊት አንዳችን ለአንዳችን መዝናኛና መጫወቻ ሆነን መቅረብ የለብንም። በትዳር መሀከል የሚፈጸመውን ሩካቤ አንዱ አካል ብቻውን የመቃወም መብት የለውም የተባለው በተገቢ መንገድ የሚፈጸመውን ሩካቤ ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው አይከላከሉ ለማለት ነው እንጂ የተጋቡ ሰዎች ከሥርዓት ውጭ የሆነ ተራክቦ መፈጸም ይችላሉ ለማለት አይደለም። ስለዚህ እያንዳንዱ ባለትዳር በትዳር ጓደኛው የሚፈጸመውን እንቅስቃሴ ተመልክቶ ከመሥመር የወጣውን ድርጊት የመቃወም መብት አለው። ሐዋርያው "ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ።" ፩ኛ ቆሮ. ፭:፱ ብሎናልና እንዲያውም ባንቃወም በተባባሪነት መወቀሳችን አይቀርም።

## ሩካቤና የባልና የሚስት ትብብር

የጋብቻ ዋና ዓላማ መተባበር ነው። ስለሆነም ባልና ሚስት በሁሉም ነገር ይተባበራሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሩካቤንም መተባበር ይለዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከጋለሞታ ጋር ዝሙትን የሚፈጽም ለማለት "ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንደሚሆን አታውቁምን።" ፩ኛ ቆሮ. ፮:፲፮ ይላል። በሌላም ስፍራ በእሪት "በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" በማለት የተጻፈው ቃል በአዲስ ኪዳን "ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁሉቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" የሚል ትርጓሜ ይዞ ተቀምጧል። ዘፍ. ፪:፳፬ ፤ ማቴ. ፲፱:፭ ፤ ማር. ፲:፯ 'ይጣበቃል' የሚለው የባልና የሚስትን ግንኙነት የሚያሳይ ቃል 'ይተባበራል' በሚል መተርጎሙ ሩካቤ መተባበር እንደሚባል ያረጋግጣል።

ሩካቤ ባልና ሚስት በባሕርያቸው ያለውን ክበደ ፍትወት ለማቃለል የሚተባበሩበት መንገድ ሲሆን ራሱ ሩካቤም በመተባበር የሚፈጸም እንጂ በአንድ ወገን ብቻ የሚከናወን ተግባር አይደለም። 'መተባበር' የሚለው ቃል ራሱ ትግግዙ በሁለቱም አቅጣጫ መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ሚስቶች በሩካቤ ጊዜ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው ለባል በመተው ድርሻቸውን አይወጡም። ይህም ማለት እነርሱ ቢታቀፉ እንጂ ባላቸውን

አያቅፉትም ባላቸው ቢስማቸው እንጂ እነርሱ አንጻራዊ መልስ አይሰጡትም ወይም አይስሙትም ማለት ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ እንኳን እነርሱ ደርሰው ባላቸውን ሊያቅፉትና ሊስሙት ይቅርና መታቀፍና መሳም እንዳለባቸው እየተሰማቸው እንኳን ባላቸውን አቀፈኝ ሳመኝ በማለት ለመናገር ዳተኞች ናቸው።

ይህ ዓይነቱ የቤቶች ዐመል የባልን ስሜት ሊጎዳና በረከስ የወሲብ እንቅስቃሴ ስልጥነዋል ወደሚባሉት ጋለሞቶች እንዲሄድ ሊያነሣሣው ወይም 'እኔ ምንድር ነኝ' በማለት የፈቀደውን ከማድረግ ወደኋላ እንዲል ሊያርገው ይችላል። በምንም ነገር ትብብር ሳያደርግ ሁሉን በጽሞና የሚከታተል ሰው ታዛቢ ይመስላልና። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ ችግርም ከመከሠቱ አስቀድሞ ለሩካቤ በተዘጋጁበት ጊዜ ሚስቶች በቃልና በድርጊት ተገቢውን ትብብር በማድረግ ድርሻቸውን መወጣት አለባቸው። ይህን በማድረጋቸው ሕጋውያን ናቸውና ቅዱስ መጽሐፍም አይነቅፋቸውም።

ሚስቶች ለባሎቻችን ያለንን ፍቅር የምናሳየው ባሎቻችን በሰውነታችን ላይ ያላቸውን ሙሉ መብት እንዲጠቀሙ ራሳችንን አሳልፈን በመስጠት ብቻ ሳይሆን በእነርሱም ሰውነት ላይ ያለንን ሙሉ መብት በመጠቀም መሆን አለበት። ይህን ሐሳብ ማንሣት ያስፈለገው ብዙ ባሎች ሚስቶቻችን በሩካቤያችን ጊዜ ቀዝቃዞችና ቸልተኞች ይመስሉናል በማለት እሮሮ ስለሚያሰሙ ባለማወቅና በሽቁጥቁጥነት ሚስቶች የሚያሳዩት ተገቢ ያልሆነ ቁጥብነት በእውነተኛ የቤተክርስቲያን ትምህርት አስወግደ ከባሎቻቸው ጋር መልካም ስምምነት እንዲፈጥሩ ለማድረግ ነው።

## ከሩካቤ በኋላ ምን ማድረግ ይገባል?

"ውሻ በበላበት ይጮኻል" ይባላል። ብዙ ሰዎችም እንዲሁ ናቸው። ለተደረገላቸው ነገር የፍቅርና የምስጋና ቃል ከአፋቸው አይወጣም። በአንጻሩ ንቀትና ጥላቻን በሚያሳይ ቃልና ድርጊት ብድራቸውን ይመልሳሉ። ይህን ዓይነት ድርጊት በባልና በሚስት መካከል መፈጸም የለበትም ይልቁንም መመስገን እንጂ ።

አምኖን ትዕማርን ወደዳት ምን ሊያደርጋት እንደሚችልም በዓይኑ ፊት እጅግ ጭንቅ ሆነበት ስለ እርሷም ብዙ ስለተከዘ ካሣ ታመመም። ይህን ያህል የተሰቃየላትን ሴት አንድ ቀን በግድ ይዞ አስነወራት። ከእርሷም ጋር ተኛ ከዚህ በኋላ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠቅስ "አምኖን ፈጽሞ ጠላት አስቀድሞ ከወደዳት ውድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በለጠ። አምኖንም ተነሥተሽ ሂጂ አላት እርሷም ቀድሞ ከሠራኸው ክፋት ይልቅ አኔን በማውጣትህ የበለጠ ክፋት ትሠራለህ



አለችው። እርሱ ግን አልሰማትም የሚያገለግለውንም ብላቴና ጠርቶ ይህችን ሴት ከፊቴ አስወጥተህ በሩን ዝጋባት አለው . . አገልጋዩም አስወጥቶ በሩን ዘጋባት።" ፪ኛ ሳሙ. ፲፫:፲፭–፲፰።

ሩካቤን ከፈጸምን በኋላ ሚስቶቻችን ወይም ባሎቻችን እንዳረከሱን በመቁጠር እዳሪ እንደነካው እንጨት ለመንካት እንኳን መጸየፍ ምንኛ ስሕተት ነው? ሩካቤን ከፈጸሙ በኋላ አብሮን የተኛውን አካል ሸለብ እስኪያደርገው ድረስ እትፍ ድግፍ በማድረግ ፋንታ መገፍተርና ጀርባን መስጠት ከግመንዘር ያውም እህትን አስገድዶ ከመድፈር የሚከፋ ነው። ይኸውም አምኖን እህቱን አስገድዶ ከደፈራት በኋላ በስም እንኳን ሳይጠራት አገልጋዩን ጠርቶ ይህችን ሴት ከፊቴ አስወጥተህ ዝጋባት ባለ ጊዜ እርሷ "ቀድሞ ከሠራኸው ክፋት ይልቅ እኔን በማውጣትህ የበለጠ ክፋት ትሠራለህ" በማለት መናገሯ በግድ ይዟት ከመድፈሩ የበለጠው የአምኖን ክፋት የልቡን ከፈጸመ በኋላ የፀሐይ ምች ያጣፋት ብሎ ከነደሟ ከቤት አስወጥቶ ማባረሩ እንደሆነ ያስረዳል።

እንደ አምኖን ያሉ ሴሰኞችና አመንዝራዎች እንኳን ዝሙታቸውን ከፈጸሙ በኋላ አብሯቸው ለተኛው አካል ሰብአዊ ክብሩን ጠብቀው እንክብካቤ አለማድረጋቸው መጨረሻ የሌለው ክፉነት መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ከላይ በጠቀስነው መልክ ከተገለጸ የባልና ሚስትን ተፋቅሮና ተከባብሮ መኖር በቀደምትነት ባጸደቀች እውነተኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔር እንዴት ያለ(ች) ባል (ሚስት) ሰጠኝ መሰላችሁ! በማለት ሲፎክሩ ከርመው የተጋቡ ሰዎች ከሩካቤያቸው በኋላ ለትዳር ጓደኛቸው ምን ዓይነት እንክብካቤና ፍቅር ማሳየት ይገባቸው ይሆን?

## ሩካቤን የት መፈጸም ይገባል?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን አፀድ ውስጥ መፈጸም የሌለበትን ድርጊት ሲፈጽሙ ያገኛቸውን ሰዎች ሲወቅስ "የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን?" በማለት ተናግሯል። ፩ኛ ቆሮ ፲፩:፲፪ ሰዎች መብልንና መጠጥን እንኳን ያለበቂ ምክንያት ከቤታቸው ውጭ እንዳያደርጉት ከመከረ በሰውር መከናወን ያለበት የባልና የሚስት ሩካቤ እንዴት ይልቅ በቤት ውስጥ ብቻ መፈጸም ይገባው ይሆን?

ሰይጣን ሰዎችን ከማሳሳት አያርፍምና በጠንቋዮች በመስሀታን (አሳሳቾች) ላይ አድሮ "አንቺ ከዲያቆን ወይም ከመነኩሴ ጋር ካልተኛሽ በቀር መፈወስ (ልጅ መውለድ) አትችይም" እያለ ሰዎችን ለጥፋት

እንደሚያነሣሣቸው ሁሉ ባለትዳሮችንም “እዚህ ቦታ ሄዳችሁ ብትገናኙ ትወልዳላችሁ” በማለት በቤተክርስቲያንና በቅዱሳት ገዳማት ሩካቤያቸውን እንዲፈጽሙ ሊልካቸው ይችላል። ይህ ዓይነቱ ድርጊት የሰይጣን ሥራ መሆኑን ካወቅን ምንም እንኳን ጠንቋይን ባንጠይቅና ከእርሱም ባንታዘዝ በቤተክርስቲያን ውስጥ ከባለቤቴ ጋር ብተኛ ምን አለበት እንደውም ቅዱስ ቦታ ስለሆነ እግዚአብሔር የተባረከ ልጅ ይሰጠኛል የሚል ሐሳብ ወደ ኅሊናችን ሲገባም ከሰይጣን የተገኘ ሐሳብ መሆኑን ማወቅ አለብን።

አዳምና ሔዋን ተፈጥረው በገነት ውስጥ ለሰባት ዓመት ከሁለት ወር ሲኖሩ አንድም ቀን እርስ በእርስ በገነት ውስጥ በሩካቤ አለመተዋወቃቸውን መጽሐፍ ይነግረናል። ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩትም አንዱና ዋነኛው ምክንያት ገነት የቤተክርስቲያን አምሳል በመሆኗ በየዘመኑ የሚነሱ ሰዎች ቤተክርስቲያንን በማቃለል በውስጧ ፈቃደ ሥጋቸውን ለመፈጸም እንዳይደፋፈሩ ትምህርት ለመስጠት ነው። ቤተክርስቲያን አፀደ ነፍስ ናትና። በነፍስ ደግሞ ፍትወተ ሥጋ የለባትም በተጨማሪም በመንግሥተ ሰማያት ሰዎች እንደ መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡም ማቴ. ፳፪:፴ ቤተክርስቲያንም የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ስለሆነች ምንም እንኳን የጋብቻን ቅዱስነትና የነፍስ በረከት ለሥጋ መትረፉን ለማመልከት የጋብቻ ሥርዓታችን የሚፈጸመው በቤተክርስቲያን ቢሆንም በግብር መተዋወቃችን ግን በውስጧ አይፈጸምም።

በመኻታችን ስናልም አድረን ስአበት(ርኩሰት) ሲያገኘን ወደ ቤተመቅደስ ለመግባት የማይፈቀድልን ከሆነ ሩካቤ ከቤተክርስቲያን ምን ያህል መራቅ እንዳለበት መገመት ይቻላል። የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ መቅደሰ የሆነ ሰውነታቸውን ማሳደፋቸው ሳይበቃቸው በመገናኛው ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉ ሴቶች ልጆች ጋር በመተኛታቸው አባታቸው ዔሊ ይህን የእርግማን ነገር ማድረጋቸውን እያወቀ እምቢ አላችሁ ልጆቼ ከማለት ብቻ በቀር የወሰደው ምንም ዓይነት እርምጃ ባለመኖሩ እግዚአብሔር በፍርድ ተነሥቶ ታቦተ ጽዮን እንድትማረክ ሲያደርግ አፍኒንና ፊንሐስንም በአንድ ቀን ጦርነት እንዲወድቁ አድርጓቸዋል። ኃጢአታቸውን በቸልታ ያለፈ አባታቸው ዔሊንም በዚያው ዕለት ወድቆ እንዲሞት አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ “የዔሊ ቤት ኃጢአት በመሥዋዕትና በቁርባን ለዘለዓለም እንዳይሠረይለት ምያለሁ” ፩ኛ ሳሙ. ፪:፲፬ በማለት ራሱ እግዚአብሔር በቤተክርቲያን የሚደረግ ዝሙት ምን ያህል ለቁጣ እንደሚያነሣሣው ገልጾልናል። ፩ኛ ሳሙ. ፪:፲፩-፴፮ ፤ ፫:፲፪-፳፩፤ ፬:፩-፳፪።



እግዚአብሔር ለቤቱ ቀናተኛ ነው። በቤቱ ይሸጡና ይለውጡ የነበሩ ሰዎችን ባየ ጊዜ ጅራፍ ገምዶ እየገረፈ ካስወጣና ገበታቸውን ከገለበጠ እኛ በቤቱ እንደ አሊና ባዝራ እጅ ለእጅ ተያይዘን ብንዛለልና ብንዳራ ብንሰስንም ምን ዓይነት ረቂት የመቅሠፍት ጅራፍ እንደሚያበጅብን በዓይነ ሕሊና መመልከት አለብን። ዮሐ. ፪:፲፭ ማቴ. ፳፩:፲፪ የጸሎትና የመሥዋዕት ቤቱን የምንዝርና የዝሙት ጎሬ ማድረግ ፍጹም ተገቢ አይደለም።

አዳምና ሔዋን ከስሕተታቸው በኋላ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ሱባኤ ይዘው እግዚአብሔርን በሚለምኑበት (ደጅ በሚጠኑበት) ጊዜ ቦታ ለይተው እንደነበር በመጻሕፍት እናነባለን። ከዚህም በመነሣት “ምጽላዩን ለአንስት ለባሕቲቶን” “ምቅዋምን ለአንስት ለባሕቲቶን” እየተባለ ሥርዓት ተሠራ ይህም ቃል በጸሎት ጊዜ የሴቶች መቆሚያና መጸለያ ስፍራ የተለያየ መሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናቸው ባልና ሚስት አብረው መኖር እንዳለባቸው ከመከረ በኋላ በጸሎት ጊዜ ግን መለያየት እንዳለባቸው ጨምሮ ጠቅሷል። ፩ኛ ቆሮ. ፯:፭። ፍትሕ መን. በአንቀጸ ጸሎት “ወለእመ ኮነ ምስለ ብእሲቱ ፪ሆሙ ይጸልዩ ኅቡረ” “ሚስት ያለችው ሰው ቢሆን ሁለቱም አንድ ጊዜ ይጸልዩ” የሚለውን ቃል ሲተረጉም ባልና ሚስቱ ባለጸጋ ቢሆኑ እርሱ ከአዳራሽ እርሷ ከእልፍኝ ሆነው ደሃ ቢሆኑ እርሱ ከጉበኑ እርሷ ከማጀት ሆነው ይጸልዩ። በማለት ባልና ሚስት በቦታ ተለያይተው መጸለይ እንዳለባቸው ያስረዳል። ይህም ሥርዓት መንፈሳዊ ተልዕኮአችንን ከሕሊና ሁከት ነጻ ሆነን ለመፈጸም ያግዘናል። ሐዋርያት ከሴቶች ጋር በአንድነት ይጸልዩ የነበረው የባሕርይ ፆር ጠፍቶላቸው ስለነበር ነው። የሐዋ. ፩:፲፬።

ጻድቁ ኖኅ ወደ መርከብ በገባ ጊዜ ሌላው ዓለም የጠፋበትን የዝሙት ተግባር ልጆቹ በመርከብ ውስጥ ሳሉም እንዳይደግሙት በመስጋት ወንዶች ልጆቹንና ሚስቶቻቸውን በአንድነት እንዳይሆኑ ለያይቷቸዋል። ምንም ሚስቶቻቸው ቢሆኑ የኖኅ መርከብ የቤተክርቲያን አምሳል ናትና ኖኅ ልጆቹ በመርከቧ ውስጥ ሳሉ በሩካቤ እንዲተዋወቁ አልፈቀደም። እኛም ኖኅን አብነት በማድረግ “መቅደሴን ፍሩ እኔ እግዚአብሔር ነኝ” ዘሌ. ፳፮:፪ በማለት ያስጠነቀቀንን አምላካችንን በመፍራት በቤተክርስቲያን ዓፀድ ዙሪያ ፈቃዳችንን ከመፈጸም መቆጠብ አለብን።

እንዲሁም እንደ ኖኅና ቤተሰቦቹ በባሕር ላይ በሚንዝ መርከብ ወይም በአየር በሚበር አውሮፕላን፣ በየብስ በሚሽከረከር

አውቶሞቢልና እንደ አቅማችን በጋማ ከብት በሚሳብ በጋሪ በምንሄድበት ጊዜ ከሆነልን በጋሪ ሲጓዝ ትንቢተ ኢሳያስን ይጸልይ እንደነበረው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ እንደ ገርሳሞት ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበብንና እየጸለይን ʼየሐዋ. ፰:፳፰ ካልሆነልንም በጨዋ ደንብ ተሰብስበን ካሰብንበት መድረስ ይገባናል። እንጂ እንደ ከብት በየመንገዱ መፋነን መዳራትና መሰስን አይገባንም። በየመንገዱ መሰስን እንዳማይገባ ቅዱስ ዳዊት "በእውነት ከወጣን ጀምረን እኛ ሰውነታችንን ከሴቶች ሦስት ቀን ጠብቀናል" ፩ኛ ሳሙ. ፳፩:፭ ያለው ቃል ያስረዳናል። ስለዚህ መጓጓዣ መኪናችንን ተንቀሳቃሽ መኝታ ክፍል በማድረግ በየመንገዱ እየተዳራን የተመልካች ሰዎችን ልቡና ማቁሰልና እግዚአብሔርን ማሳዘን ወቀሳና ቅጣት ያስከትልብናል። ምንም ባለትዳሮች ብንሆን ተግባራችን በገዛ ቤታችን መወሰን አለበት። ይህ ልማድ በትዳራችን አለመተማመንን ከመፍጠሩም በላይ ዕድሉን ስናገኝ ከትዳራችንም ውጪ ቢሆን በጀ አይሉንምና።

እስራኤላዊያን በመተተኛው በለዓም አቀናባሪነት በተዘጋጀው የተንኮል መረብ ተይዘው ለጣዖት በሰገዱና ከአሕዛብም ጋር ባመነዘሩ ጊዜ ዘንበሪ የተባለ እስራኤላዊ ከስቢ የተባለች ምድያማዊትን ተሸክሞ ወደ መገናኛው ድንኳን ካገባት በኋላ ከእርሷ ጋር ተኛ። በዚህ ጊዜ ፊንሐስ የተባለ የካህኑ የዓልአዛር ልጅ የድንኳኑ አውታር ሲነቃነቅ አይቶ ተከትሏቸው ቢገባ ዘንበሪና ከስቢ እርስ በእርስ ተያይዘው አገኛቸው። ለእግዚአብሔር ፍጹም ቅናት ቀንቶ ወደ ቤተ እግዚአብሔር በስእለት አማካይነት በገባ ጦር በሚሠራሩባት አንድ አድርጎ ወጋቸው። "ወረገዛ ማዕከለ ኀፍረታ" ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው። ዘዳ. ፳፭:፩-፱ ፣ ሠለስቱ ሐዲሳት ትርጓሜ። እግዚአብሔርም በፊንሐስ ሥራ ፍጹም ደስ አለው። ሰው እንደገደለም አልቆጠረበትም የጠመመን እንደማቅናት የጎደለን እንደመሙላት አየለት እንጂ። እግዚአብሔርም ከቁጣው ተመልሶ ለፊንሐስ ለዘለዓለም በክህነት ያገለግለኝ በማለት ቃል ኪዳን ሰጠው። በዚያም ዕለት በመቅሠፍት የሞቱት ሰዎች ቁጥር ሃያ አራት ሺህ ነበር። እንደ ፊንሐስ ሕይወታችንን ሙሉ እግዚአብሔርን በማገልገል መኖር ከፈለግን ራሳችንን ከዚህ ዓለም እድፍ መጠበቅና ለቤቱም በመቅናት የገዛ ሰውነታቸውንና ዓፀደ ቤተክርስቲያንን ለማሳደፍ የሚንቀሳቀሱትን ሰዎች እንደ ፊንሐስ በጦር ልንወጋቸው ክርስትናችን ባይፈቅድም በተቻለን ሁሉ መቃወምና መገሠጽ ይጠበቅብናል። በእግዚአብሔር ቤት ማመንዘር ቅሠፈኝ ብሎ እንደመጸለይ ነው። በተጨማሪም የጸሎት ቤታችንም ቤተ ጸሎት ናት እንጂ ሩካቤ ሥጋ



የሚፈጸሙበት አይደለችምና ሳናቃልላት ለጸሎት ብቻ በእግዚአብሔር ፊት እንቁምባት።

## ምዕራፍ ፭

## የተጋቡ ሰዎች ከሩካቤ የሚታቀቡባቸው ዕለታት

እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለው። የጠዋቱን ግታ የማታውን ጠዋት አይሠራም። ይህም ማለት የሠራውን ደግሞ መሥራት አይችልም ማለት ሳይሆን ማንኛውንም ነገር ከመደበኛ ጊዜው አሳለፎ ወይም አስቀድሞ አይሠራም ማለት ነው። ይህም እመቤታችን "የወይን ጠጅ የላቸውም" ባለችው ጊዜ 'ጊዜዬ ገና አልደረሰም' በማለት ተአምር የሚያሳይበት ጊዜ አለመድረሱን ባመለከተበት ቃል ይታወቃል። እንደዚሁም ሁሉ የሰው ልጆች ፈጣሪያቸውን አብነት አድርገው ሁሉን ነገር በወቅቱ መፈጸም አለባቸው። ሁሉም ነገር ጊዜና ወቅት አለውና ጠቢቡ ሰሎሞንም "ለሁሉም ጊዜ አለው" ብሏል። መክ. ፫:፩ ፤ ዮሐ. ፪:፫–፬።

በተጋቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሩካቤ የሚፈጸምባቸውና የማይፈጸምባቸው ጊዜያት አሉ። በተገቢ ጊዜ የሚፈጸም ሩካቤ ጌታ ጊዜው በደረሰ ጊዜ ወደ ወይንነት የለወጠው ውኃ ጣዕሙ ከቀደመው ወይን ይልቅ የተወደደ እንደነበር እንዲሁ ያለጊዜው ከሚፈጸም ሩካቤ የተወደደ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም ራስን መውቀስና የሕግ ተላላፊነት መንፈስ አይሜነውምና። በሕግ ተወስኖ በተከለከለ ወቅት ሩካቤን መፈጸም ግን ጊዜው ያልደረሰና ያልበሰለን ፍሬ እንደመመገብ ያህል ጣዕም አይኖረውም።

ምንም እንኳን በቀን አትጠጡ የሚል ሕግ ባይኖርም ብዙ ሰዎች በቀን አይጠጡም። ይህም መልካም ነውና መጽሐፍ ይደግፈዋል። ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ በተለያዩ ብሔረሰቦች ቋንቋ ስለተናገሩ ከሰሟቸው ሰዎች ጥቂቶቹ ቃላቸውን ቢያምኑም ሌሎች ብዙዎቹ ግብዞች ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለወይን ጠጅ በመስጠት ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው የሆነ ያልሆነውን ይዘላብዳሉ። በማለት ሐዋርያትን ነቀፈዋቸዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ በመካከላቸው ቆሞ ለትችታቸው መልስ ሲሰጥ እንደምናውቀው "ገና ከቀኑ ሦስት ሰዓት አይደለምን?" በማለት በቀን አይሰክርምና ሐዋርያት ሰክረው ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ ቋንቋ ገልጾላቸው እየተናገሩ እንደሆነ የነቢዩ ኢዩኤልን ትንቢት ጠቅሶ አስረድቷል። የሐዋ. ፪:፩–፲፰ ወይን ጠጅ ላለመጠጣት እንደዚህ ጊዜ የሚጠበቅለት ከሆነ እንዲሁ በትዳራችን ለምንፈጽመው ሩካቤም ጊዜውን ልንጠብቅለት ይገባናል።

ለሩካቤ ጊዜ የማይወሰንለት ቢሆን ኖሮ በሕፃንነታችን ወቅትም ሩካቤን ለመፈጸም ብቃት በኖረን ነበር። ነገር ግን ስለሩካቤ ማሰብና መመኘት እንኳን የሚፈጠርብን በአሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ስንገኝ ነው። ይህም ሩካቤ የሚፈጸምበትና የማይፈጸምበት ጊዜና ወቅት እንዳለው ያመለክታል። ሥርዓት በመከተል በተገቢው ጊዜ የሚፈጸም ሩካቤ የተባረከ ልጅ እንደሚገኝበትና ዕለቱም ምስጉን እንደሚሆን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ "አይ ይእቲ ዕለት ዕለተ ሩካቤሆሙ ንጽሕት እንተባቲ ሐንበበት ፍሬ ቡርክተ ድንግልተ እስራኤል ኢጽዕልተ" "ነውር ነቀፋ የሌለባት የእስራኤል ድንግል የተባረከች ፍሬ ያፈራችበት (ያበበችበት) ንጽሕት ሩካቤያቸው የተደረገችባት ይህች ዕለት እንደምን ያለች ናት?" በማለት ሐና እና ኢያቄም ጊዜውንና ሥርዓቱን ጠብቀው በንጽሕና የፈጸሙት ሩካቤ እመቤታችን ድንግል ማርያምን እንዳስገኘና ያችም ዕለት ክብርት እንደሆነች ተናግሯል። አርጋኖን ዘዓርብ።

አንድ ገበሬ ዘር የሚዘራበትንና የማይዘራበትን ወቅት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት ይህን ሳያውቅ ቀርቶ ወይም በቸልተኝነት ያለ ጊዜው ዘርቶ ቢሆን ከድካምና ከኪሣራ በቀር የሚያገኘው ትርፍ የለም። እንደዚሁም ሁሉ በገበሬ የሚመሰል ባል በመልካም እርሻው በሚስቱ ላይ የሚዘራው ዘር አስደሳች እንዲሆን ጊዜውን አይቶ ሊዘራ ይገባዋል። በትዳር የሚፈጸም ሩካቤ ጊዜ አለውና መጽሐፍ ቅዱስ "ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው።" መክ. ፫:፭ በማለት ሩካቤ በሕርስ፣ በትክት፣ በአጽዋማት፣ በዓበይት በዓላትና በሰንበታት እንደማይፈጸምና እንደሁኔታው ታይቶ ከነዚህ ውጭ ባሉ ቀናት የሚፈጸም መሆኑን ገልጸልናል።

## ሴቶች በሕርስ ወይም በትክት ላይ እያሉ ሩካቤን መፈጸም ክልክል ነው።

መዋዕለ ሕርስ:- አንዲት ሴት ልጅ ከወለደች በኋላ የወለደችው ወንድ ከሆነ ዐርባ ቀን ሴት ከሆነች ደግሞ ሰማንያ ቀን እስኪሆናት ድረስ ያለው ጊዜ መዋዕለ ሕርስ ይባላል። ዘሌ. ፲፪:፩ መዋዕለ ትክት የሚባለው ደግሞ ሴት ልጅ ከአርግዝና ጊዜ ውጭ በየወሩ ቀን ጠብቆ የሚፈሳት ደም ከመጣባት ዕለት ጀምሮ እስከተቋረጠበት ድረስ ያለው ጊዜ ወይም በሌላ ቃል የወር አበባ ወቅት የምንለው ነው።

ሴቲቱ በእነዚህ ሁለት ወቅቶች ማለትም በሕርስና በትክት ውስጥ እያለች ባልና ሚስት ሩካቤ መፈጸም አይፈቀድላቸውም። ከላይ በጠቀስናቸው ሁለት ወቅቶች የሚፈጸም ሩካቤ የሚወለደውን ሕፃን ጨምሮ የባልና የሚስቱን ጤና ሊጎዳ እንደሚችል የሃይማኖት



መጻሕፍቶቻችን ያውጃሉ። ይህን የጤና መቃወስ ብንተወው እንኳን በነዚህ ዕለታት የሚፈጸም ሩካቤ አስፀያፊና ስሜት አልባ ስለሚሆን ስለ ራሳችን ሕሊና ብለን ልንተወው ይገባናል።

የሰው ልጅ ዘር ክቡር ነው። ሴት ልጅ በትክት (በወር አበባ) ላይ ሳለች ሩካቤን መፈጸም ክቡር ዘርን እዳሪ ከሆነ ደም ጋር መቀላቀል ነውና ትልቅ ኃጢአት ነው። በሕርስ ጊዜ ደግሞ ለብዙ ወራት ለመውለድ ይዘጋጁ የነበሩ ሕዋሳቶቿ ወደ ቀደመ ይዞታቸው ተመልሰው ሩካቤን ለመፈጸም ዝግጁ አያደርጓትምና በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚፈጸም ሩካቤ የሁለቱንም ስሜት የሚጎዳ ነው።

ንጉሥ ዳዊት ከሰው ሚስት ጋር በመፈጸሙ ድርጊቱ ቢነቀፍም ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋር በምንጣፍ በተገናኘ ጊዜ ከወር አበባዋ ነጽታ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይጠቅሳል "ዳዊትም መልክተኞችን ልኮ አስመጣት ወደ እርሱም ገባች ከርኩሰትዋም ነጽታ ነበርና ከእርሷዋ ጋር ተኛ ወደቤቷም ተመለሰች ሴቲቱም አረገዘች" ፪ኛ ሳሙ. ፲፩:፬ "ከርኩሰትዋም ነጽታ" ነበር ያለው የወር አበባዋን ነው። ስለምን ቢሉ ደመ ትክቶ(የወር አበባ) በኦሪት የእርግማን ምልክት ነበርና። ዘፍ. ፫:፲፮ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዓይነት አገላለጽ ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር የተገናኘችበትን ጊዜ መግለጽ የፈለገው ሴቶች ከወር አበባ በነጹበት ጊዜ ከወንድ ጋር ቢገናኙ ወዲያው ፅንስ ይይዛሉና በአንድ ጊዜ ፅንሰች ብሎ ለማስከተል ሲሆን በተጨማሪም ሩካቤ ከወር አበባ ጊዜ ውጭ የሚፈጸም እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሴት ልጅ በትክት (በወር አበባ) ላይ እያለች የሚፈጸም ሩካቤን ሲከለክል እንዲህ ይላል። "እርሷዋም በመርገምዋ ርኩሰት ሳለች ኃፍረተ ሥጋዋን ትገልጽ ዘንድ ወደ ሴት አትቅረብ።" ዘሌ. ፲፰:፲፱ ይህንን ሕግ ተላልፎ ኃጢአት የሠራ ሰው ስለሚገባው ቅጣት ሲናገር ደግሞ "ማንኛውም ሰው ከባለ መርገም ሴት ጋር ቢተኛ ኃፍረተ ሥጋዋንም ቢገልጥ ፈሳሽዋን ገልጧልና እርሷም የደምዋን ፈሳሽ ገልጣለችና ሁለቱ ከሕዝባቸው መካከል ተለይተው ይጥፉ።" ዘሌ. ፳:፲፰ ይላል። ትክቶ(የወር አበባ) ምንም እንኳን በአዲስ ኪዳን መርገም ወይም ርኩሰት ባይባልና በዚህም ወቅት ሩካቤን የሚፈጽሙ ሰዎችም እንደ ኦሪቱ በድንጋይ ተወግረው በእሳት ተቃጥለው እንዲጠፉ ባይፈረድም ሕግ ስላፈረሱ በመንፈሳዊ ቅጣት (በቀኖና) መቀጣታቸው አይቀርም። በወር አበባ ወቅት የሚፈጸም ሩካቤ በአዲስ ኪዳንም ክልክል ነውና።

## በእርግዝና ወቅት ሩካቤ ክልክል ነው።

ሴት ልጅ እርጉዝ ሆና ሩካቤ በጣም አደገኛ ነው። ምክንያቱም በፅንስ ወቅት የሚደረግ ሩካቤ የፅንሱን አቀማመጥ እንዲዛባ በማድረግ በፅንሱና በእናቲቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የጤና መታወክ ሊያስከትል ስለሚችል ነው። ከዚህም ሌላ በመንፈሳዊ ዓይን ለተመለከተው ሴቲቱ ሴት ፅንሳ እንደሆነ እናትና ልጅን በአንድ ጊዜ እንደመገናኘት ሲሆን ፅንሱ ወንድ ከሆነ ደግሞ ግብረ ሰዶም እንደመሥራት ነውና በፅንስ ወቅት የሚደረግ ሩካቤ በሃይማኖት ፈጽሞ የተወገዘ ነው።

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በሙሉ ባለማወቅ እንኳን ከእርጉዝ ሴት ጋር በምንጣፍ እንዳይገናኙ በረቂቅ መንገድ ይጠብቃቸዋል። ይህም በኦርዮ ይታወቃል። የኦርዮ ሚስት ቤርሳቤህ ከንጉሥ ዳዊት ጋር ባመነዘረች ጊዜ በአንድ ጊዜ ሆዷ ፅንስ ለመያዝ ታድሎ ነበርና አረገዘች። እንደ ብልህ ሴቶች ቀኗን በመቁጠርና እርግዝናን ተከትለው የሚከሠቱ ምልክቶች ማለትም የሴቶች ልማድ መቅረት፣ የጡት መጥቆር፣ የሆድ መግፋት፣ የከንፈር ማረርና ጺቅ ጺቅ ማስኘት (ማቅለሽለሽ) በራሷ ላይ ማየት ስትጀምር ማርገዟን አውቃ ከፍርድ የምትድንበትን መላ እንዲፈጥር ለፅንሱ ባለቤት ለዳዊት ላከችበት በኦሪት ያመነዘረች ሴት በድንጋይ ተወግራ ትገደል ነበርና። ዘሌ. ፳:፲ ፤ ዘዳ. ፳፪:፳ ፤ ዮሐ. ፰:፭ ዳዊትም ፅንስ ለማሳሳትና ያንተ ነው ለማለት ባሏ ኦርዮን ከዘመተበት የጦር ሜዳ በዘዴ አስጠራውና ከሚስቱ ጋር እንዲያድር ለማድረግ ሞከረ ኦርዮ ግን ወደ ሚስቱ አልገባም። ፪ኛ ሳሙ. ፲፩:፲፩ ይህ ታሪክ እንደ ዳዊት ንጉሥ እስከመሆን ደርሰን ሹመት ቢኖረን እንኳን እግዚአብሔር አውቆ ካላለፈን በቀር ኃጢአታችንን በችሎታችን መሰወር እንደማንችል ከማስተማሩም በላይ እግዚአብሔር በእርግዝና ወቅት ከሚፈጸም ሩካቤ ሰዎችን እንደሚጠብቅ ያሳያል። ኦርዮ ካረገዘች ሚስቱ ጋር አልተኛምና። እንዲህ ከሆነ ሕሊና እያወቀ በእርግዝና ወቅት ከሚፈጸም ሩካቤ ምን ያህል መሸሽ ይገባን ይሆን?

## ክርስትና በማንሣት ጊዜ ሩካቤ አይፈቀድም።

ይህ ንዑስ ርእስ የክርስትና አባትና እናት ስለሚሆኑ ሰዎች የሚናገር ነው። እነዚህ ሰዎች ባለትዳሮች ከሆኑ ክርስትና ከማንሣታቸው በፊት ለሁለት ቀን ክርስትና ካነሡ በኋላም እንዲሁ ለሁለት ቀን በመዓልትም በሌሊትም ቢሆን ከሩካቤ መጠበቅ(መከልከል) አለባቸው። ይህንንም የሚያደርጉት ስለክብረ መንፈስ ቅዱስ ነው። ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ዕጣን አጥኖ ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ ለሁለት ቀን ከሚስቱ ጋር እንዳልተገናኙ ማለት ነው። መጽሐፋችን "ወእምድኅረ ፪ኤ መዋዕል



ፀንሰት ኤልሣቤጥ ብእሲቱ" ማለትም "ከሁለቱ ቀናትም በኋላ ኤልሣቤጥ ፀነሰች" ሉቃ. ፩:፳፬ በማለት የጠቀሰው ይህንኑ ነው። ስለዚህ ክርስትና በሚያነሱበት ጊዜ ከላይ ለተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ያህል ከሩካቤ መከልከል ያስፈልጋል።

## ወደ ቤተክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ ሩካቤ አይፈቀድም።

እግዚአብሔር ሕግጋትን ለሙሴ በሚሰጥበት ጊዜ ግርማውን አይተው በመፍራት እንዲያመልኩትና አገልጋዩ ሙሴንም እንዲያከብሩት ሕዝቡን ሁሉ ወደ ሲና ተራራ ይወጡ ዘንድ በጠራቸው ጊዜ ልብሳቸውንና ሰውነታቸውንውን እንዲያጠቡ ተነግሯቸው ነበር። ዳግመኛም ሙሴ መላልሶ እንደቀደሳቸውና "ለሦስተኛውም ቀን ተዘጋጁ ወደ ሴቶቻችሁም አትቅረቡ" የሚል ትእዛዝ እንዳስተላለፈላቸው እናነባለን። ዘፀ. ፲፱:፲፭ እግዚአብሔር ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ለተገለጸበት ለሲና ተራራ ከሚስቶቻቸው እስኪለዩ ድረስ ይህን ያህል ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ከታዘዙ ዕለት ዕለት ሥጋውና ደሙ የሚፈተትባት፣ ሕገ ወንጌል የሚነገርባትና እግዚአብሔር በመዓልትና በሌሊት የማይለያት ቅድስት ቤተክርስቲያን የበለጠ ዝግጅት እንደሚያስፈልጋት አውቀን ክብሯን በማቃለል ከሚስቶቻችን ጋር በሩካቤ አድረን በቤተመቅደስ ለመቆም መድፈር የለብንም።

በእመቤታችን የተአምር መጽሐፍ የተጠቀሰው ታሪክም አስቀድመን የገለጽነውን ሐሳብ ይደግፍልናል። ይኸውም ጠዋትና ማታ ደጇን በመክፈትና በመዝጋት ቤተ እግዚአብሔርን በማገልገል የሚተጋ አንድ ሰው ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ከሴት ጋር ድቀት አገኘው ሲነጋም እንደለመደው ደጃፏን ለመክፈት ወደቤተ እግዚአብሔር ገሠገሠ የእግዚአብሔር መልአክም በዘንግ ነካ አድርጎ እንዳይገባ ከለከለው። የት እንዳደርህ ዘንግተህ ባይሆንና በድፍረት ፈጽመኸው ቢሆን እንደ አክርማ ለሁለት በሰነጠኩህ ነበር። ነገር ግን ዕንቡዝ ልብ ሆነህ መጥተሃልና ተመለስ ብሎ አሰናበተው። የእግዚአብሔር መልአክ ይህንን ሰው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ከመግባት የከለከለው ስላመነዘረ ብቻ ሳይሆን ከሚስትም ጋር ቢሆን በምንጣፍ ተገናኝቶ ወደ ቤተክርቲያን መሄድ ክልክል ስለሆነ ነው። ስለዚህ 'እኔ መቼ አመነዘርኩኝ?' እያልን ራሳችንን በነፍስና በሥጋ ጉዳት ላይ ከመጣላችን በፊት ለሥርዓተ ቤተክርቲያን ተገዢ መሆን አለብን።

**በዓበይት በዓላትና በሰንበት ሩካቤ ክልክል ነው።**

ባልና ሚስት በዐበይት በዓላትና በሰንበት በምንጣፍ ከመገናኘት መራቅ አለባቸው በዚህም ልጆቻችንን 'የሰንበት ጥንስስ' ተብሎ ከመሰደብ ማዳን ብቻ ሳይሆን እኛም ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ በሚገኝ ጸጋ እንከብራለን። ዓበይት በዓላት የሚባሉት ዘጠኙ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓላት ሲሆኑ እነርሱም ብሥራት፣ልደት፣ ጥምቀት፣ ደብረ ታቦር፣ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት እና ጰራቅሊጦስ ናቸው። በእነዚህ ዕለታትና በሰንበት ሩካቤ የተከለከለበት ምክንያት በመጀመሪያ ሰንበት ለዘለዓለም ዐርፈን ለምንኖርባት ለመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ስለሆነችና በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ፈቃደ ሥጋን መፈጸም ማግባትና መጋባት ስለሌለ ምሳሌነቱን ለማጽደቅ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከባለቤት ጋር በሩካቤ አድሮ በቤተመቅደስ በድፍረት መቆም ሥርዓት ስላልሆነ ዘፀ. ፲፱:፲፭ ፈቃዳችንን በመፈጸማችን ምክንያት ወደ ቤተ እግዚአብሔር ከመሄድ ተከልክለን በዕለተ ሰንበትና በበዓላት በዝተው ከሚፈጸሙ መንፈሳዊ ሥርዓቶች ተሳታፊ ሳንሆን በመቅረታችን ከበረከት እንዳንራቆት ነው።

ነገር ግን ብዙ ሰዎች ኪሳቸው የሚያብጠውና የዕረፍት ጊዜያቸውም ሰንበት በመሆኑ በቀላሉ በመዲናችን በየዕለቱ ከሚፈጸሙት የፆታ ግንኙነቶች በሰንበት ዕለት የሚፈጸመው ብዙውን እጅ ይዞ ይገኛል። በአንድ አጋጣሚ ከብዙዎች አንዱን ብቻ በማንሣት ከተነበበ ዘመናዊ የጥንቆላ ጋዜጣ (አስትሮሎጂ) ከአሥራ ሁለቱ ኮከቦች የአምስቱ የጥፋት ትንበያ እንዲህ ይል ነበር "በዚህ ሳምንት የፍቅረኛዎ ጋር መዝናናት ቢያምርዎ ቅዳሜ ምሽትን ይምረጡ የወደዱትንም ከማድረግ ወደ ኋላ አይበሉ፤ ጥሩ ምሽት እንደሚሆንልዎና ምንም ችግር እንደማያጋጥምዎት እርግጠኛ ይሁኑ" ይህ ሐሰተኛ ትንቢት ፍቅረኛ ከተባለ (ካላገባነው) ሰው ጋር ምንም ሳንጨነቅ ዝሙት እንድንፈጽም ከመምከሩም በላይ ሰንበትን እንዳናከብር እና በቀጣዩም የሰንበት ቀን መንፈሳዊ በረከት በሚገኝበት ሥፍራ እንዳንገኝ አሳፋሪ ሥራን እንዳመለከተን ማወቅ ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ተከልክለን ሰንበትን ማክበር እንዳለብን እንዲህ ሲል ይገልጽልናል "ፈቃድህን በተቀደሰው ቀኔ ከማድረግ እግርህን ከሰንበት ብትመልስ፣ ሰንበትንም ደስታ፣ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው፣ የገዛ መንገድህንም ከማድረግ ፈቃድህንም ከማግኘት ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው፣ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል፤ በምድር ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ፣ የአባትህንም የያዕቆብ ርስት አበላሃለሁ። የእግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና።" ኢሳ. ፶፰:፲፫–፲፬ በማለት ሰንበትን ማክበር እንዳለብን ብቻ ሳይሆን እንደታዘዝነው ሰንበትን ብናከብር



የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ ርስት የምትባል መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያወርሰን ቃል ኪዳን ገብቶልናል። ሰንበትን ስናከብርም "ፈቃዳችንን ከማድረግ እግራችንን በመመለስ" እና "የገዛ መንገዳችንንም ከማግኘት" ተከልክለን መሆን እንዳለበት ጨምሮ ገልጾታል። ስለዚህ ፈቃደ ሥጋን በሰንበት ከመፈጸም ተቆጥቦ ሰንበትን ማክበር ታላቅ ዋጋ አለው።

**ባልና ሚስት ሥጋ ወደሙን ከመቀበላቸው በፊት ለሦስት ቀናት ከሩካቤ መከልከል አለባቸው።**

የእስራኤል ልጆች ከሚስቶቻቸው ጋር ሩካቤ ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር ወደሚገለጥበት ተራራ እንዳይወጡ በተከለከሉት መሠረት እኛም ሩካቤን ፈጽመን ወደ እውነተኛይቱ ተራራ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳንገባ ሥርዓት ተሠርቷል። ይህ ከሆነ በቅድስት ቤተክርስቲያን ብቻ የሚፈተተውን የአምላክ ሥጋና ደም ለመቀበል ለምን ያህል ጊዜ ከሩካቤ ተቆጥበን መቅረብ ይገባን ይሆን? ዘፀ. ፲፱:፲፭።

እግዚአብሔር ንጉሥ ዳዊትን ለመቅጣት ወደ በልጁ በአቤሴሎም ምክንያት ከዙፋኑ ወርዶ እንዲሰደድ ባደረገው ጊዜ በረሀብና በጥም ስለተቸገረ የሚበላ ነገር ሲሻ ወደ ካህኑ አቤሜሌክ ዘንድ ሄዶና አንዳች የሚበላ ነገር እንዳለ እባክህ ፈልግልኝ ሲል ተማጸነ። ካህኑም አንዳች ነገር እንኳን የለኝም። ነገር ግን ካህናት ብቻ ሊበሉት የተፈቀደ ኅብስት (መሥዋዕት) አለኝ አለው። በረሀብ ከምንሞት አይፈቀድምን? በማለት ካህኑን ባማከረ ጊዜ ንጹሐን ከሆናችሁ ተፈቅዷል ሲል መለሰለት። ዳዊትም ቀጠል አድርጎ እኛ ባሮችህ ከቤት ከወጣን ጀምሮ ሦስት ቀን ሙሉ በመንገድ ነበርንና ከሚስቶቻችን ጋር አላደርንም በእኛም ዘንድ ያሉ ብላቴኖች ንጹሐን ናቸው። በማለት ተናገረ ፩ሳሙ. ፳፩:፩–፮ ካህኑ አቤሜሌክም የመሥዋዕቱን ኅብስት ሰጥቷቸው ከበሉ በኋላ መንገዳቸውን ቀጠሉ መሥዋዕት አሪትን ለመመገብ ከሚስቶቻቸው ጋር ለሦስት ቀን ከሴት ጋር አለመገናኘታቸው እንደተገቢ ነገር ከተቆጠረ ይልቁንም ሥጋውንና ደሙን የሚቀበል ሰው ይህንን ሥርዓት ምን ያህል አጥናክሮ መጠበቅ ይገባው ይሆን? ስለዚህ ቤተክርስቲያን ለጥቅማችን የሠራችልንን ሥርዓት እናክብር ይህን ባናደርግ ግን ሥጋወደሙን እንደናቅን ይቆጠርብናል ይህ ደግሞ የበደል ሁሉ በደል ነው።

## ባልና ሚስት ሥጋ ወደሙን ከተቀበሉ (ከቆረቡ) በኋላ ለሁለት ቀናት ከሩካቤ መከልከል አለባቸው።

ፍትወት ምንም እንኳን እሳት ቢሆን ገትቶ የሚያቆመው መለኮታዊ ኃይል አለ። ይህን ለማየትና ስለሥጋወደሙ ክብር ስንል ከቆረብን በኋላ ለሁለት ቀናት ከሩካቤ እንከለከላለን። ለምሳሌ እሑድ የቆረበ ሰው የቆረበባትን እሑድ ይውላል ያድራል ሰኞንም ይውላል። ለማክሰኞ አጥቢያ ፈቃዱን መፈጸም ይችላል ይህም በፍትሐ ነገሥት እንዲህ ሰፍሯል "ለይኑም ብእሲ እቱተ አምብእሲቱ እምሠርክ ቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት እስከ ጽባሐ ቀዳማይ ሰዓተ መዓልተ ወእስከ ዳግም ሠርከ ሌሊት" ነገር ግን የቻሉና የፈቀዱ እንደ አቅማቸው ሰባትና አርባ ቀን ከዚያም በላይ ያለማገናኘት እንቆያለን ቢሉ በአንድ ሐሳብ እስከተስማሙ ድረስ ይመሰገናሉ እንጂ አይነቀፉም ቤተክርስቲያን የትሩፋትን ሥራ የሚገድብ ሕግ የላትምና። ሆኖም ይህ ፈቃድ ነው እንጂ ሕግ አይደለምና ከሁለት ቀን በላይ እንዲቆዩ አይገደዱም።

ካህኑ ዘካርያስ በዘመነ ዕብሬቱ (ሰሞንኛ ሳለ) በቤተ መቅደስ ተገኝቶ ዕጣን ሲያጥን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተገለጠለትና መጥምቀ መለኮት የተባለ ዮሐንስን እንደሚወልድ የምሥራች ነገረው ነገር ግን የምሥራች ቃሉን ስለተጠራጠረና ምልክት ስለፈለገ መልዐኩ ተቆጥቶ ዲዳ (መናገር የማይችል) አደረገውና ወደሰማይ ዐረገ። ዘካርያስም ወደ ቤቱ ተመለሰ "ወእምዝ ፈጺሞ መዋዕለ ዕብሬቱ አተወቤቶ" ሉቃ. ፩:፳፫ ያለው ይህንን ነው። ከቤተ መቅደስ ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ እስከ ሁለት ቀን ሚስቱን አልተገናኛትም። ይህን ሐሳብ በግዕዙ ቋንቋ አዲስ ኪዳን (አሥመራ የታተመው) "ወእምድኅረ ፪ኤ መዋዕል ፀንሰት ኤልሣቤጥ ብዕሲቱ ወከበተት ፅንሳ ኀምስተ አውርኀ " ማለትም "ከሁለት ቀንም በኋላ ሚስቱ ኤልሣቤጥ ብእሲቱ ፀነሰች ለአምስት ወርም ራስዋን ሰወረች" በማለት ይገልጽልናል። ዘካርያስ ከማዕጠንት (ዕጣን ካጠነ) በኋላ ለሁለት ቀን ከሚስቱ ጋር በምንጣፍ አለመገናኘቱ ባልና ሚስት ከቆረቡ በኋላ ተገቢውን የቤተክርስቲያን ቀኖና መፈጸምና ለሁለት ቀንም ሩካቤ ተከልክለው ከዚያ በኋላ ወደ ሩካቤያቸው መመለስ እንዳለባቸው ለሚደነግገው የሥርዓት መጽሐፍ መነሻ ሆኗል። ይህንን ሥርዓት ቸል በማለት ከቆረቡ በኋላ ተደፋፍሮ ወደ ሩካቤ መሄድ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅና ቁጣውንም ማነሣሣት ነው። ዕብ. ፲:፳፱–፴፩ ፤ ፩ኛ ቆሮ. ፲፩:፳፯–፴፬ ።

## በአጽዋማት፣ በሱባኤና በቀኖና ላይ እያሉ ሩካቤ ክልክል ነው።

በተመሣሣይ ሁኔታ በአጽዋማት ጊዜም ክርስቲያኖች ከሩካቤ መለየት አለባቸው ጾም የሚታወጀው ለመላው ሕዋሳቶቻችን ነው እንጂ



በአንድ ንዑስ አባል በሆዳችን ብቻ አይደለም በመላው ሕዋሳቶቻችን እንበድላለን "ሁሉ አመፁ በአንድነትም ረከሱ" መዝ. ፲፫:፫ ይላልና ጽድቁም ለመላ አካላችን መድረስ አለበት ቅዱስ ያሬድ "ይጹም ዓይን፣ ይጹም ልሣን ዕዝንኒ ይጹም እምሰሚዓ ሕሡም በተፋቅሮ" እንዳለ ዓይን ልሣንና ጆሮ በፍቅር ሆነው ከክፉ ነገር መጾም ይገባቸዋል። በነዚህ ሦስት ሕዋሳቶቻችን መነሻነት መላ ሕዋሳቶቻችን መጾም እንዳለባቸው ገልጾልናል ከንዑስ መሌሊቶች አንዱ ተላጽቆ የሚፈጸምበት አባለዘራችን ስለሆነ በእርሱም ጾም አውጀን ኀፍረተ አካላችንን ከሩካቤ ማስጾም ይገባናል።

በተጨማሪም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሱባኤ በጾምና በጸሎት ጊዜ ብቻ እንጂ ባልና ሚስት ሰይጣን እንዳይፈትናቸው መለያየት እንደሌለባቸው ሲገልጽ "ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በእርሳችሁ አትከላከሉ ራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ" ፩ኛ ቆሮ. ፯:፭ በማለት ጽፎልናል። ባልና ሚስት ምንም እንኳን በመኝታ መለያየት ባይገባቸውም ለጸሎትና ለጾም ሲባል ግን በመኝታ መለያየት እንዳለ 'ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ' የሚለው ቃል ያሳያል ይህን የሐዋርያውን አዋጅ ጥሰን በጾም ጊዜ ፈቃደ ሥጋን ለመፈጸም መርጥ ለሥጋችን መገዛታችንንና ፍቅረ እግዚአብሔር የጎደለብን መሆናችንን ያሳያል።

የጾም ፍቺና አካሄድ ብዙ ቢሆንም አንዱ ግን ለሥጋ ደስ የሚያሰኙትንና ሥጋችን የሚፈልገውን ነገሮች ለጊዜው በመከልከል ከሥጋችን ይልቅ ለእግዚአብሔር መገዛታችንን የምናሳይበት መንገድ መሆኑ የታወቀ ነው። ታዲያ ሩካቤን ያህል ታላቅ ደስታ እየፈጸሙ በንስሐና፣ በኀዘን፣ በሱባኤና በጾም ላይ ነኝ ማለት እንዴት ይቻላል ሩካቤ ጠቦት አርዶ መመገብ ነውና ጠቦት እየበሉ መጾም ደግሞ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ሩካቤን መፈጸምና የሰባ በግን አርዶ መመገብ አንድ መሆናቸውን ነቢዩ ናታን አስረድቶናል። ቅዱስ ዳዊት የኦርዮን ሚስት በመንጠቁ ምክንያት እንዲገስጸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነቢዩ ናታን በተላከ ጊዜ ዳዊት የሠራውን ሥራ በምሳሌ ሠውሮበት ስለራሱ ዳዊትን እንዲፈርድ ሲጋብዘው "በአንድ ከተማ አንዱ ባለጸጋ አንዱንም ደሀ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ባለጸጋውም እጅግ ብዙ ላምና በጎች ነበሩት ለድሃው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳች አልነበረውም። አሳደጋትም ከልጆቹም ጋር ከእርሱም ጋር አደገች እንጀራውንም ትበላ በዋንጫውም ትጠጣ በብብቱም ትተኛ ነበር። እንደ ልጅም ነበረች ወደ

ባለጠጋው እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለዚያ ወደ እርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድ ሳሳ የዚያንም የድሀውን ሰው በግ ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ" በማለት ነበር የዚህን ጊዜ በእርሱ ላይ የተመሰለበት ምሳሌ መሆኑን ያላወቀ ዳዊት ተቆጥቶ ይህ ሰው የሞት ልጅ ነው ስለአንዱም አራት ይክፈል ሲል ሳያውቅ በራሱ ፈረደ ብዙ ላሞችና በጎች አሉት የተባለው ብዙ ሚስቶችና ዕቁባቶች ያሉት ንጉሥ ዳዊት ነው። አንዲት በግ ብቻ ያለችው ድሃም አንዲት ሚስት ቤርሳቤህ ብቻ ያለችው ኦርዮ ነው። እንግዳም ወደ ሀብታሙ ሰው መጣ ማለት በዳዊት ፈቃደ ሥጋ ተነሣበት ማለት ነው። ፈቃደ ሥጋ እያደር አዲስ ስለሆነና ስለማይለመድ እንግዳ ይባላል። ታዲያ ዳዊት ከሚስቶቹ ከአንዷ ጋር ማደር ሲቻለው በግ የተባለችውን ቤርሳቤህን ተመገባት ማለትም ከባሏ ነጥቆ ተገናኛት በዚህ ታሪክ ነቢዩ ናታን ሩካቤን መፈጸም ጠቦት አርዶ መመገብ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ገልጾታል በጾም ጊዜ ሩካቤ ተገቢ አይደለም መባሉን የሚንቅፍ ቢኖር በጾም ጠቦት መመገብ ይቻላል ማለቱን መገንዘብ አለበት። ስለዚህ በጾም ጊዜ ከሩካቤ በመራቅ ጾማችንን ፍጹም ንጹሕ ማድረግ ይገባናል።

የሥርዓት መጽሐፋችን ፍትሐ ነገሥት ባልና ሚስት በጾም ጊዜ በምንጣፍ አይገናኙ ይልቁንም በዓቢይ ጾም ፈጽሞ ከዚህ ይሽሹ ከዐቢይ ጾምም በተለይ በሰሙነ ሕማማት በዚህ ግብር የሚገኝ እንዳይኖር "አሌሎቱ ለዘይገብር ዘንተ ኃጢአተ በመዋዕለ ቅድስት " ማለትም "ይህንን ኃጢአት ቅድስት በምትሆን በሰሙነ ሕማማት ለሚፈጽም ሰው ወዮለት" በማለት ያስጠነቅቃል። የባልና የሚስት ሩካቤ ኃጢአት ባይሆንም በማይገባ ወቅት ይልቁንም በሰሙነ ሕማማት ከተፈጸመ ኃጢአት እስከመባል ይደርሳል። ለዚህ ነው ፍትሐ ነገሥት በሰሙነ ሕማማት የሚፈጸመውን ሩካቤ 'ዘንተ ኃጢአተ' በማለት የገለጸው። በሰሙነ ሕማማት ሩካቤን መፈጸም ፍጹም ይሁዳን መምሰል ነው። ይሁዳ በዚያ ወቅት ሩካቤን እንደፈጸመ ግብረ ሕማማት የተባለው መጽሐፍ 'ወሰከባ ለብእሲቱ' በማለት ይገልጸል። በጾም በጸሎትና በኀዘን ከዕንባ ጋር ወደ እግዚአብሔር በመመለሻ ወቅት በሥጋ ግቢያ ሲልከሰኩ መገኘት በጣም ያሳፍራል። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዓይነት ጊዜ ሙሽራን እንኳን ሲያዝ "በጽዮን መለከትን ንፉ ጾምንም ቀድሱ ጉባኤንም አውጁ" ካለ በኋላ ጨመር አድርጎ "ሙሽራው ከእልፍኙ ይውጣ ሙሽራይቱም ከጫጉላዋ ይውጡ" ይለናል ኢዮ. ፪፥፲፭–፲፮።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ከሩካቤ መራቅንና መብል መጠጥን በመተው መጾምን አንድ ላይ ያስኬዳቸዋል። ነቢዮ ዳዊት ኦርዮን የልጅ



ፍቅር የሴት ከንፈር አያምርህምን? ሂድ ወደ ሚስትህ ግባ ባለው ጊዜ "... የጌታዬ ባሪያዎች በሜዳ ሰፍረዋል እኔ ልበላና ልጠጣ ወይስ ከሚስቴ ጋር ልተኛ ወደ ቤቴ እሄዳለሁን?" ፪ኛ ሳሙ. ፲፩፥፲፩ በማለት የተናገረው ንግግር ሐሳባችንን ግልጽ ያደርገዋል። ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች በጾም ጊዜ ፈቃደ ሥጋን መፈጸም ጾምን መግደፍ እንደሆነ ተገንዝበን ልንቆጠብ ይገባናል።

እንደዚሁም ሁሉ በንስሐ አባታችን አማካይነትም የተሰጠንን ቀኖና እስክንፈጽም ድረስ ሩካቤ ክልክል ነው። እንኳን በጾም ወቅትና በንስሐ (በቀኖና) ውስጥ ሳለን ይቅርና ስለምንሻው ነገር በግላችን ሱባኤ ስንገባ እንኳን በሱባኤ ውስጥ ሩካቤ ክልክል እንደሆነ ማወቅ አለብን። ዳዊት "ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም" መዝ. ፻፴፩፥፫ በማለት የፈጣሪውን ማደሪያ እስኪያገኝ ድረስ ከሚስቱ ጋር ላለመተኛት የወሰነው ውሳኔ በሱባኤ ጊዜ ሩካቤ እንደማይፈቀድ ያስገነዝበናል።

አንዳንድ ሰዎች ከሌላው ሰው ይልቅ ፍትወት ያስቸግራቸዋል። ስለዚህ አጽዋማትን በትዕግሥት ለማለፍ ይቸገራሉ። በዚህ ጊዜ እንደ ጾመ ሕርቃል ዓቢይ ጾም እና ሰሙነ ሕማማት በፍጹም ጥንቃቄ ማለፍ በሌሎች አጽዋማት ግን ከመምህረ ንስሐቸን ጋር በመመካከር በስጡን የመፍትሔ ሐሳብ መጓዝ ይገባል። ምክንያቱም ጾምን ለመፈጸም ብሎ በትዳር ችግር ከመፍጠር ወይም ስለሩካቤ እያሰቡ ከማደር ሩካቤን አንድ ጊዜ መፈጸም ይሻላልና። ሆኖም መምህረ ንስሐን ማማከር ግን ግዴታ መሆኑ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ አንድ ሰው በጾም ወቅት ፍትወት ቢያስቸግረውና መፈጸም ቢኖርበት መፈጸም ያለበት መመገብ በሚቻልበት ሰዓት ብቻ ነው ማለትም ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት (ለስድስት ሰዓታት) ማለት ነው። ይህ ሐሳብ በፍትሐ ነገሥት በዚህ መልኩ ቀርቧልና። "እመ ቦ ዘተመውአ እምፍትወት ነዳዲት ወዘኢይትከሀሎ ላዕለ ተጋድሎታ ይደልዎ ሎቱ ከመያጥፍአ ኪያሃ ወያእትት ተዳድቆተ ኀሰማ በጊዜያተ ሌሊት ዘብውሕ ባቲ በሊዕ ወሰትይ ዘእንበለ ሌሊተ መዓልት እንተ ባቲ ተአዘዘ ይቅረቡ ባቲ" ምንም እንኳን መመገብ በሚቻልበት ሰዓት በፍትወት ለተቸገሩት ሰዎች ሩካቤ ቢፈቀድም ረቡዕ ዓርብ ቅዳሜንና እሑድ በሚያስከትሉ ሌሊቶች መቆጠብ እንደሚገባ ጨምሮ ጠቅሶልናል።

## ምዕራፍ ፱
## <u>ማመንዘር ክልክል ነው!</u>

አታመንዝር፦የሚለው ሕግ መልኩን ሳይቀይር ቁልጭ ብሎ በኦሪት መጽሐፍ ሰፍሯል። ዘፀ. ፳፥፲፬ ከዚያም በፊት ምንም እንኳን ይህ

ትእዛዝ በጽላት ላይ ተቀርጾና በመጽሐፍ ላይ ተጽፎ ለሰው ልጆች ባይሰጥም በልቡናቸው ላይ በተፈጥሮ የተሳለባቸውን ሕግ /ሕገ ልቡና/ ጥሰው ሲያመነዝሩ የተገኙ ሰብአ ትካት /የቀድሞ ሰዎች/ እና ሰብአ ሰዶም በመቅሠፍት ውኃና በእሳት ተቃጥለው መጥፋታቸው አልቀረም። ዘፍ. ፮,፰ እና ፲፱፤ ፪ኛ ጴጥ. ፪:፬-፲ ፤ ይሁዳ ፯።

የሕገ ልቡና ዘመን ካለፈ በኋላም ሲያመነዝሩ የተገኙ ሰዎች በድንጋይ ተወግረው እንዲሞቱ "ማንኛውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ።" ዘሌ. ፳:፲ የሚል የፍርድ ትእዛዝ እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ለሰው ልጆች ሰጠ። በዚህ ትእዛዝ መሠረት ሲያመነዝሩ የተገኙ ሰዎች ያለምንም ርኅራኄ በድንጋይ እየተወገሩ ሕጉ እስከ አዲስ ኪዳን ድረስ ጸንቶ ኖረ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌ በዚህች ምድር ላይ ሲመላለስ አይሁድ በኦሪት ሕግ መሠረት ስታመነዝር የተያዘች ሴት ወደ እርሱ አመጡና ሙሴ በድንጋይ ተወግራ እንድትሞት አዞናል አንተ ስለዚህች ሴት ምን ትላለህ በማለት የፈተና ጥያቄ አቀረቡለት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለሁሉም የየራሳቸው ኃጢአት እንዲታያቸው ካደረገ በኋላ "ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። "እነርሱም ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ሁሉም ጥለዋት ሸሹ ጌታችንም ሴቲቱን "እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁን ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።" ዮሐ. ፰:፫-፲፩ በዚህ የጌታ ቃል መሠረት ተወግሮ መገደልን የሚያዘው የኦሪት ትእዛዝ ተሻረ ነገር ግን ምንም እንኳን ተወግሮ መሞትን የሚያዘው ትእዛዝ የተሻረ ቢሆንም ያመነዘሩ ሰዎች ንስሐ ባይገቡና "ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" የሚለውን የጌታ ቃል ጥሰው በኃጢአታቸው ጸንተው ቢኖሩ ሰማያዊ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።

በአዲስ ኪዳን ጌታችን ያሳለፈው በድንጋይ ተወግሮ መሞትን ነው እንጂ 'አታመንዝር' የሚለውን ሕግ አይደለም። ይህም ጌታችን ራሱ "ለቀደሙት አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል" ማቴ. ፭:፳፯-፳፱ በማለቱ ይታወቃል። እንዲያውም "ወደ ሴት ያየ የተመኛትም" በማለት አጠናክሮታልና ሕጉ አለመሻሩ ግልጽ ነው። ጌታችን ሕግና ነቢያትን ለማሻር አልመጣምና። ማቴ. ፭:፲፯።

'አታመንዝር' የሚለው ሕግ በቀጥታ የሚመለከተው ባለትዳሮችን ነው። ባለትዳር ሰው እንኳን ማመንዝር አይቶ መመኘት እንኳን



አይገባውም። 'ያየ የተመኛትም' የሚለው ሕግ ይመለከተዋልና። ከትዳር ውጭ ያሉ ሰዎች የሚፈጽሙት ሩካቤ ሥጋ ዝሙት /ሴሰኝነት/ ይባላል። እንጂ በልማድ ካልሆነ በቀር ማመንዝር አይባልም። ማመንዝር የሚጠቀሰው ለባለትዳሮች ብቻ ነው። ይህ ገለጻ ስለሁለቱ ድርጊቶች የስያሜ ልዩነት ለመግለጽ ነው እንጂ ኃጢአትን እንዱን ከአንዱ ለማበላለጥ አይደለም። ያገባ ቢያመነዝር ያላገባም ሲሰስን ሁለቱም ኃጢአት ከመሥራት አልሸሹም።

## ማመንዝር ሥጋን እንዴት ይበድላል?

የሚያመነዝር ሰው ሥጋውን ይበድላል። ሥጋው የሚባለው የራሱ ሰውነት ሲሆን ሚስቱም አካሉ ናትና ሥጋው ትባላለች። ልጆቹም እንደዚሁ። በተጨማሪም አብራው የምታመነዝረዋም ሴት ሥጋው ትባላለች። በሩካቤ ተዋሕዷታልና። በዚህ አተረጓጎም አመንዝራ ሰው በአራት አቅጣጫ ሥጋውን ይበድላል። በመጀመሪያ የገዛ ሰውነቱን በደዌ፣ በመቅሠፍት፣ ሕጉን በማፍረስ ልጆቹንም ለሚተላለፍ በሽታ ሲዳረግ ሚስቱን ደግሞ ለበሽታ ከመዳረጉም በላይ ንብረቷን ያባክንባታል የሚገባትን ለሌላ ይሰጥባታል። ሌላይቱንም ሴት ከባሏ ይለያታል ሕጓን ያፈርስባታል። ይህን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዐረፍተ ነገር ሲያስረው። "ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል" ይላል ፩ኛ ቆሮ. ፮:፲፰።

ከላይ በገለጽነው መንገድ ካገቡ በኋላ ማመንዝር ወይም ሌላ ሚስት /ቁባት/ ማኖር ሚስትን መበደል መሆኑን አጎቱ ላባ ለሴቶች ልጆቹ ያዕቆብን ቃል ባስገባው ጊዜ "ልጆቼ ብትበድላቸው ወይም በላያቸው ሚስቶችን ብታገባባቸው ከእኛ ጋር ሰው የለም እግዚአብሔር በእኔና በአንተ መካከል ምስክር ነው።" ዘፍ. ፴፩:፶ በማለት የተናገረው ቃል ያስረዳናል።

## ካመነዘሩ በኋላ መሸሸግ አይቻልም

"ተደብቀው የፀነሱ ሴቶች በሰው በረንዳ ይወልዳሉ" የሚባለው አመንዝራ ኃጢአቱን መደበቅ እንደማይችል ለመግለጽ ነው። እግዚአብሔር ከባቴ አበሳ /በደልን የሚሰውር/ ስለሆነ ንስሐችንን ተቀብሎ ኃጢአታችንን ካልሰወረልን በስተቀር በራሳችን ጥበብ ኃጢአታችንን መሸሸግ አንችልም። ከሕሊናችን የምንሰውረው ምን ውስጥ ገብተን ነው? ከዚህ ይልቅ ከእግዚአብሔር መንፈስ የምንደብቀው ወዴት ሸሽተን ነው? ስለዚህ አመንዝራ ምንም የሚሮጥበት ሜዳ የሚገባበት ቀዳዳ የለውም። እግዚአብሔር ቢፈልግ

ምድርንና ሰማይን ጨለማንና ብርሃንን በእኛ ላይ ማስመስከር ይችላል። ከነዚህ ፍጥረታት ተለይቶ ኃጢአት መሥራት የሚቻለው የሰው ወገን ይኖር ይሆን? በጭራሽ የለም። እያንዳንዱ ሰው የትም ቢሄድ ጠባቂ መልአክ አለው ኃጢአት ስንሠራም ጥበቃውን አያቋርጥም ምስክር እንዳይሆንብን በምን ልናልፈው እንችላለን?

ዳዊት የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ ኃጢአት ሠራ። ባረገዘችም ጊዜ በደሉን ለመሰወር ያልሞከረው ሙከራ አልነበረም ፅንስ ለማሳሳት ባሏን ካሰከረው በኋላ አብሯት እንዲያድር መከረው ስላልተሳካለትም በጦር አስገደለው። በመጨረሻም እግዚአብሔር ጥረቱን ሁሉ ከንቱ ለማድረግ ነቢዩ ናታንን ልኮ በግልጽ እንዲወቅሰው አደረገ። የዳዊትን ያህል ሹመት ሀብትና ጥበብ ቢኖረን እንኳን በገዛ ጉልበታችን ኃጢአታችንን መሰወር የማይታሰብ ነገር ነው። ፪ኛ ሳሙ. ፲፪:፩-፳፫።

ሰው ተሰውሮ የሚሠራውን እግዚአብሔር በግልጽ እንደሚያይ "ሚስቱን ትቶ የሚሄድ ሰው መንደሩ ጨለማ ነው የሚያየኝም የለም አጥር ይጋርደኛል ከዚህ በኋላ ምን እፈራለሁ እግዚአብሔርም ኃጢአቴን ይዘነጋልኛል እኔንም በመዓት አያሰበኝም ይላል። ነገር ግን እንዳያየው የሰውን ዓይን ይፈራል እልፍ ፀሐይ የለም እንጂ የእግዚአብሔርም ዓይን ከዚያ ይልቅ እንዲያበራ የሰውንም ሥራ እንዲያዩ ሰው ተሠውሮ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እንዲያውቅ አያውቅም።" ሲራክ. ፳፫ :፲፰-፲፱ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል።

## የማመንዝር ቅጣት

እንኳን ዝሙት ማንኛውም ኃጢአት ቅጣትን ማስከተሉ አይቀርም። ቅጣቱም እግዚአብሔር በፈቀደው መንገድ በረቂቅ መንገድ ወይም በግልጽ ሊሆን ይችላል።

ዳዊት በማመንዝር ኃጢአት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር የሚያመጣበትን ቅጣት በዝርዝር ነግሮታል። በኋላም ቅጣቶቹን በየተራ በዳዊት ትከሻ አኑሯቸዋል። እግዚአብሔር የተናገረውን አያስቀርምና። ፪ኛ ሳሙ ፲፪:፲ -፲፪ የዳዊት ቅጣቶች በሙሉ ጉልህና ማስተማሪያ መሆን የሚችሉ ነበሩ። ለምሣሌ አንዱ ቅጣቱ በዝሙት የፀነሰው ልጁ መታመምና መሞት ነበር ይህም ሰው ሊረዳው በሚችል መልኩ ነው። ሁለተኛው ደግሞ "እነሆ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ" የሚለው ሲሆን ይህም ሊፈጸም አምኖን የተባለ ወንድ ልጁ ትዕማር የተባለችውን ሴት ልጁን በግድ ደፈራት "ለዘለዓለም ከቤትህ ሰይፍ አይርቅም" የሚለው ሦስተኛው ቅጣት እንዲፈጸም ደግሞ አቤሴሎም የተባለው ወንድ ልጁ አምኖን የተባለውን የቤቱን ታላቅ በሰይፍ ሲያስገድለው



ራሱ ዳዊትንም ከዙፋኑ አስነሥቶ አሳድዶታል። ከሁሉ የሚያስደነግጠው ደግሞ "ሚስቶችህንም በዓይንህ ፊት እወስዳለሁ ለዘመድህም እሰጣቸዋለሁ በዚህችም ፀሐይ ዓይን ፊት ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል" በማለት እግዚአብሔር የተናገረበት የቁጣ ቃል የገዛ ልጁ አቤሴሎም ሚስቶቹን በገዛ መኝታው ላይ በደፈራቸው ጊዜ ትንቢቱ መፈጸሙ ነው። እግዚአብሔር ይህን ሁሉ በዳዊት ላይ ያመጣበት ዳዊት ይህን ሠርቶ ምን ሆነ? በማለት እንዳንገዳደረው መሆኑን አውቀን ከኃጢአታችን ባንቆጠብ የሚያገኘን ቅጣት እንደ ዳዊት ምድራዊ ብቻ አይሆንም።

ማመንዘርን የሚወዱ ሰዎች የጥፋታቸውም ምክንያት የሚሆነው ማመንዘር ነው። ምንዝር የምትወድ አንዲት ሴት ነበረች አንድ ቀን ባሏን ትታ ወደ እናት አባቷ ቤት ሄዳ ተቀመጠች ከአራት ወርም በኋላ ባሏ ዕርቅ ፈለገና ወደ ቤቱ ሊመልሳት ፍለጋዋን ተከትሎ ሄደ። ይዟትም ወደ ቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ከመንገድ መሸባቸውና በእንግድነት ተጠግተው ወደ አንድ ሽማግሌ ሰው ቤት ገቡ። ወስላቶች የሆኑ የከተማው ሰዎች በብዙ ትግል ሚስቱን ቀምተው ከቤት ካስወጧት በኋላ ሲያመነዝሩባት አደሩ። እርሷም ዘር አስከሯት ሞተች። መሳ. ፲፱:፩-፳፮ ይህች ሴት የሞተችው ትወደው በነበረ ዝሙት መሆኑን ተመለከትክን? ስለዚህ መጥፊያህ እንዳይሆን አታመንዝር!

ከዚህ በላይ ባሰፈርነው ታሪክ ከወንድ ንጉሥ ዳዊትን ከሴት ደግሞ በአመንዝራነቷ ምክንያት የሞተችውን ቤተልሔማዊት ሴትና የደረሰባቸውን ቅጣት አይተናል። ከዚህም በተጨማሪ ጥበበኛው ሲራክ "ኃጢአት ከጨረሰ በኋላ እንዲህ ያደረገዋል ባገርም መካከል ይበቀለዋል ያላሰበውም ጠላት ያጠፋዋል። ባሏን ትታ የምትሄድም ሴት እንደ እርሱ ናት ከውሽማዋ ልጅ ትወልዳለች። በእግዚአብሔር አንዲት ክህደት አደረገች ሁለተኛም ባሏን ወነጀለችው ሦስተኛም በቤሰኝነቷ ሰረቀች ከውሽማዋም ልጅ ወለደች። እንዲህ ያለችቱን ሴት ያጎስቁሏታል በልጆቿም ትገረፋለች። የልጅ ልጆችና ልጆቹ ይጠፋሉ ልጆቿም ልጅ አይወልዱም። ስም አጠራሯም የተረገመ ይሆናል። ወገኖቿንም ታስረግማቸዋለች እርግማኗ ጉስቁልናዋ ፈጽሞ አይጠፋም። ያያት ሁሉ እግዚአብሔርን ከመፍራት የሚበልጥ እንደሌለ የእግዚአብሔርንም ሕግ ከመጠበቅ የሚበልጥ እንደሌለ ያውቃል።" ሲራክ ፳፫:፳ -፳፯በማለት አመንዝራነት የሚያስከትለውን ቅጣት በዝርዝር አስቀምጦታል።""

## ወደማመንዝር የሚገፋፉ ጥቂት ሰይጣናዊ ሐሳቦች

ባልና ሚስት ተማምነውና ተፋቅረው መኖራቸው መልካም ነገር ነው። ነገር ግን ይህ ዕድል ሁል ጊዜ አይገኝምና ከሁለት በአንዳቸው

ቃል ኪዳን ማፍረስና ማመንዘር ሊፈጠር ይችላል። በዚህ ጊዜ በእጅጉ የሚፈተነው ቃል ኪዳኑን ጠብቆ የተገኘው ሰው ነው። ምናልባትም ሰይጣን ብድሩን እንዲመልስና በተራው እንዲያመንዝር ሹክ ሊለው ይችላል። በዚህ ሰበብ የሚያመንዝር ካለ ሰይጣኑም ራሱ ቂል ብሎ ሳይቀልድበት አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱስ "ውሽማዋንና ባሏን የምታቀና ሴት ኃፍረት ናት።" ሲራክ. ፳፮:፲፬ ይላል። አንዳንድ ሰዎች የትዳር አጋራቸውን ማስቀናት እንደ መልካም ነገር ይቆጥሩታል። ይህ መንገድ ለሚሄዱበት ሰዎች ለራሳቸው መጨረሻው ጥፋት ከመሆኑም ሌላ የትዳር አጋርን ክፉ ትምህርት ያስተምራል። ስለዚህ የባልና የሚስት እርስ በእርስ ለማስቀናት መሞካከር በሃይማኖት ትምህርት የተወገዘ ነው። ለማስቀናትም ብሎ መዳራትና ማመንዘር ለወቀሳና ለቅጣት የቅርብ ዘመድ መሆን ነው።

ማንኛውም ሰው በኑሮ አጋሩ በደል ሊደርስበት ይችላል። ሆኖም ተበድያለሁና በማለት ለመበደል መነሣት "ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ በሰው ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።" ሮሜ. ፲፪፲፯ ፤ምሳ. ፳:፳፪ ፤ ፩ኛ ተሰ. ፭:፲፭ የሚለውን የፈጣሪ ቃል መተላለፍ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በትዳሩ በደል ቢደርስበት በዳዩን ወገን ለማናደድና ለመበቀል ሲል ለማመንዘር ማሰብ የለበትም።

ከማመንዘር የምንቆጠበው ሰዎችን፣ ልጆቻችንንና ሚስታችንን ብለን ብቻ መሆን የለበትም የእግዚአብሔርንም ቃል በማሰብ ነው እንጂ። ይህ ካልሆነ ግን ልጆቻችንንና ሚስታችንን በማንገዳበት መልኩ የማመንዘር ዕድል ሲገጥመን ሐሳባችንን ለማስቀም አቅም አይኖረንም።

ሩካቤን ለመፈጸም በተነሣሣንበት ሰዓት ከትዳር አጋራችን ተቃውሞ ቢገጥመን ተረጋግተን ነገሩን በአንክሮ ማጤንና ለውይይት በር መክፈት ይገባል እንጂ ወዲያውኑ ፈቃዳችንን የምንፈጽምበት ሌላ ሰው በልቡናችን መቃኘት የለብንም።

በአንዳንድ ፊልሞችና መጻሕፍቶች ታግዘን መንፈሳዊ መጽሐፍና ተፈጥሮአችን የማይደግፈውን የሩካቤ አፈጻጸም በመውደድ በገንዘብ ከምትገዛ የዝሙት ባለሙያ ጋር ኃጢአት መሥራት እንዳያምረን ሁል ጊዜ ሰዶምና ገሞራን መዘከር ይገባል።

እንደማንኛውም ችግር በትዳር መሐል ልጅ አለመውለድ /መካንነት/ ሊፈጠር ይችላል። ይህ ችግር ደግሞ እንደሌሎች ችግሮች በመወያየት በመመካከርና እርስ በእርስ በመተራረም ላይፈታ ይችላል። ቢሆንም ግን ልጅ ለመውለድ በሚል ሰበብ ከትዳር ወጥቶ ለማመንዘር ምክንያት አይሆንም።



## ከባልና ከሚስት የአንዳቸው ሞት

ከባልና ከሚስት አንዳቸው ቀድመው ቢሞቱ በሕይወት የተረፈው ልጆቹን ባለው ዓቅሙ የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት። ቀሪ ሕይወቱን በብቸኝነት ለመግፋት ካልቻለም በሥጋ ወደሙ ዳግመኛ ማግባት ይችላል። ሆኖም ይህ ጋብቻ በሥጋ ወደሙ መፈጸም አለበት። ቅዱስ ጳውሎስ ስለሁለተኛ ጋብቻ ሲናገር "*በጌታ ይሁን እንጂ*" በማለት መናገሩ ሁለተኛም ጋብቻ ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸም እንዳለበት ለመጠቆም ነው። ፩ኛ ቆሮ ፯: ፴፱ - ፵።

<u>የባል ወይም የሚስት ሞት ለማመንዘር ምክንያት መንስዔ መሆን የለበትም በብቸኝነቱ መጽናት ካልሆነላቸው ማግባት ይችላሉና።</u> ዳግመኛ ማግባትን ካልፈቀዱ በንጽሕና መኖር ይጠበቅባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ባል የሞተባት ሴት ዳግመኛ ማግባት እንደምትችል እንዲህ በማለት ይገልጸዋል "ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ስለባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች።" ስለዚህ ባልዋ በሕይወት እያለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች። ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።" ይላል ሮሜ ፯:፪-፫ ይህ ቃል ለወንዱም እንዲሁ ነው።

በተጨማሪም በሞት ምክንያት ስለሚደረግ ሁለተኛ ጋብቻ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል። "ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነፃነት አላት። *እንደ ምክሬ ግን እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት።*" ፩ቆሮ. ፯:፴፱-፵ ።

ያፌ መንጢጥ የምትባል ወፍ አለች። ባሏ በሚሞትባት ጊዜ ምንቃሯን በመተልተል ኀዘኗን ትገልጣለች። ዳግመኛም አታገባም። በግድም የሚመጣ ባል ቢኖር ከባልንጀሮቿ ጋር ተባብራ ታባርረዋለች። ከዚህች እንስሳ ተምሮ ሰው ከሁለተኛ ጋብቻ ቢርቅ መልካም ነው ቀሪ ኑሮው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የደስታ ይሆንለታል። ቅዱስ ጳውሎስ "*እንደ ምክሬ ግን እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት*" በማለት የተናገረው የሚቻል ከሆነ ዳግመኛ አለማግባት ይመረጣል በዳግም ጋብቻ ከሚመጣ ልዩ ልዩ ፈተና ትርቃለችና። ነገር ግን ይህ ምክር ነው እንጂ ሕግ ስላልሆነ በዚህ ጉዳይ መወሰን የሚችለው የኑሮ አጋሩ በሞት የተለየበት ሰው ራሱ ነው። ካህንንም ቢሆን ከክህነቱ ታሽረዋለች። ሁለተኛ ጋብቻ ለካህናት አይፈቀድምና።

ባሏ የሞተባት ሴት ከአሥር ወር በኋላ ፣ ሚስቱ የሞተችበት ደግሞ ከአንድ ዓመት በኋላ ዳግመኛ የማግባት መብት አላቸው። ጋቢቻቸውም

የመአስባን (አግብተው የፈቱና በንስሐ የተመለሱ ምዕመናን) ዓይነት ነው። ይኸውም ፍትሐት ዘወልድ እና ጸሎተ ንስሐ ይደገምላቸዋል እንጂ ጸሎተ ተክሊልና ሥርዓተ ተክሊል አይደረግላቸውም። በዚህ ዓይነት ባለቤቶቻቸው በተደጋጋሚ የሞቱባቸው ሰዎች ለብቻቸው መኖር ካልቻሉ ምንም የተናቀ ቢሆን እስከ ሦስት ጊዜ ማግባት ይችላሉ። ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳፬።

## ለማመንዘር መብት ያለው ሰው ይኖራልን?

ሰዎችን እንዳያመነዝሩ ያገደው ሕግ የተገኘው በቀጥታ ከእግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ማንኛውም የሰው ወገን እርማትና ማስተካከያ ሊሰጥበት ቀርቶ ራሱም ሊተላለፈው አይገባም። መንፈሳዊ ነገሮችን በተመለከተ ልዩ ሥልጣን ያላቸው ካህናትም ቢሆኑ ይህን በመሰለና ዶግማዊ ይዘት ባለው የእግዚአብሔር ሕግ ላይ የሚጨምሩት ወይም የሚቀንሱት አንዳች ነገር እንደሌለ መታወቅ አለበት። ከዚህ ወጥተው ለመሥራት ቢሞክሩ መናፍቅ ተብለው ይለያሉ እንጂ ከህነታቸውን በአግባቡ ተጠቀሙበት አይሰኙም።

አታመንዝር የሚለው ሕግ የማይመለከተው ወይም ከዚህ ሕግ በላይ የሆነና ለማመንዘር ልዩ ፍቃድ የሚሰጠው የሰው ወገን የለም። ጠንቋይ ቢያመነዝር ኃጢአቱ ድርብ ነው አንድ ጠንቋይነቱ ሁለት አመንዝራነቱ፤ ነቢያት ካህናትና ነገሥታት ቢያመነዝሩ ደግሞ በእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት መቆማቸው አይቀርም። ለሕዝብ አርአያና አገልጋይ ሁኑ ብሎ ያሠለጠናቸው የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሰዋልና።

## ማመንዘርን ማን ሊፈቅድ ይችላል?

ለማመንዘር ሥልጣን ያለው የሰው ወገን እስከሌለ ድረስ ሌሎች ሰዎች እንዲያመነዝሩ የመፍቀድ ሥልጣን ያለው አካል ሊኖር አይችልም። ነገር ግን አንዳንድ የእምነት ድርጅቶች አመንዝራነትን ፈቅደው ለተከታዮቻቸው እያስተማሩ ነው። በዚህም ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርተዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሏቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል።" ፪ኛ ጴጥ. ፪:፪ በማለት የተናገረው ቃል እንደነዚህ ላሉ የእምነት ድርጅቶች ሊጠቀስ ይችላል። ጠንቋዮችም ሰውን ወደ አመንዝራነት ለማንገድ በጥበብ የተሠሩ ድልድዮች ናቸው። አንዳንድ የሕክምና ባለሙያዎችም አስተውለውትም ይሁን ሳያስተውሉት ሰውን ወደ አመንዝራነት የሚገፋፉበት ጊዜ አለ። ከሁሉ የሚያስደንቀው ግን ባል ሚስቱን ሚስት ደግሞ ባሏን ወደ ዝሙት ፈቅደው ሲያሰናብቷቸው



ማየት ነው። እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁሉ ግን እንኳን አመንዝራነትን ሊፈቅዱ ራሳቸው በተጠያቂነት ውስጥ ያሉ ናቸው።

## ባልና ሚስት ለማመንዘር ቢፈቃቀዱስ?

አንዳንድ ሚስቶች የባሎቻቸውን ማመንዝር እያዩና እየሰሙ/እያወቁ/ በመቃወም ፈንታ ዝም ብለው በቸልታ ያልፏቸዋል። ሌሎች ደግሞ በተለያዩ መንገዶች እና በግልጽ ቃል ባሎቻቸውን ወደ ማመንዘር ይገፋፏቸዋል። ጋብቻ ሰዎች ከማመንዘር እንዲጠበቁ ተዘጋጅቶ እያለ የትዳር አጋሮች ራሳቸው ለባሎቻቸውና ለሚስቶቻቸው ማመንዘር ምክንያት በመሆን መጠቀሳቸው በጣም ያሳዝናል።

የኑሮ አጋርን ወደ ዝሙት መገፋፋት በሚስትም በባልም ላይ የሚታይ የጎላ ስሕተት ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ በብዛት የገለጠው የሚስቶችን አነሣሽነት ነው። የተጠቀሱትም ሴቶች ባሎቻቸውን ወደዚህ ድርጊት እንዲገፋፏቸው ያደረጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሯቸውም ሁሉም ፈራሽና መሠረተ ቢስ ነበሩ።

ባሏ ሲያመነዝር በዝምታ ያለፈች/የፈቀደች/ ሴት ለምን ባሏን በቸልታ እንደምታልፈው ብትጠየቅ ባሏን እንደምትወደውና እርሱ የሚሆነውን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ እንደሆነች ወይም ድርጊቱን ብትቃወመው ጨርሶ ልታጣው እንደምትችል አስባ በመስጋቷ ድርጊቱን ለመቀበል ግድ እንደሆነባት ወይም ደግሞ ከባሏ ጋር አብራው የምታመነዝረዋ ሴት ለእርሷም የልብ ወዳጇ በመሆኗ ችግር እንደሌለው ልትናገር ትችላለች። ይህ አመለካከት ግን ፍጹም ስሕተት ነው። እንኳን እግዚአብሔር ይቅርና ፈቃድ የሰጠችው ባሏ እንኳን ከፍቅሯ የተነሣ በቸልታ እንዳየችው አያስብላትም። በእርግጥም በመንፈስ መነጽር ስንመለከተው ይህ ዓይነት ፈቃደኝነት ከፍቅር ሊመነጭ አይችልም። ምክንያቱም ዝሙት ዓመፅ ነው ውሸትም ነው። ፍቅር ደግሞ "ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም።" ይላልና። ፩ኛ ቆሮ. ፲፫:፮-፯

በሌላ አንፃር አንዲት ሴት ለባሏ መልካም ፍቅር ከሌላት ማመንዘሩን ላትቃወም፣ ምንም ላትቀናና ንቃ ልትተወው ትችላለች ወይም ባሏን በአጥፊነት ለመወንጀል ከፈለገች እንዲያመነዝር ሁኔታዎችን ራሷ ልታመቻችለት ትችላለች። በዚህ ድርጊቷ ምንም ወንጀለኛ ብትሆን ባሏን ከተጠያቂነት ነጻ የሚያወጣው ምንም ምክንያት የለም። ሚስቱ ብትፈቅድለት ወይም ብታሰናክለውም ያፈረሰው የእግዚአብሔርን ሕግ ነውና።

"እልክ ምላጭ ያስውጣል" ተብሎ ይተረታል። እልክ መንፈሣዊና ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም ብዙ ጊዜ ግን ጥሩ ገጽታ የለውም።

## ዋቢ መጻሕፍት


1. ሰማንያ ወአሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ (አማርኛ); 1980 ዓ.ም።
2. አዲስ ኪዳን (በግዕዝ);1957 አሥመራ።
3. ወንጌል ቅዱስ (አንድምታ); ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት, 1988 ዓ.ም. አ.አ።
4. መልክተተ ጳውሎስ (አንድምታ); ትንሣኤ ዘ/ ማተሚያ ቤት, 1988 ዓ.ም.
5. መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ (አንድምታ) ; ትንሣኤ ዘ/ማተሚያ ቤት.
6. መዝሙረ ዳዊት (አንድምታ); ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት, 1982.
7. አሪት ዘፍጥረት አንድምታ (እጅ ጽሑፍ)
8. መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ(አንድምታ); ትንሣኤ ዘ/ማተማያ ቤት. 1989
9. መጽሐፈ ቅዳሴ /አንድምታ/;ትንሣኤ ዘ/ማተሚያ ድርጅት. 1988. አ.አ።
10. ፍትሐ ነገሥት/አንድምታ/; በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት,1958.አ.አ
11. ግብረ ሕማማት /ግዕዝ/;ትንሣኤ ዘ/ማተሚያ ድርጅት,1990.አ.አ
12. ተአምረ ማርያም።
13. ድርሳነ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/አንድምታ/; ተስፋ ገ/ ሥላሴ ማተ

 ቤት,1988 ,አ.አ።
14. ድርሳነ ሚካኤል; ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት,1992,አ.አ።
15. አርጋኖነ ማርያም /ግዕዝ/;ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት.አ.አ።
16. ሰዋሰወ ግዕዝ; ትንሣኤ ዘ/ማተሚያ ድርጅር, 1987, አ.አ።
17. የተለያዩ ወራት አሕማር/ሐመሮች/እና መለከት መጽሔቶች እንዲሁም የተ

 ስምዐ ጽድቅ ጋዜጦች።
18. ገድለ ተክለ ሃይማኖት; ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት,1984.አ.አ።
19. የጋብቻ ሕይወት በመጽሐፍ ቅዱስ; ከኃ/ማርያም ተገኝ,1988,አዋሳ።
20. ሥነ-ምግባር; ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ። ግንቦት 28/1948 ዓም ተስፋ

 ማተሚያ ቤት።
21. ተግሣፅ; ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1987 ,አ.አ።


ꙮ ꙮ ꙮ

የሰ/ደ/ገ/ቅ/ሚካኤል
ሠ/ት/ቤት